## ኢትዮጵያ፡ የ2012 የሰብአዊ መብት ሪፖርት

### አጭር ማጠቃለያ

ኢትዮጵያ በፌዴራላዊ ስርዓት የምትመራ አገር ነች፡፡ ጠቅላይ ሚኒስትር መለስ ዜናዊ ነሐሴ 14 ቀን 2004 ዓ.ም. ከዚህ ዓለም በሞት ተለዩ፡፡የኢትዮጵያ ሕዝቦች አብዮታዊ ዴሞክራሲያዊ ግንባር (ኢሕአዴግ) በወቅቱ ምክትል ጠቅላይ ሚኒስትር የነበሩትን ኃይለማርያም ደሳለኝን መለስን ተክተው የፓርቲው ሊቀመንበር እንዲሆኑ መረጣቸው፡፡ ቀጥሎም ኢሕአዴግ ለጠቅላይ ሚኒስትርነት በዕጩነት አቀረባቸው፡፡ የተወካዮች ምክር ቤት መስከረም 11 ቀን 2005 ዓ.ም. ኃይለማርያም ደሳለኝን በጠቅላይ ሚኒስትርነት መረጠ፡፡ በ2002 በተካሄደው አገር አቀፍ የፓርላማ ምርጫ፣ ኢሕአዴግ እና አጋር ድርጅቶች ካሉት 547 የፓርላማ መቀመጫዎች 545ቱን በማሸነፍ በተከታታይ ለአራተኛ የአምስት ዓመት የሥራ ዘመን በሥልጣን ላይ ለመቆየት ችለዋል፡፡ ምንም እንኳ ምርጫዎቹን እንዲታዘቡ የተፈቀደላቸው አንጻራዊ በሆነ አነጋገር በቁጥር አነስተኛ የሆኑ ዓለም አቀፍ ታዛቢዎች የድምፅ አሰጣጡ ቴክኒካዊ ገጽታዎች በብቃት ተከናውነዋል ብለው ቢደመድሙም፣ አንዳንዶች ደግሞ ከምርጫው አስቀድሞ ለነጻ እና ፍትኃዊ ምርጫ የተመቻቸ ሁኔታ እንዳልነበረ ጠቅሰዋል፡፡

የጸጥታ ኃይሎች ተጠሪነት በጠቅላላው ለሲቪል ባለስልጣናት ቢሆንም፤ ልዩ ፖሊስ እና የአካባቢ ሚሊሻዎች ከሲቪል ቁጥጥር ውጭ ወይም በራሳቸው የተንቀሳቀሱባቸው አጋጣሚዎች ነበሩ፡፡

በተቃዋሚ የፖለቲካ ፓርቲ አባላት፣ የሰባዓዊ መብት ተሟጋቾች፣ ጋዜጠኞች እና ብሎገሮች ላይ ፖለቲካዊ ይዘት ያላቸውን ክሶችና የፍርድ ውሳኔዎች በማሳለፍ ሃሳብን በነጻነት የመግለጽ እና የመደራጀት መብት ላይ የተደረጉ ክልከላዎች እና በሕትመት ሚዲያው ላይ እየጨመሩ የመጡ እገዳዎች በጣም ጎልተው ከታዩ የሰብዓዊ መብት ችግሮች መካከል ናቸው፡፡ በሐምሌ ወር የጸጥታ ኃይሎች መንግስት በሃይማኖት ጉዳዮች ውስጥ ጣልቃ ገብቷል በማለት የተቃወሙ ሙስሊሞችን ኃይል ተጠቅመው አስረዋቸዋል፡፡ መንግስት በበጎ አድራጎት ድርጅቶች እና ማሕበራት አዋጅ አማካኝነት በሲቪክ ማህበራት እና መንግስታዊ ባልሆኑ ድርጅቶች እንቅስቃሴዎች ላይ የጣለው እገዳ እንደቀጠለ ነው፡፡

ሌሎች የሰብኣዊ መብት ችግሮች በጸጥታ ኃይሎች በእስረኞች ላይ የሚፈጸሙ የዘፈቀደ ግድያዎች፣ ማሰቃየት ፣ ድብደባ፣ ማዋከብ እንዲሁም በዘፈቀደ በቁጥጥር ሥር ማዋል እና ማሰር፤ ያለ ክስ ማሰር እና ከፍርድ ሒደት በፊት ለተራዘመ ጊዜ አስሮ ማቆየት፤ ደካማ፣ የተጨናነቀ እና በፖለቲካ ተጽዕኖ ስር የወደቀ ፍርድ ቤት፣ ሕገ-ወጥ ብርበራን ጨምሮ የዜጎችን የግላዊ ህይወት መብቶች መጣስ፣በመንግስት የሰፈራ መርሃግብር አፈጻጸም ወቅት ተፈጸሙ የተባሉ የመብት ጥሰቶች፣

በአካዳሚያዊ ነጻነት ላይ የተደረጉ ክልከላዎች፤ በመሰብሰብ በመደራጀት እና ከቦታ ቦታ በመንቀሳቀስ ነጻነት ላይ የተጣሉ ገደቦች፣ በሃይማኖታዊ ጉዳዮች ጣልቃ የመግባት ክሶች፤ ዜጎች መንግስታቸውን መቀየር የሚችሉበትን አቅም መገደብ፤ በፖሊስ፣ በአስተዳደር ኃላፊዎች እና በፍርድ ቤቶች የሚፈጸም ሙስና፤ አመጽ እና በሴቶች ላይ የሚደርስ ማህበራዊ መድልኦ እንዲሁም የሕጻናት መብት ጥሰት፤ የሴት ልጅ ግርዛት፤ ሕጻናትን በኢኮኖሚያዊ ስራ እና በወሲብ ንግድ ማሰማራት፤ ሕገወጥ የሰዎች ዝውውር፤ በአካል ጉዳተኞች ላይ የሚደርስ ማህበራዊ መገለል፤ አነስተኛ የሕዝብ ብዛት ባላቸው ጎሳዎች መካከል የተነሱ ግጭቶች፤  ባላቸው ወሲባዊ ዝንባሌ የተነሳ እና ኤች አይ ቪ/ ኤድስ በደማቸው የሚገኝ ሰዎችን ማግለል፤ በሰራተኛ መብቶች ላይ የተጣሉ ገደቦች፣ የግዳጅ ስራ፣ እንዲሁም ሕፃናትን በግዳጅ ማሠራትን ጨምሮ የሕፃናት ጉልበት ብዝበዛን ያካትታሉ።

አጥፊዎችን ሕግ ፊት ያለማቅረብ ችግር ነበር። በአንዳንድ አጋጣሚዎች ካልሆነ በስተቀር፣ መንግስት ከሙስና ውጪ ጥፋት የፈጸሙ ባለስልጣናት ላይ ክስ የመመስረትም ሆነ የመቅጣት እርምጃ አልወሰደም።

የመብት ጥሰቶቹ የተፈጸሙት በሶማሌ ክልል በሚንቀሳቀሰውና በተከፋፈለው አማጺ ተገንጣይ ብሔር ተኮር ቡድን ማለትም የኦጋዴን ብሔራዊ ነጻነት ግንባር (ኦብነግ) አንጃዎች ነበር። በጥር ወር በአፋር ክልል በነበሩ የውጭ አገር ቱሪስቶች ላይ ለተፈጸመ ጥቃት የአፋር አብዮታዊ ዴሞክራሲ ሕብረት ግንባር (አርዱፍ)  ኃላፊነት ወስዷል።

### ክፍል አንድ - የሰው ልጅን ክብር መጠበቅ፣ ከሚከተሉት ነጻ የመሆን መብትን ጨምሮ፡

### ሀ. በዘፈቀደ ወይም ከሕግ ውጪ ሕይወትን ማጥፋት

የጸጥታ ኃይሎች ተቃውሞዎችን ለማስቆም ግድያዎችን ፈጽመዋል፤ ለሞት የሚያበቃ ኃይል ተጠቅመዋል (ክፍል 2፣ ለ ን ይመልከቱ) ። ሪፖርቱ በሚሸፍነው ዓመት በመንግስት ኃይሎች በዋነኝነትም በክልል መንግስታት በሚደገፉ ሚሊሻዎች እና በርዝራዥ የኦብነግ ኃይሎች መካከል በተበታተነ መልኩ የሚደረጉ ውጊያዎች ቀጥለዋል። በብሔረሰቦች መካከል በተነሱ ግጭቶች በዓመቱ ከ100 እስከ 150 የሚሆኑ ሰዎችን ለሞት ተዳርገዋል (ክፍል 6 ን ይመልከቱ) ።

ሚያዝያ 20 ቀን ታጣቂዎች ጋምቤላ ክልል በሚገኘው የሳዑዲ ስታር ቅጥር ግቢ ውስጥ በፈጸሙት ጥቃት ቢያንስ አምስት ሰዎች በመገደላቸው እና በርካቶች በመቁሰላቸው ምክንያት የኢትዮጵያ የጸጥታ ኃይሎች በወሰዱት እርምጃ ስድስት የሚሆኑ ሰዎችን እንደገደሉ ተዘግቧል።

የካቲት 4 ቀን በሶማሌ ክልል የልዩ ፖሊስ ኃይል አባላት በክልሉ ኦጋዴን አካባቢ ለስብሰባ ተቀምጠው በነበሩ ሰዎች ላይ ተኩስ ከፍተው 20 ሰዎችን መግደላቸው ተዘግቧል። የአካባቢው ነዋሪዎች ስብሰባውን የጠሩት ቀደም ሲል በአንድ የአገር ሽማግሌ ላይ በተፈጸመ ግድያ ጉዳይ ለመወያየት እንደነበረ ተነግሯል። በዚሁ ወቅት በርካቶችም ለእስር ተዳርገዋል።

አርዱፍ ጥር 9 ቀን በአፋር ክልል በነበረ የውጭ ቱሪስቶች ቡድን ላይ ለተፈጸመው ጥቃት ኃላፊነቱን ወስዷል። በጥቃቱ አምስት አውሮፓውያን ሕይወታቸው ሲያልፍ ሁለት ኢትዮጵያውን እና ሁለት አውሮፓውን ታግተዋል። የታገቱት አውሮፓውያን በመጨረሻ የተለቀቁ ሲሆን፤ ኢትዮጵውያኑ ታጋቾች ግን ስላሉበት ቦታም ሆነ ስለድህንነታቸው ሁኔታ እስከዓመቱ መጨረሻ ለማወቅ አልተቻለም።

## ለ. የሰዎች መሰወር

ፖለቲካዊ መንስዔ ያለው የሁለት ሰዎች መሰወር ጉዳይን የሚጠቁም ሪፖርት የቀረበ ሲሆን፤ በዚህም የፀጥታ ኃላፊዎች የተቃዋሚ ፖለቲካ ተሟጋቾችን ለአጭር ጊዜ ከማንም ጋር በማይገናኙበት ሁኔታ በቁጥጥር ሥር አውለዋቸው ነበር።

ፌዴራል ፖሊስ ሰኔ 8 ቀን የመላው ኢትዮጵያ አንድነት ድርጅት (መኢአድ) የጭልጋ ወረዳ ምክትል ሊቀመንበር መለስ አሸሬን፤ እንዲሁም በሰሜን ጎንደር ዞን የመኢአድ ስራ አስፈጻሚ አባል ታድሎ ተፈራን በአማራ ክልል ሰሜን ጎንደር አካባቢ እንዳሰረ ተነግሯል። መለስ እና ታድሎ በእስራቱ ወቅት የነበሩበት ቦታ አይታወቅም ነበር። ሆኖም ኃላፊዎች በነሐሴ ወር ለቀዋቸዋል።

## ሐ. ማሰቃየት እና ሌላ ጭካኔ የተሞላበት፣ ኢ-ሰብአዊ፣ ወይም ሰብአዊ ክብርን የሚያዋርድ አያያዝ ወይም ቅጣት

ሕገ-መንግሥቱ እና ሕጉ እንዲህ ያሉ ተግባራትን (ማሰቃየትን እና ማንገላታትን) የሚከለክሉ ቢሆንም፤ የጸጥታ ኃይሎች በእስር ላይ ያሉ ሰዎችን እንዳሰቃዩ አልያም በደል እንዳደረሱባቸው በርካታ ሪፖርቶች አመልክተዋል።

ባለሥልጣናት በሙስሊሞች ጉዳይ መጽሔት አዘጋጅ እና አምደኛ አህመዲን ጀበል ላይ ማሰቃየት ፈጽመዋል ተብሏል (ክፍል 2፣ ሀ ን ይመልከቱ)።

የተባበሩት መንግሥታት የፀረ-ማሰቃየት ኮሚቴ (UN Committee Against Torture) በ2003 ሪፖርቱ፣ በፖሊስ፣ በወህኒ ቤት ኃላፊዎች እና ጦር ሠራዊቱን ጨምሮ በሌሎች የፀጥታ ኃይል አባላት፣ የፖለቲካ ልዩነት ባላቸው ግለሰቦች እና በተቃዋሚ ፓርቲ አባላት፣ በተማሪዎች፣ በሽብር

ተጠርጣሪዎች፣ እንዲሁም እንደ ኦብነግ እና ኦነግን የመሰሉ ነውጠኛ ተገንጣይ ቡድኖችን ይደግፋሉ ተብለው በሚጠረጠሩ ሰዎች ላይ ‹‹የማሰቃየት ዘዴን አዘውትሮ መጠቀም››ን አስመልክቶ የሚደርሱት ‹‹በርካታ እና ተደጋጋሚ አቤቱታዎች›› ‹‹እጅግ የሚያሳስቡት›› መሆኑን ገልጿል፡፡ ኮሚቴው በሪፖርቱ፣ እንዲህ ያሉ ተግባራት ብዙዉን ጊዜ በፖሊስ ጣብያዎች፣ በማቆያ ማዕከላት፣ በፌደራል ወህኒ ቤቶች፣ በወታደራዊ ሠፈሮች፣ እና በይፋ በማይታወቁ ወይም በምስጢራዊ የማቆያ ስፍራዎች፣ በሹመኞች እና በእነርሱ አነሳሽነት፣ አልያም በእነርሱ ይሁንታ እንደሚፈፀሙ ሪፖርት አድርጓል፡፡ ሪፖርቱ በተጠናቀረበት ወቅት ይህን መሰል የመብት ጥሰቶችን የሚመለከቱ አንዳንድ ሪፖርቶች ቀርበዋል፡፡

የታመኑ ምንጮች አዲስ አበባ በሚገኘው ማዕከላዊ የፖሊስ ወንጀል ምርምራ ዋና መሥሪያ ቤት፣ መርማሪ ፖሊሶች [በቁጥጥር ሥር የዋሉ እስረኞች] ጥፋተኝነትን እንዲናዘዙ ለማድረግ አዘውትረው አካላዊ ድብደባን እንደተጠቀሙ አረጋግጠዋል፡፡ ባለሥልጣናት የዲፕሎማቲክ ማኅበረሰብ አባላት እና መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች በማዕከላዊ ወንጀል ምርመራ የሚገኙ እስረኞችን እንዳይጎበኙ ከልክለዋል፡፡

በሂውማን ራይትስ ዎች ሪፖርት መሰረት በጋምቤላ ክልል የሳዑዲ ስታር ቅጥር ግቢ ሚያዝያ 20 ቀን ታጣቂዎች የፈጸሙትን ጥቃት ተከትሎ ወታደሮች ሰዎችን በዘፈቀደ አስረዋል፤ አስገድደው ደፍረዋል (ክፍል 1፣ ሀ ን ይመልከቱ)፡፡ አስገድዶ መድፈር መፈጸሙን የሚያረጋግጥ ተጨማሪ ሪፖርት አልቀረበም፡፡

**የማረሚያ ቤቶች እና የማቆያ ማዕከላት ሁኔታ**

ማረሚያ ቤቶች እና የቅድመ-ፍርድ ሒደት ማቆያ ማዕከላት ይዞታ በአስከፊ ደረጃ ላይ የሚገኝ እና በአንዳንድ ሁኔታዎችም ለሕይወት አስጊ ነው፡፡ ባለስልጣናት በእስረኞች ላይ ድብደባ እንደሚፈጽሙ የሚገልጹ በርካታ ሪፖርቶችም ቀርበዋል፡፡ በአንዳንድ ሁኔታዎች ድብደባውን ተከትሎ እስረኞች በቂ የሕክምና ክትትል አይደረግላቸውም፡፡

<u>አካላዊ ይዞታ</u>፡ ከመስከረም ወር ጀምሮ ከ 70,000 — 80,000 ሰዎች በእስር ቤቶች የሚገኙ ሲሆን፤ ከነዚህም 2,500 ሚሆኑት ሴቶች፤ 600 ደግሞ ከእናቶቻቸው ጋር የታሰሩ ሕጻናት ይገኙበታል፡፡ ወጣት አትፊዎች አልፎ አልፎ ከአዋቂዎች ጋር የሚታሰሩ ሲሆን፣ ጨቅላ ሕጻናትም እንዲሁ ከእናቶቻቸው ጋር ታስረዋል፡፡ በአጠቃላይ ወንድ እና ሴት ታራሚዎች የተለያየ ቦታ ይታሰራሉ፡፡

(በማረሚያ ቤቶች) በተለይ በመኝታ ቦታዎች አስከፊ የሆነ መጨናነቅ ማየት የተለመደ ነው፡፡ መንግሥት ለአንድ እሥረኛ ለምግብ፣ ለውሃ እና ለጤና እንክብካቤ በቀን ስምንት ብር ገደማ መድቧል፡፡

ብዙ እስረኞች ይህን ከመንግሥት የተመደበላቸውን ገንዘብ የቤተሰብ አባላት በሚያቀብሏቸው የዕለት ምግብ ወይም በአካባቢው ካሉ ሻጮች በሚገዙት ምግብ ይደጉማሉ፡፡ ይሁንና አንዳንድ እስረኞች ከቤተሰቦቻቸው ምግብ እንዳይቀበሉ እንደተከለከሉ ሪፖርት ተደርጓል፡፡ በፌደራል ማረሚያ ቤቶች የሚሰጠው የህክምና አገልግሎት በቂ አይደለም፡፡ በክልል ማረሚያ ቤቶች የሕክምና አገልግሎት የለም በሚባል ደረጃ ላይ ይገኛል፡፡ እንደአብዛኛው የአገሪቱ ዜጋ ሁሉ እስረኞችም የመጠጥ ውሃ የማግኘት ችግር አለባቸው፡፡ የውሃ እጥረት ለንጽህና መጓደል መንስዔ ሆኗል፤ አብዛኛዎቹ ማረሚያ ቤቶችም የመፀዳጃ ቦታ ችግር አለባቸው፡፡ ብዙ እስረኞች በማቆያ ሥፍራ ሳሉ ከባድ የጤና ችግሮች ቢያጋጥሟቸውም፣ የሚያገኙት ህክምና በቂ አልነበረም፡፡ በዓመቱ ከጤና ጥበቃ ሚኒስቴር የተገኘ መረጃ እንደሚያመለክተው በአገሪቱ በተለያዩ እስር ቤቶች ከሚገኙ እስረኞች 62 በመቶ የሚሆኑት የአእምሮ ጤና መታወክ የገጠማቸው ሲሆን፤ ለብቻ መታሰር፣ የእስር ቤቶች መጨናነቅ እና በቂ የጤና እንክብካቤ ለማግኘት አለመቻል በምክንያትነት ተጠቅሷል፡፡

አገሪቱ ስድስት የፌደራል እና 120 የክልል ማረሚያ ቤቶች አሏት፡፡ በተጨማሪም ዴዴሳ፣ ብር ሸለቆ፣ ጦላይ፣ ሆርማት፣ ብላቴ፣ ታጠቅ፣ ጂጂጋ፣ ሆለታ እና ሰንቀሌ የሚገኙትን ጨምሮ በመላ አገሪቱ በርካታ ይፋ ያልሆኑ የማቆያ ማዕከላት አሉ፡፡ አብዛኛዎቹ የሚገኙት በወታደራዊ ሰፈሮች ነው፡፡

ክስ ከመመስረቱ በፊት ተጠርጣሪዎች ፖሊስ ጣቢያዎች ውስጥ በሚገኙ ማቆያ ቤቶች የሚታሰሩ ሲሆን፤ በነዚህ ማቆያ ማዕከላት ያለው አያያዝም ከቦታ ቦታ ይለያያል፡፡ በፖሊስ ጣቢያዎች በቅድመ ክስ እስር ሂደትን በተመለከተ የወጡ ሪፖርቶች በማቆያ ቤቶቹ የንጽሕና መጓደል፣ ቤተሰብንና የሕግ አማካሪን ጨምሮ በጎብኝዎች እንዳይጠየቁ መከልከል እንዲሁም ፖሊስ በእስር ላይ ባሉ ሰዎች ላይ ድብደባ እንደሚፈጽም ያመለክታሉ፡፡

<u>አስተዳደር</u>፡ ግልጽ አሰራር ባለመኖሩ የተነሳ እስርን የሚመለከት መዝገብ በበቂ ሁኔታ ተይዟል ለማለት ያስቸግራል፡፡ ኃላፊዎች አመጽ የሌለበት ወንጀል ለፈጸሙ ታሳሪዎች አማራጭ የቅጣት ዘዴዎችን አልዘረጉም፡፡ በእስር ቤቶች ለሚነሱ ቅሬታዎች ምላሽ የሚሰጡ የዕንባ ጠባቂ ባለሙያዎች የሉም፡፡ በአንዳንድ እስር ቤቶች ለእስረኞች አገልግሎት የሚሰጡ የሕግ ድጋፍ ማዕከላት ነበሩ፡፡ የማረሚያ ቤቶች ኃላፊዎች አብዛኛውን ጊዜ ጠያቂዎች (እስረኞችን) እንዲጎበኙ ፈቅደዋል፡፡ በአንዳንድ ሁኔታዎች ቤተሰቦች እስረኞችን መጠየቅ የሚችሉበት ጊዜ በዓመት ውስጥ ለጥቂት ቀናት እንዲሆን ተደርጎ ነበር፡፡ በሽብር ተግባር የተከሰሱ እስረኞች ቤተሰቦች ታሳሪዎችን እንዳያገኙ የተከለከሉባቸውን አጋጣሚዎች የጠቀሱ ሲሆን፤በሽብርተኝነት የተከሰሱም እንዲሁ ከጠበቆቻቸው ወይም ከፓርቲዎቻቸው ተወካዮች እንዳይገናኙ መደረጋቸው ሪፖርት ተደርጓል፡፡

በአጠቃላይ እስረኞች እምነታቸውን በነፃነት እንዲያራምዱ ቢፈቀድላቸውም፣ እንደ ማረሚያ ቤቱ አስተዳደር ውሳኔ ሁኔታው ከማረሚያ ቤት ማረሚያ ቤት አንዳንዴም በአንድ ማረሚያ ቤት ውስጥ ባሉ ክፍሎች መካከል ይለያያል፡፡ እስረኞች በማረሚያ ቤት ውስጥ በቂ የፀሎት ስፍራ እንደተከለከሉ የተናገሩባቸው አጋጣሚዎች ነበሩ፡፡ እስረኞች ፣ ፍርድ ቤት በሚቀርቡበት ጊዜ፣ ስለ እስር ቤቱ ሁኔታ ወይም ስለ አያያዛቸው ክሱን ለሚሰማው ዳኛ አቤቱታ እንዲያቀርቡ ተፈቅዶላቸዋል፡፡

<u>ክትትል</u>፡ በዓመቱ ዓለም አቀፍ የቀይ መስቀል ኮሚቴ የክልል ማረሚያ ቤቶችን ጎብኝቷል፡፡ ጉብኝቶቹ የተደረጉት መንግስት ከ 1996 ጀምሮ በቀይ መስቀል ላይ ጥሎት የነበረውን የጉብኝት ክልከላ ካነሳ እና መደበኛ ጉብኝት እንዲያደርግ ከፈቀደ በኋላ ነው፡፡

የክልል ባለስልጣናት የመንግስት እና መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች ተወካዮች ሶስተኛ ወገን በሌለበት አዘውትረው እስረኞችን እንዲያገኙ ፈቅደዋል፡፡ የኢትዮጵያ ሰብዓዊ መብት ኮሚሽን የፌዴራል እና የክልል ማረሚያ ቤቶችን በመጎብኘት፤ በስፋት ይፈጸማሉ ስለሚባሉ የሰብዓዊ መብት ጥሰቶች የማረሚያ ቤቶች ኃላፊዎችንና እስረኞችን አነጋግሯል፡፡ ጀስቲስ ፎር ኦል - ፕሪዝን ፌሎውሺፕ ኢትዮጵያ የተሰኘው አገር በቀል በጎ አድራጎት ድርጅት የተለያዩ ማረሚያ እና የማቆያ ማዕከላትን የመጎብኘት ፈቃድ ተሰጥቶታል፡፡

<u>መሻሻሎች</u>፡ መንግሥት እና የወህኒ ቤት አስተዳደር አካላት ጀስቲስ ፎር ኦል - ፕሪዝን ፌሎውሺፕ ኢትዮጵያ (JFA-PFE) የተሰኘው የበጎ-አድራጎት ድርጅት፣ የወህኒ ቤቶችን ሁኔታ ለማሻሻል ለሚያደርጋቸው ጥረቶች ትብብር አድርገዋል፡፡ ድርጅቱ ከሌሎች እስር ቤቶች እጅግ የሚሻሉ ሞዴል ማረሚያ ቤቶችን በአዳማ እና በመቀሌ ከተሞች አቋቁሟል፡፡ መንግስትም በዓመቱ ውስጥ በትግራይ፣ አማራ፣ ኦሮሚያ እና ደቡብ ብሔሮች ብሔረሰቦች እና ሕዝቦች ክልል ለሚገኙ ማረሚያ ቤቶች የእድሳት ስራዎችን አከናውኗል፡፡

**መ. በዘፈቀደ በቁጥጥር ሥር ማዋል ወይም ማሠር**

ምንም እንኳ የአገሪቱ ሕገ-መንግሥት እና ሕጉ በዘፈቀደ በቁጥጥር ስር ማዋል እና ማሠርን ቢከለክሉም፣ መንግሥት በመፈጸም ረገድ በጸደጋጋሚ ቸልተኝነት ይታይበታል፡፡ ፖሊስና የጸጥታ ኃይሎች ሰዎችን በዘፈቀደ በቁጥጥር ስር እንዳዋሉ እና እንዳሰሩ የሚጠቁሙ በርካታ ሪፖርቶች ቀርበዋል፡፡

በሶማሌ ክልል የሚሰሩ ሲቪሎች፣ አለም አቀፍ መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች እና የዕርዳታ ድርጅቶች የመንግስት የጸጥታ ኃይሎች፣ የአካባቢ ሚሊሻዎች እና የኦጋዴን ብሔራዊ ነጻነት ግንባር (ኦብነግ) የሰብዓዊ መብት ጥሰት እንደሚፈጽሙና በዘፈቀደ እንደሚያስሩ ሪፖርት አቅርበዋል፡፡

**የፖሊስ እና የፀጥታ መዋቅር ሚና**

የፌዴራል ፖሊስ ኮሚሽን ተጠሪነቱ ለፌዴራል ጉዳዮች ሚኒስቴር ሲኾን፣ የሚኒስቴር መስሪያ ቤቱም ተጠሪነቱ ለፓርላማው ነው፤ ነገር ግን በተግባር ይህ የተጠሪነት ተዋረድ የላላ ነው፡፡ የአገሪቱ ዘጠኝ ክልሎች እያንዳንዳቸው ለክልሉ ሲቪል ባለሥልጣናት (አስተዳደር) ተጠሪ የሆነ የክልል ወይም ልዩ የፖሊስ ኃይል አላቸው፡፡ በመላው አገሪቱ የሚገኙ የአካባቢ ሚሊሽያዎች ከክልልና ከፌደራል ፖሊስ እንዲሁም ከአገሪቱ ሠራዊት ጋር ልል በሆነ ቅንጅት ይንቀሳቀሳሉ - የቅንጅታቸው ደረጃ በየክልሉ ይለያያል፡፡ በአመዛኙ እነኝህ ሚሊሽያዎች የአካባቢው የኢሕአዴግ የፖለቲካ ሹማምንት ተቀጥላ ሆነው ይሠራሉ፡፡

የፀጥታ ኃይሎች ሥራቸውን በብቃት ያከናውናሉ፤ ነገር ግን [በሕግ] ያለመጠየቅ አሳሳቢ ችግር ነበር፡፡ የተፈፀሙ የሕግ ጥሰቶችን ለማጣራት የፌደራል ፖሊስ የሚጠቀምባቸው ስልቶች አይታወቁም፡፡ የሶማሌ ክልል ልዩ ፖሊስ የሰብዓዊ መብት ጥሰቶችን እንደፈጸመ የሚገልጹ በርካታ አቤቱታዎች ቀርበዋል፡፡ ብዙ የክልሉ ፖሊስ አባላትም ባሳዩት የዲሲፕሊን ጉድለት የተነሳ እንደታሰሩ ሪፖርት ተደርጓል፡፡ መንግሥት በዘፈቀደ ማሰርን እና በሰላማዊ ሰዎች ላይ ድብደባ መፈፀምን በመሳሰሉ በፀጥታ ኃይሎች የተፈፀሙ የመብት ጥሰቶች ላይ ያካሄዳቸው ምርመራዎችን ውጤት በይፋ የሚገልጽባቸው አጋጣሚዎች እጅግ በጣም ጥቂት ናቸው፡፡

መንግሥት ለፖሊስ እና ለጦር ሠራዊት ተቀጣሪዎች በሰብአዊ መብት ላይ ያተኮሩ ስልጠናዎች ለመስጠት የሚያደርገውን ጥረት ቀጥሏል፡፡ በዓመቱ መንግሥት በሕገ-መንግሥቱ እንዲሁም በዓለም አቀፍ የሰብዓዊ መብቶች ሕግጋት እና ስምምነቶች ዙርያ ተጨማሪ ትምህርቶችን በማካተት በሰብአዊ መብት ላይ የሚሰጠውን ሥልጠና እና ሥርዓተ-ትምህርት ለማሻሻልና በበቂ ባለሙያዎች እንዲሰጥ ለሚያደርገው ጥረት ጀስቲስ ፎር ኦል - ፕሪዝን ፌሎውሺፕ ኢትዮጵያ ከተሰኘው መንግሥታዊ ያልሆነ ድርጅት እና ከኢትዮጵያ ሰብአዊ መብት ኮሚሽን ድጋፍ አግኝቷል፡፡ ጀስቲስ ፎር ኦል - ፕሪዝን ፌሎውሺፕ ኢትዮጵያ እና የኢትዮጵያ ሰብአዊ መብት ኮሚሽን በትግራይ፣ አማራ፣ ኦሮሚያ፣አፋር፣ ደ/ብ/ብ/ሕ/ክ/መ፣ጋምቤላ እና አዲስ አበባ ለሚገኙ ፖሊስ ኮሚሽነሮች፣ አቃብያነ ሕግ፣ ዳኞች፣ የማረሚያ ቤቶች አስተዳዳሪዎች እንዲሁም ሚሊሽያዎች በሰብአዊ መብት ላይ ያተኮረ ስልጠና ሰጥተዋል፡፡

## በቁጥጥር ሥር የማዋል ስነስርዓት እና በእሥር ላይ ያሉ ሰዎች አያያዝ

ምንም እንኳ ሕገ-መንግሥቱ እና የወንጀለኛ መቅጫ ሕጉ በቁጥጥር ሥር የዋሉ ሰዎች በ48 ሰዓታት ውስጥ ፍርድ ቤት ሊቀርቡና ክስ ሊመሠረትባቸው እንደሚገባ ቢደነግጉም፣ አንዳንድ ጊዜ ይህ ድንጋጌ ተግባር ላይ አይውልም። ከበድ ያለ ጥፋት በመፈፀም የተጠረጠሩ ሰዎች የፍርድ ቤት ይሁንታ ሲገኝ ክስ ሳይመሠረትባቸው ለ14 ቀናት፣ እንዲሁም የምርምራ ሒደቱ ካልተጠናቀቀ፣ ለተጨማሪ የ14 ቀን ጊዜ በእሥር ሊቆዩ ይችላሉ። በፀረ-ሽብርተኝነት ሕጉ ፖሊስ ሰዎችን የ28-ቀናት ጊዜ እየጠየቀ እስከ አራት ወራት ለሚደርስ ጊዜ ክስ ሳይመሠርትባቸው ለማቆየት ፍርድ ቤትን ሊጠይቅ ይችላል። ሕጉ በይፋ ከሚታወቅ ማረሚያ ቤት ውጪ እስረኞች እንዳይታሰሩ ቢከለክልም፤ የአካባቢ ሚሊሽያዎች እንዲሁም መደበኛ እና መደበኛ ያልሆኑ ሕግ አስፈጻሚ አካላት በኦፊሴል የማይታወቁ በርካታ እስር እስር ቤቶችን ተጠቅመዋል።

ህጉ የዋስ መብት ይፈቅዳል። ነገር ግን የዋስትና መብት ለነፍስ ማጥፋት፣ ለአገር ክህደት እና ለሙስና ክሶች ላይ ተፈጻሚ አይደለም። በአንድ በጣም በሚታወቅ ክስ ላይ ያስቻሉ ዳኛ የፍትህ ጋዜጣ ዋና አዘጋጅ ተመስገን ደሳለኝ ከተለቀቀ መንግስትን የሚያንቋሽሽ ጽሁፍ መጻፍ ሊቀጥል ይችላል በሚል ዋስትና ከልክለዋል። ዳኛው አክለውም ሊጠፋ ይችላል የሚል ምክንያት ያቀረቡ ሲሆን፤ እንደእውነቱ ግን ክሱ ከመመስረቱ በፊት ከአንድ ወር ለሚበልጥ ጊዜ በነጻነት ይንቀሳቀስ ነበር። ነሐሴ 22 ቀን ባለስልጣናት የመሰረቱበትን ክስ ካነሱ በኋላ በታኅሳስ ወር መዝገቡን በድጋሚ በመክፈት ክሱ እስከ ዓመቱ መጨረሻ ድረስ ሲሰማ ቆይቷል። በአብዛኛው የመንግስት አካላት ለዋስትና የሚጠይቁት የገንዘብ መጠን በ500 እና በ10,000 ብር መካከል ሲኾን፣ ይህም ከአብዛኞቹ ዜጎች አቅም በላይ ነው። ተጠርጣሪዎች በዋስ እንዲለቀቁ ከፍርድ ቤት የሚተላለፍን ትዕዛዝ የፖሊስ አባላት ሁልጊዜ አያከብሩም። በራሳቸው ወጪ የግል የሕግ አማካሪ ለመቅጠር አቅም ለሌላቸው እስረኞች መንግሥት ጠበቃ ያቆምላቸዋል፤ ይህ የሚሆነው ግን ጉዳያቸው ፍርድ ቤት ሲቀርብ ብቻ ነው። ተጠርጣሪዎች በቅድመ ፍርድ ሒደት በእሥር ላይ ሳሉ፣ ከሕግ አማካሪ ጋር ይገናኙ ዘንድ ባለሥልጣናቱ እጅግ ውሱን በሆነ ደረጃ ይፈቅዱላቸዋል ወይም ከነጭራሹ ካለመፍቀዳቸውም ሌላ በጤንነታቸው ሁኔታ ላይ ሙሉ መረጃ አይሰጡም፤ ቤተሰብም እንዲጠይቃቸው አይፈቅዱም።

<u>**በዘፈቀደ በቁጥጥር ሥር ማዋል**</u>፡- ባለሥልጣናት ያለ ፍርድ ቤት ማዘዣ ሰዎችን በቁጥጥር ሥር ያውላሉ፤ ከሕግ አማካሪ እና አንዳንዴም ከቤተሰብ አባላት ጋር የመገናኘት መብትንም ይነፍጋሉ፣ ይህ በተለይ ራቅ ባሉ ክልሎች ይታያል።

**<u>ቅድመ-ክስ እሥር</u>**: አንዳንድ እሥረኞች ክስ ሳይመሠረትባቸው እና ፍርድ ቤትም ሳይቀርቡ ለበርካታ ዓመታት መታሠራቸውን ሪፖርት አድርገዋል። በአብዛኛው የፍርድ ሒደት መጓተት የሚከሰተው በተራዘሙ የሕግ ሥነ-ሥርዓቶች፣ በታራሚዎች ብዛት፣ በፍትኅ ሥርዓቱ የቅልጥፍና ማነስ ችግር እና የሰው ኃይል እጥረት ሳቢያ ነው።

**<u>ምህረት</u>**: ለረዥም ዘመናት ሲወርድ ሲዋረድ በመጣው በኢትዮጵያ አዲስ ዓመት ለእስረኞች ምህረት የማድረግ ልማድ መሠረት የፌዴራል መንግሥት መስከረም 1 ቀን ለ1,993 እስረኞች ምህረት አድርጓል። የክልል መንግስታትም በዓመቱ ውስጥ ለእስረኞች ምህረት አድርገዋል። ለምሳሌ የደ/ብ/ብ/ሕ/ክ መንግሥት ለ5,395 እስረኞች፤ የኦሮሚያ ክልላዊ መንግስት ለ4,700 እስረኞች፤ እንዲሁም የአማራ ክልላዊ መንግስት ለ2,607 እስረኞች ምህረት አድርገዋል።

### ሠ. ፍትሃዊ (ግልፅ) የፍርድ ሒደት መነፈግ

ሕጉ ነጻ የዳኝነት ሥርዓትን ደንግጓል። ምንም እንኳ የፍትሀ ብሔር ፍርድ ቤቶች ከፍተኛ በሆነ ነጻነት ቢንቀሳቀሱም፣ የወንጀል ፍርድ ቤቶች ግን ደካማ፣ ከአቅማቸው በላይ የሥራ ጫና ያለባቸው እና ለፖለቲካዊ ተጽዕኖ የተጋለጡ ናቸው። ሕገመንግስቱ ለሐይማኖታዊ እና ለባሕላዊ ወይም ልማዳዊ ፍርድ ቤቶች እውቅና ይሰጣል።

### የፍርድ ሒደት

በሕጉ መሠረት፣ የተከሰሱ ሰዎች ጉዳያቸው በፍርድ ቤት ግልጽ እና ፍትሃዊ በሆነ ሒደት የመዳኘት እና ተቀባይነት ባለው የጊዜ ገደብ ውስጥ ፍርድ የማግኘት፣ (ጥፋተኝነታቸው እስካልተረጋገጠ ድረስ) ንፁህ ተደርጎ የመታሰብ፣ በመረጡት የሕግ አማካሪ (ጠበቃ) የመወከል፣ እንዲሁም የይግባኝ መብት አላቸው። ሕጉ ለተከሳሾች የመከላከያ ምስክሮችን እና ማስረጃዎቻቸውን የማቅረብ፣ ለአቃቤ ሕግ ምስክሮች መስቀለኛ ጥያቄ የማቅረብ፣ እንዲሁም በመንግሥት እጅ የሚገኙ ማስረጃዎችን የማግኘት መብት ይሰጣል። ነገር ግን፣ መንግሥት በተግባር [የተከሳሾችን] መረጃ የማግኘት መብት ሁልጊዜ አያከብርም። የፍርድ ሥርዓቱ በ‹‹ጁሪ›› (ገለልተኛ የማኅበረሰብ ተወካዮች የፍርድ ሒደቱን በሙሉ ተከታትለው ተከሳሹ ጥፋተኛ ነው አይደለም የሚል ብይን የሚሰጡበት አሠራር) አይጠቀምም። የፍርድ ቤቶች የቅልጥፍና ጉድለት እና ብቃት ያለው የሰው ኃይል እጥረት አብዛኛውን ጊዜ የክስ ሒደቶች ከሚገባው በላይ እንዲጓተቱ እና ሕጉ ግልጽ እንዳይሆን አድርጎታል። መንግስት ለስር ፍርድ ቤቶች ዳኞች እና ዐቃቤያነ ሕግ በዋነኝነት ውጤታማ በሆነ የፍትህ አስተዳደር ላይ ያተኮረ ስልጠና መስጠቱን

ቀጥሏል፡፡ አብዛኛውን ጊዜ ተከሳሾች ክስ የመስማት ሂደቱ እስኪጀመር ድረስ የቀረበባቸውን ክስ አለማወቃቸው ተከላካይ ጠበቆች ክሱን ለመከላከል በበቂ መልኩ እንዳይዘጋጁ ያደርጋቸዋል፡፡

ምንም እንኳ በጠበቃዎች እጥረት ምክንያት የአገልግሎት አድማሱ እና ጥራቱ ውሱን ቢሆንም፣ የተከላካይ ጠበቃዎች ጽ/ቤት ጠበቃ የመቅጠር አቅም ለሌላቸው ሰዎች በነጻ የሕግ ምክር አገልግሎት ሰጥቷል፡፡ በመላ አገሪቱ በዋነኝነትም በከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ውስጥ የሚገኙ በርካታ ነጻ የሕግ ማማከር አገልግሎት የሚሰጡ ማዕከላት ለደንበኞች የሕግ ምክር ሰጥተዋል፡፡ የአንዳንድ ክልሎች ሕግ አውጪ አካላት እንደ ሕግ ተማሪዎች እና መምህራን ያሉ በጎ ፈቃደኞች የለምንም ክፍያ በለጉዳዮችን ወክለው ፍርድ ቤት እንዲቆሙ የሚፈቅዱ ሕግጋትን አውጥተዋል፡፡

በዓመቱ ውስጥ በፀረ-ሽብርተኝነት ሕጉ መሰረት በሽብርተኝነት ተከስሰው የነበሩ የ31 ሰዎች ክሶች እልባት አግኝተዋል፡፡ እነዚህ ክሶች በ12 ጋዜጠኞች፣ የተቃዋሚ ፖለቲካ ፓርቲ አመራሮች፣ በአገር ውስጥ የሚንቀሳቀሱ የሰብዓዊ መብት ተሟጋቾች እንዲሁም የተባበሩት መንግስታት ድርጅት ሰራተኛ የሆነ አንድ ኢትዮጵያዊ ላይ የተመሰረቱ ነበሩ፡፡ ሁሉም ተከሳሾች ጥፋተኛ ተብለዋል፡፡ በውጭ አገራት የሚኖሩ 18 ሰዎች በሌሉበት የፍርድ ውሳኔ ተላልፎባቸዋል፡፡ በተጨማሪም መንግስት የፀረ ሽብር ሕጉን 28 ሙስሊሞች ላይ፤ እንዲሁም ከውጭ አገር ኤምባሲ በሕገ ወጥ መንገድ ገንዘብ በተቀበሉ አንድ ሙስሊም ላይ ክስ ለመመስረት ተጠቅሞበታል፡፡ ብዙ ዓለም አቀፍ የሰብዓዊ መብት ድርጅቶች እና የዲፕሎማቲክ ሚሽኖች የክሶቹን አካሄድ በተመለከተ ስጋታቸውን ገልጸዋል፡፡ በክሶቹ ላይ የቀረቡ ማስረጃዎችን የተመለከቱ ታዛቢዎች ማስረጃዎቹ ለትርጉም ክፍት የሆኑ አልያም ከሽብርተኝነት ይልቅ ፖለቲካዊ ይዘት ያላቸውን ድርጊቶች የሚያመለክቱ ሆነው አግኝተዋቸዋል፡፡ የሰብዓዊ መብት ድርጅቶች በተጨማሪም ሕጉ ለሽብርተኝነት የሚሰጠውን ሰፊ ትርጓሜ፣ እንዲሁም የሚጥላቸውን ከባድ ቅጣቶች፣ ስፋት ያለው የማስረጃ አቀራረብ ድንቡን እና ለፖሊስ እና ለፀጥታ ኃይሎች በጉዳዮች ላይ እንዳመኑበት የመወሰን ሥልጣን እንደሚሰጥ ታዝበዋል፡፡

በዋነኝነት በሙስሊሙ ማህበረሰብ የመብት ተሟጋቾች ላይ የተመሰረቱ ክሶችን ጨምሮ ከብሔራዊ ጸጥታ ጋር ከተዛመዱ አንዳንድ ጉዳዮች ጋር በተያያዘ የታሰሩ ሰዎች መጀመሪያ ላይ ጠበቃ የማግኘት መብታቸውን በባለስልጣናት ተነፍገው እንደነበረ ጠቅሰዋል፡፡ከተቃውሞ ጋር ግንኙነት ያላቸው 28 ሙስሊሞች እና ከውጭ አገር ኤምባሲ ሕገ ወጥ በሆነ መንገድ ገንዘብ የተቀበሉ የአንዲት ሙስሊም የክስ ሂደት ቀደም ሲል ለጋዜጠኞች እና ለዲፕሎማቶች ክፍት የነበረ ቢሆንም፤ ለቤተሰቦቻቸው እና ደጋፊዎቻቸው ሙሉ በሙሉ ክፍት አልነበረም፡፡ የአሸባሪዎቹ ድርጅቶች የአል ቃኢዳ እና አልሸባብ አባል በመሆን ግንቦት 11 ቀን ክስ የተመሰረተባቸው የ11 ግለሰቦች (በሌሉበት የተከሰሱ ስድስት ሰዎችን ጨምሮ) የክስ ሂደት ለህዝብ ክፍት አልተደረገም፡፡

በገጠር አካባቢዎች የሚኖሩ ብዙ ዜጎች በመደበኛ የዳኝነት ስርዓት የመዳኘት ዕድላቸው ውስን በመሆኑ ግጭቶችን የሚፈቱት በባህላዊ መንገድ ነው። በሕግ ረገድ በአንድ ጉዳይ ላይ የሚከራከሩ ወገኖች ጉዳያቸው በባህላዊ ወይም ሃይማኖታዊ ፍርድ ቤት መታየት ከመጀመሩ በፊት ተከራካሪዎቹ በእንዲህ ያለው ፍርድ ቤት ለመዳኘት የግድ መስማማት አለባቸው፤ ከተከራካሪ ወገኖች ማንኛቸውም በማንኛውም ጊዜ ለመደበኛው ፍርድ ቤት ይግባኝ ማለት ይችላል። የሸሪዓ (እስላማዊ) ፍርድ ቤቶች ሙስሊሞችን የሚመለከቱ ሃይማኖታዊ እና ቤተሰባዊ ጉዳዮችን ሊዳኙ ይችላሉ። የሸሪዓ ፍርድ ቤቶች ከመንግስት የተወሰነ የገንዘብ ድጋፍ የሚደረግላቸው ሲሆን በአብዛኛው ሙስሊሞች በሚኖሩባቸው በሶማሌ እና በአፋር ክልሎች ለሚነሱ በርካታ ጉዳዮች ዳኝነት ሰጥተዋል። በተጨማሪም እንደ የአገር ሽማግሌዎች ሸንጎ ያሉ ሌሎች ባሕላዊ የፍትሕ ሥርዓቶች፣ አሉ። አንዳንድ ሴቶች በልማዱ መሠረት ሴቶች በሽማግሌዎች ሸንጎ ላይ ስለማይሳተፉ እና በገጠር አካባቢም ጠንካራ የሆነ የጾታ መድልዎ በመኖሩ ምክንያት በባህላዊው የፍትሕ ሥርዓት ነጻ እና ፍትኃዊ ዳኝነት የማግኘት ዕድላቸው አነስተኛ ነው ሲሉ ቅሬታ አሰምተዋል።

## የፖለቲካ እስረኞች እና በቁጥጥር ሥር ያሉ ሰዎች

የፖለቲካ እሥረኞችን ብዛት በተመለከተ የሰብዓዊ መብት ድርጅቶች እና ዲፕሎማቲክ ሚሽኖች የሚሰጡት ግምት ይለያያል። በአገር በቀል እና ዓለም አቀፍ የበጎ አድራጎት ድርጅቶች ግምት መሠረት በዓመቱ መጨረሻ እስከ 400 የሚደርሱ የፖለቲካ እስረኞች ነበሩ። መንግሥት እሥረኞች በአለም ዓቀፍ የሰብዓዊ መብት ድርጅቶች እንዲጎበኙ አልፈቀደም።

በፀረ ሽብር ሕጉ አማካኝነት የተፈረደባቸው አስራሁለቱ ጋዜጠኞች፣የተቃዋሚ ፖለቲካ ድርጅት አባላት እና የመብት ተሟጋቾች ዓመቱን ያሳለፉት በማረሚያ ቤት ነው። በርካታ ዓለም አቀፍ የሰብዓዊ መብት ድርጅቶች እና የውጭ አገራት ዲፕሎማቲክ ሚሽኖች የክሶቹን አካሄድ በተመለከተ ያላቸውን ስጋት ገልጸዋል።

ጥር 10 ቀን ፍርድ ቤት በሽብርተኝነት በተከሰሱት በጋዜጠኞች ውብሸት ታዬ እና ርዕዮት ዓለሙ እንዲሁም በተቃዋሚ ፓርቲ አመራሩ ዘሪሁን ገብረእግዚአብሔር ታደሰ ላይ ፍርድ አስተላልፏል። ፍርድ ቤቱ በተጨማሪም በአቃቤ ሕግ የተቃዋሚ ፖለቲካ ፓርቲ አመራር እንደሆነች ተደርጎ የቀረባበትን ክስ ክዳ በተከራከረችው ሂሩት ክፍሌ ወልደየሱስ ላይ የፍርድ ውሳኔ አሳልፏል። ጋዜጠኛ እና ብሎገር ኤልያስ ክፍሌም በሌለበት በተመሳሳይ ክስ ተፈርዶበታል። ጥር 17 ቀን ውብሸት እና ርዕዮት እያንዳንዳቸው የ14 ዓመት እስራት ሲፈረድባቸው ሌሎቹ ሁለቱ ተከሳሾች የ17 እና የ19 ዓመት እስራት ተፈርዶባቸዋል። ርዕዮት ለጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ያቀረበች ሲሆን፤ ፍርድ ቤቱም ከተከሰሰችባቸው ሶስት ክሶች ሁለቱን ውድቅ በማድረግ ቅጣቱንም ወደ አምስት ዓመት ዝቅ

አድርጎላታል። በመጨረሻም ጠቅላይ ፍርድ ቤቱ በጉዳይዋ ላይ ውሳኔ ሲያሳልፍ መሰረታዊ የሕግ ስህተት ፈጽሟል በማለት ለሰበር ሰሚ ችሎት አመልክታ ነበር። ሌሎቹ ተከሳሾች ግን ይግባኝ ለማለት አልመረጡም።

የፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ሰኔ 20 ቀን በጋዜጠኛ እና ብሎገር እስክንድር ነጋ፣ የተቃዋሚ ፓርቲዎች ስብስብ የሆነው መድረክ ምክትል ሊቀመንበር በአንዱአለም አራጌ እና በአንድነት ለዴሞክራሲና ለፍትህ ፓርቲ አመራር አባል ናትናኤል መኮንን ላይ በአገር መክዳት እና በሽብርተኝነት ወንጀል የጥፋተኝነት ውሳኔ አሰተላልፏል። ሐምሌ 6 ቀን እስክንድር እና ናትናኤል እያንዳንዳቸው በ18 ዓመት እስራት ሲቀጡ፣አንዱአለም የዕድሜ ልክ እስራት ተፈርዶበታል።እስክንድር እና አንዱአለም የተላለፈባቸውን የፍርድ ውሳኔ በመቃወም ለፌዴራሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ያሉ ሲሆን፣ ጉዳዩ በዓመቱ መጨረሻም መታየት እንደቀጠለ ነበር። በመስከረም ወር መንግስት የእስክንድር እና የአንዱአለም ንብረቶች ለተከሰሱባቸውና ቅጣት ለተቀበሉባቸው ወንጀሎች መፈጸሚያነት መዋላቸውን ለማጣራት በመፈለጉ የንብረት የታገድልኝ ጥያቄ ለፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ማቅረቡን አስታውቆ ነበር። ንብረቶቹን የተመለከቱ የክስ ሂደቶችም በዓመቱ መጨረሻም እንደቀጠሉ ናቸው።

የኦሮሞ ብሔር ተወላጅ የሆኑት ሁለቱ ታዋቂ የተቃዋሚ ፖለቲካ ፓርቲ አመራሮች በቀለ ገርባ እና ኦልባና ሌሊሳ እንዲሁም ሌሎች ሰባት ግለሰቦች በወንጀል ሕጉ መሰረት መንግስትን ለመጣል በማሴር እና አመጽ በመቀስቀስ የወንጀል ፍርድ ተላልፎባቸዋል። በቀለ በስምንት ዓመት እስራት እንዲቀጣ፣ ኦልባና ደግሞ በ13 ዓመት እስራት እንዲቀጣ ፍርድ ቤት ወስኗል። በ2003 ዓ.ም. በወንጀል ሕጉ በአገሪቱ የፖለቲካ እና የግዛት አንድነት ላይ ጥቃት በመፈጸም ክስ የተመሰረተባቸው የኦሮሞ ተቃዋሚ ፖለቲካ ፓርቲዎች አባላት የሆኑ 69 ሰዎች ክስ በዓመቱ መጨረሻም እንደቀጠለ ነበር።

### የፍትሐ-ብሔር የዳኝነት ሥነ ሥርዓት እና የመፍትሔ እርምጃዎች

ሕጉ ዜጎች የሰብአዊ መብት ጥሰቶች ሲፈፀሙባቸው በፍትሐብሔር ፍርድ ቤቶች አቤቱታ የማቅረብ መብት ይሰጣል፣ ሆኖም በዓመቱ ውስጥ እንዲህ ያሉ ጉዳዮች አልቀረቡም።

### ረ. በግል ነጻነት፣ በቤተሰብ፣ በመኖሪያ ቤት ወይም በመልዕክት ልውውጥ ላይ የዘፈቀደ ጣልቃ-ገብነት

ሕጉ የመንግስት አካላት የግለሰብ ንብረትን ለመፈተሽ የፍርድ ቤት ማዘዣ ይዘው እንዲቀርቡ ያዝዛል፣ ነገር ግን በተግባር ፖሊሶች ብዙውን ጊዜ ሕጉን አያከብሩም፣ ፍርድ ቤቶችም ያለ ፍተሻ ትዕዛዝ የተገኘ ማስረጃን ተቀባይነት መንፈጋቸውን የሚያሳይ ሰነድም አልነበረም። የተቃዋሚ ፖለቲካ ፓርቲ መሪዎች

የስልክ ጠለፋ እና ሌሎች በኤሌክትሮኒክ መሳሪያዎች የታገዙ ስለላዎች እንደሚካሄዱ ጥርጣሬ እንዳላቸው ሪፖርት አድርገዋል፡፡

መንግስት የአንዳንድ ግለሰቦችን እንቅስቃሴ ተከታትለው ሪፖርት እንዲያደርጉለት ገንዘብ የሚከፈላቸው መረጃ አቀባዮችን የማሰማራት ስልትን በስፋት ተጠቅሟል የሚሉ ሪፖርቶች አሉ፡፡ በዓመቱ የገዢው ፓርቲ ካድሬዎች እና የሚሊሽያ አባላት፣ ማስፈራራትን ዓላማ አድርገው ሳይፈቀድላቸው መኖሪያ ቤታቸው ድረስ ዘልቀው መግባታቸውን የተቃዋሚ ፓርቲ አባላት ሪፖርት አድርገዋል፡፡

የፀጥታ ኃይሎች በመንግሥት ለጥያቄ የሚፈለጉ ሰዎችን ቤተሰቦች በቁጥጥር ስር ማዋል ቀጥለው ነበር፡፡ ከገዥው ፓርቲ ጋር ግንኙነት የሌላቸው ሥራ አጥ ወጣቶች ሥራ ለማግኘት አስፈላጊ የሆነውን ‹‹የድጋፍ ደብዳቤ›› ከቀበሌያቸው ለመቀበል አልፎ አልፎ እክል ገጥሟቸው እንደነበር ሪፖርቶች ቀርበዋል፡፡

መንግስት በዜጎች የቤተሰብ መብቶች ውስጥ ጣልቃ ገብቷል፡፡ ለዓለም አቀፍ ጉዲፈቻ ሁኔታዎችን ለማመቻቸት ሲባል የተፈጸሙ የሕክምና ስራ ጥሰቶች ተመዝግበዋል፡፡ይህም ብቃት በሌላቸው የሕክምና ባለሙያዎች አማካኝነት አራስ እናቶች የአእምሮ ሕመም እንዳለባቸው እና ልጆቻቸውን እንዲሰጡ ተገደዋል፡፡

የፌደራል መንግሥት እና የክልል መንግሥታት በአፋር፣ በቤኒሻንጉል ጉሙዝ ፣ በጋምቤላ፣ በደ/ብ/ብ/ሕ/ክ እና በሶማሊ ክልሎች ‹‹የመንደር ምሥረታ›› እቅዶችን በሥራ ላይ ማዋል ቀጥለዋል፡፡ እቅዶቹ በተበታተነ አኳኋን የሚኖሩ የገጠር ሕዝቦችን ለተደጋጋሚ ድርቅ ከተጋለጡ ደረቅ አልያም ከፊል-ደረቅ አካባቢዎች አንስቶ በክልል መንግሥታት ወደተዘጋጁ ቦታዎች በአንድ አካባቢ ማስፈርን ያካትታሉ፡፡ የመንደር ምሥረታው ዓላማዎችም (የጤና አገልግሎት፣ የትምህርት እና የንፁህ መጠጥ ውሃ አቅርቦትን የመሳሰሉ) የመንግሥት አገልግሎቶችን አቅርቦት ማሻሻል፣ ማኅበረሰቦችን ከተፈጥሯዊ አደጋዎች እና ጥቃቶች መከላከል፣ እንዲሁም አካባቢን ክፉኛ የሚጎዱ አሉታዊ የአስተራረስ ልማዶችን መለወጥ ናቸው ተብለው ተገልፀዋል፡፡ አንዳንድ ታዛቢዎች ግን፣ መርኃ-ግብሩ ለንግድ እርሻ የሚውል መጠነ-ሰፊ መሬት በሊዝ ማከራየት የሚቻልበትን ሁኔታ ለማመቻቸት የታለመ ነው ሲሉ ይገልጻሉ፤ ሆኖም መንግሥት ይህን ያስተባብላል፡፡ መንግሥት የመንደር ምሥረታ መርኃ-ግብሩ ሙሉ በሙሉ በፈቃደኝነት ላይ ተመሥርቶ እንደሚፈፀም ይገልጻል፡፡

በአለምዓቀፍ ለጋሾች የተደረጉ ግምገማዎችም በዚህ መርኃ ግብር የሰብዓዊ መብት ጥሰት ስለመፈጸሙ የሚገልጽ ስልታዊ ማስረጃ ማግኘት አልቻሉም፡፡ መርሃ ግብሩን ለመተግበር በነበረው ችኮላ የተነሳ ለማኅበረሰቦች ቃል በተገባላቸው መሰረት በአዲሱ አካባቢ በቂ መሠረተ ልማቶች ማሟላት ያለመቻል

የመሳሰሉ ችግሮች ታይተዋል፡፡ ማህበረሰቦች እና ቤተሰቦች የምግብ እርዳታ፣ መሠረታዊ አገልግሎቶች እና መሬት እንደሚያገኙ ባለሥልጣናት በሰጧቸው ማረጋገጫ ላይ ተመሥርተው ለመሥፈር የተስማሙ ቢመስልም  በአንዳንድ ሁኔታዎች ግን በአዲሱ ስፍራ በቂ መሰረታዊ አገልግሎቶች እና መጠለያ ሳይዘጋጅላቸው ከለመዱት ቀያቸው የተንቀሳቀሱ ማህበረሰቦች ነበሩ፡፡ ለምሳሌ በነሐሴ ወር መጀመሪያ አካባቢ ደ/ብ/ብ/ሕ/ክ፣ ደቡብ ኦሞ በተደረገ የመስክ ጉብኝት (የማስፈር) ሂደቱ በፈቃደኝነት ላይ የተመሰረተ ቢሆንም ሰዎች በቦታው ሲደርሱ እንደ ውሃ አቅርቦት፣ ትምሕርት፣ እና ጤና ያሉ መሰረተ ልማቶች ቃል እንደተገባው ተሟልተው አልተገኙም፡፡ በጥቅምት ወር በተመሳሳይ ቦታ በተደረገ ጉብኝት የውሃ መሳቢያ ሞተር ተከላ፣ አዲስ የተገነባ ትምሕርት ቤት፣እንዲሁም በተባበሩት መንግስታት የሕጻናት መርጃ ድርጅት (ዩኒሴፍ) ዕቃዎች የተሟሉለት የጤና አገልግሎት መስጫ ድንኳንን ጨምሮ የተሻለ ሁኔታ ለማየት ተችሏል፡፡  በጥር ወር የወጣ የሒዩማን ራይትስ ዎች ሪፖርት በ2003 የተሰበሰበ መረጃን መሰረት በማድረግ ሂደቱን ‹‹በፈቃደኝነት ላይ ያልተመሰረተ›› ሲል ገልፆታል፡፡ ሪፖርቱ ሁኔታውን በመጀመርያ ለመሄድ ፍላጎት እንደሌላቸው ከገለፁ ማኅበረሰቦች ጋር በተደረጉ ስብሰባዎች ላይ የፀጥታ ኃይሎች እና የአካባቢ ሚሊሽያዎች ይገኙ እንደነበረና የኋላ ኋላም ነዋሪዎቹ ወደ አዲሱ አካባቢ ሄደው የሳር ጎጆዎቻቸውን ሲቀልሱ [የፀጥታ ኃይሎቹ እና ሚሊሽያዎቹ] አብረዋቸው በመሄድ የግንባታ እንቅስቃሴውን ይከታተሉ ነበር ሲል ገልጿል፡፡ ሪፖርቱ ፣ የፀጥታ ኃይሎች ማኅበረሰባቸውን በመንደር ለማስፈር የተነደፈውን ዕቅድ የተቃወሙ ሰዎችን ደብድበዋል፤ አንዳንዶም በድብደባው ምክንያት እንደሞቱ፣ እንደሚያስፈራሩ፣ ክስ ሳይመሰርቱ በቁጥጥር ስር እንደሚያውሉ ገልጿል፡፡ በተጨማሪ የሒውማን ራይትስ ዎች ሪፖርት እንደሚገልጸው መንግስት ሰፋፊ የእርሻ መሬቶችን ለኢንቨስትመንት ለማዘጋጀት በማቀድ በደቡብ ኦሞ የሚገኙ ግለሰቦችን አስፈራርቷል፣አጉላልቷል፣እንዲሁም በዘፈቀደ አስሯል፡፡ የልማት አጋሮች ባደረጓቸው ጉብኝቶች ይህን የሚያረጋግጥ ማስረጃ አላገኙም፡፡

**ክፍል 2፡ የሲቪል መብቶች እና ነጻነቶች ከበሬታ**

**ሀ. የመናገር እና የፕሬስ ነፃነት**

**የመናገር እና የፕሬስ ነፃነት ያለበት ሁኔታ**

የመናገር እና የፕሬስ ነጻነት በሕገ-መንግሥቱ እና በሕግ የተደነገገ ቢሆንም፣ ባለስልጣናት ጋዜጠኞችን እና መንግስትን ይተቻሉ ተብለው የሚታሰቡ ሰዎችን በቁጥጥር ስር አውለዋል፣አስረዋል ብሎም አስፈርደውባቸዋል፡፡

**<u>የመናገር ነፃነት</u>**፡ ባለሥልጣናት ሰዎች በመንግሥት ላይ ትችት በመሰንዘራቸው በቁጥጥር ሥር አውለው አስፈራርተዋቸዋል፡፡ መንግስት በማስፈራራት፣ ጋዜጠኞችን እና ተቃዋሚ ፖለቲከኞችን በማሰር እንዲሁም የተቃዋሚ ፖለቲካ ቡድኖችን እንቅስቃሴ በመከታተልና ጣልቃ በመግባት የሚሰነዘርበትን ትችት ያፍናል፡፡ አንዳንድ ነዋሪዎች በጸጥታ ኃይሎች (የመብት) ጥሰት የተፈጸመበት ማንኛውም ሰው ጉዳዩን ሪፖርት ቢያደርግ የቂም በቀል እርምጃ እንደሚወስዱ ማስፈራራታቸውን ቀጥለዋል፡፡

በሐምሌ ወር ጀማል ከድር የተባለ ግለሰብ በተንቀሳቃሽ ስልኩ አማካኝነት ‹‹አላሁ አክበር፤ አስራሰባት ጊዜ ድምጻችን ይሰማ፤ በማረሚያ ቤት ያሉ እስረኞች ይፈቱ›› ሲል በላከው አጭር መልዕክት የተነሳ ‹‹ ለብጥብጥ በማነሳሳት፣ ጥላቻ በመቀስቀስ እና የፖለቲካ፣ የዘር እና የሐይማኖት ግጭት በመፍጠር›› ተከስሷል፡፡ በተጨማሪም ፖሊስ ሙስሊሞች አዲስ አበባ ወደሚገኘው ታላቁ አንዋር መስጊድ እንዳይገቡ ከልክሏል የሚል መልዕክት በመላክ እና ተጨማሪ ተቃውሞዎች እንዲካሄዱ እንዲሁም እስረኞች እስካልተፈቱ ድረስ በኢትዮጵያ የእስልምና ጉዳዮች ጠቅላይ ምክር ቤት አባላት ምርጫ ላይ እንዳሳተፉ ጥሪ የማድረግ ክስ ተመስርቶበት ነበር፡፡ መስከረም 3 ቀን ፍርድ ቤት የጥፋተኝነት ውሳኔ ባሳለፈበት ወቅት ዳኛው ክሱን ‹‹ በተንቀሳቃሽ ስልኩ አሉባልታ በመንዛት›› ሲሉ ከገለጹ በኋላ የአንድ ዓመት እስር ፈርደውበታል፡፡

በጥቅምት ወር በኦሮሚያ ክልልለገጣፎ አካባቢ ስላለው የመሬት መቀራመት ጉዳይ ለሬዲዮ ቃለመጠይቅ የሰጡ ሰባት ግለሰቦች በፖሊስ ታስረው ነበር፡፡ ግለሰቦቹ ያለበቂ የካሳ ክፍያ ከመሬታቸው እንደተፈናቀሉ ገልጸዋል፡፡ ቆይቶም ፖሊስ ከእስር ፈቷቸዋል፡፡

**<u>የፕሬስ ነፃነት</u>**፡- ኢትዮ-ቻናል፣ነጋድራስ፣ፍትህ እና ሁለት የሙስሊም ጋዜጦች በመንግስት ጫና ምክንያት ተዘግተዋል፡፡ በአዲስ አበባ የቀሪዎቹ 15 ጋዜጦች ጠቅላላ ስርጭት በ2003 ዓ.ም. ከነበረበት 150,000 ወደ 100,000 ቀንሷል፡፡ በመንግሥት ይዞታ ሥር ካሉት ዕለታዊ የአማርኛ እና የእንግሊዝኛ ጋዜጦች በስተቀር አብዛኞቹ ጋዜጦች በየሳምንቱ ወይም በሳምንት ሁለት ጊዜ የሚታተሙ ነበሩ፡፡

መንግስት ራዲዮን ጨምሮ ለአብዛኛው ሕዝብ ዋነኛ የዜና ምንጭ የሆነውንና አገር አቀፍ ሥርጭት ያለውን ብቸኛ የቴሌቪዥን ጣብያ ተቆጣጥሯል፡፡ በዋና ከተማይቱ ሦስት የግል የኤፍ.ኤም. ራዲዮ ጣብያዎች የሚገኙ ሲሆን፤ በክልሎች 13 የማኅበረሰብ ራዲዮ ጣቢያዎች ፕሮግራሞቻቸውን ያሰራጫሉ፡፡ በመንግስት ይዞታ ስር ያለው የኢትዮጵያ ሬዲዮ በአገሪቱ ሰፊ የስርጭት ሽፋን ያለው ሲሆን፤ ተከታዩ ሬዲዮ ፋናም ከገዢው ፓርቲ ጋር ግንኙነት አለው፡፡

በመንግሥት ቁጥጥር ስር ያሉ መገናኛ ብዙኃን በአመዛኙ የመንግሥትን እና የገዢውን ኢሕአዴግ ዕይታ [አቋም] አንፀባርቀዋል፡፡ መንግሥት በየጊዜው ከውጭ አገራት የሚተላለፉ ስርጭቶችን አፍኗል፤ይህ ከጠቅላይ ሚኒስትር መለስ ዜናዊ ሕልፈት በኋላም ቀጥሏል፡፡ የብሮድካስቲንግ ሕጉ የፖለቲካ እና የሃይማኖት ድርጅቶችን እንዲሁም የውጭ አገር ዜጎችን የኤሌክትሮኒክ መገናኛ ብዙኃን ባለቤት ከመሆን ይከለክላል፡፡ የኢንቨስትመንት ሕጉም እንዲሁ የውጭ አገር ዜጎች የብሮድካስት ጣቢያ ባለቤት እንዳይሆኑ ክልከላ ያደርጋል፡፡

<u>ሁከት እና ወከባ</u>፡ መንግሥት ጋዜጠኞችን ማሠር፣ ማዋከብ እና ለፍርድ ማቅረቡን ቀጥሏል፡፡ በርካታ የተባበሩት መንግስታት ራፖርተሮች እና የሰብዓዊ መብት ኮሚሽነሮች መንግስት በጋዜጠኞች እና ተቃዋሚ ፖለቲከኞች ላይ የፀረ- ሽብር ሕጉን በመጠቀሙ ያላቸውን ስጋት ገልጸዋል፡፡

ነሐሴ 3 ቀን ፍትህ ሚኒስቴር በፍትህ ጋዜጣ ዋና አዘጋጅ ተመስገን ደሳለኝ ላይ ሶስት ክሶችን መስርቷል፡፡ ክሶቹ ከታሕሳስ እስከ ነሐሴ 2003 በታተሙ ጽሁፎች አማካኝነት የአገሪቱን ወጣቶች ለአመጽ ማነሳሳት እና መገፋፋት፣ የመንግስትን ስም ማጥፋት እና የሀሰት ዜናዎችን በማሰራጨት ሕዝብን ማወክን ያካትታሉ፡፡ ተመስገን ነሐሴ 17 ቀን በቁጥጥር ስር ውሎ፤ነሐሴ 22 ቀን ክሱ በመነሳቱ በዚሁ ዕለት ከእስር ተፈቷል፡፡ መንግስት በተመስገን ላይ የመሰረተውን ክስ በታህሳስ 2 ቀን በድጋሚ ያንቃሳቀሰ ሲሆን፤በዓመቱ መጨረሻም ጉዳዩ መታየት እንደቀጠለ ነበር፡፡

ሐምሌ 13 ቀን ባለስልጣናት የሙስሊሞች ጉዳይ (መጽሔት) አዘጋጅ ዩሱፍ ጌታቸውን እና አምደኛ አህመዲን ጀበልን በቁጥጥር ስር አውለዋል፡፡ አህመዲን ጀበል የማሰቃየት ድርጊት እንደተፈጸመበት ተነግሯል፡፡ በዓመቱ መጨረሻም ከሌሎች 27 የሙስለሞች (መብት) ተሟጋቾች ጋር በሽብር ተግባር ተከሰው በእስር ላይ ይገኛሉ፡፡

በዚሁ ሐምሌ ወር ሁለት የሙስሊሞች ጉዳይ (መጽሔት) አዘጋጆች ማለትም አክመል ነጋሽ እና ይስሐቅ እሸቱ እንዳይታሰሩ በመፍራት ከአገር ሸሽተዋል፡፡ ከነዚህ እስሮች እና ስደቶች በኋላ (የመጽሔቷ) ሕትመት ቆሟል፡፡

በ2003ዓ.ም. በቁጥጥር ስር በዋሉት ጋዜጠኖች ማለትም ውብሸት ታዬ፣ ርዕዮት ዓለሙ እና እስክንድር ነጋ እንዲሁም በሌሉበት በተከሰሱ ስድስት ጋዜጠኞች/ ብሎገሮች ላይ በፀረ ሽብር ሕጉ የተለያዩ አንቀጾች በተመሰረተባቸው ክስ ፍርድ ቤት ጥፋተኛ ብሏቸዋል፡፡ (ክፍል 1.ሰ ን ይመልከቱ)

<u>ቅድመ-ምርመራ (ሳንሱር) ወይም በይዘት ላይ የተጣሉ ገደቦች</u>፡ መንግሥት በጋዜጠኞች ላይ የሚያደርሰው ወከባ ጋዜጠኞቹ በአንዳንድ አወዛጋቢ ጉዳዮች ላይ ለመዘገብ ፍራቻ እንዲያድርባቸው አድርጓል፡፡ ጥቂት የማይባሉ የግል ጋዜጦች በመንግሥት መደበና ያልሆነ የኤዲቶሪያል ቁጥጥር

ይደረግባቸው እንደነበር አመልክተዋል፤ ለዚህም [ከመንግሥት ባለሥልጣናት የተዘጋጁ] ጽሑፎችን አትመው እንዲያወጡ የሚቀርብላቸውን ጥያቄ እና ታትመው የወጡ መንግሥትን የሚተቹ ጽሑፎችን አስመልክቶ ከመንግሥት ባለሥልጣናት የሚደርሷቸውን የስልክ ጥሪዎች ጠቅሰዋል። የግሉ ዘርፍ እና የመንግሥት ጋዜጠኞች በየዕለት ተዕለት ሥራቸው ራሳቸውን ሳንሱር አድርገዋል።

በሚያዚያ ወር በመንግስት ይዞታ ስር ያለው እና በአገሪቱ ከሚታተሙ ጋዜጦች 90 በመቶ ያህሉን የሚያትመው ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ድርጅት ለግል አሳታሚ ደንበኞቹ አዲስ የሕትመት ውል በስራ ላይ አውሏል። ውሉ ‹‹ሕገ ወጥ›› የሚባል ይዘት ያለበትን ጋዜጣ ለማተም ፈቃደኛ ያለመሆን መብትን ለማተሚያ ቤቱ ይሰጣል። በግል ይዞታ ስር ያሉ ጋዜጦች አዘጋጆች ውሉ ቅድመ ምርመራ ነው፤ ሕገመንግስታዊውን የፕሬስ ነጻነት መብት ይጻረራል በማለት ውሉን አልፈረሙም። ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ድርጅት አዲሱን ውል ያልፈረሙ የሕትመት ውጤቶችን ማተም አቁሟል።

ሐምሌ 13 ቀን ፍትህ ሚኒስቴር በዚያ ሳምንት ታትሞ የነበረው የፍትህ ጋዜጣ እንዳይሰራጭ በፍርድ ቤት ትዕዛዝ አሳግዷል። እገዳው ከጋዜጣው ይዘቶች የቀድሞውን ጠቅላይ ሚኒስትር ጤና እና በአንዳንድ የሙስሊም ማህበረሰብ አባላት የተደረጉ ተቃውሞዎች መቀጠላቸውን የሚመለከቱ ዘገባዎች የተካተቱበት ከመሆኑ ጋር እንደሚያያዝ ሪፖርቶች አመልክተዋል። ፍትህ ሚኒስቴር ቀጣይ መመሪያ ያልሰጠ ቢሆንም ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ድርጅት ፍትህ ጋዜጣን ለማተም ፈቃደኛ ሳይሆን ቀርቷል።

ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ድርጅት ከታዋቂ ተቃዋሚ የፖለቲካ ፓርቲዎች መካከል የአንድነት ለዴሞክራሲ እና ለፍትህ ፓርቲ ልሳን የሆነውን የፍኖተ ነጻነት ጋዜጣ የነሐሴ 25 እትም ለማተም ፈቃደኛ ሳሆን ቀርቷል። ጋዜጣው በቀደመው እትሙ ስለጠቅላይ ሚኒስትሩ ሞት ያወጣው ዜና ከሕዝቡ በኩል ቅሬታ ያስነሳ መሆኑ እንደምክንያት ቀርቧል። በመስከረም ወር ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ድርጅት ማተሚ ማሽኑ ስራ በዝቶበታል በሚል ምክንያት የአንድነት ልሳን የሆነውን ጋዜጣ እንደማያትም ገልጧል። ጋዜጣው ከግል ማተሚያ ቤት ጋር በተደረሰ ስምምነት በጥቅምት ወር ሕትመት የቀጠለ ቢሆንም በሕዳር ወር ሕትመቱን ለማቆም ተገዷል።

<u>የስም ማጥፋት (የመልካም ስም ማጉደፍ) ሕግጋት/ብሔራዊ ደኅንነት</u>፡ መንግሥት የፀረ-ሽብር ሕጉን ትችትን ለማፈን ተጠቅሞበታል። ጋዜጠኞች በሰኔ ወር ፓርላማው ሽብርተኛ ድርጅቶች ብሎ በፈረጃቸው አምስት ቡድኖች (ግንቦት 7፣ ኦብነግ፣ ኦነግ፣ አል-ቃዒዳ እና አል-ሸባብ) ዙርያ መዘገብን ፈርተዋል፤ ለዚህም የጠቀሱት ምክንያት በእነዚህ ቡድኖች ዙርያ መዘገብ በሕጉ መሠረት የሚያስቀጣ ይሁን አይሁን ግልጽ አለመሆኑን ነው። የአገር ውስጥ እና የውጭ አገር የዜና ወኪሎችን ጨምሮ በርካታ ጋዜጠኞች ራስን ሳንሱር የማድረግ ዝንባሌ እያደገ መምጣቱን ጠቁመዋል።

በመስከረም ወር መንግስት ዮሐን ፔርሰን ማርቲን ሺብዬ ለተባሉ ስዊድናውያን ጋዜጠኞች ምህረት አድርጓል፡፡ በታሕሳስ 2003 ዓ.ም. ፍርድ ቤት ለሽብርተኛ ቡድን ድጋፍ በማድረግ እና በሕገወጥ መንገድ ወደ አገር በመግባት ወንጀል ፈርዶባቸው ነበር፡፡

በዓመቱ መንግስት ትችትን ለማፈን ስም ማጥፋትን የሚመለከቱ ሕግጋትን ተጠቅሟል፡፡

**የኢንተርኔት ነፃነት**

መንግሥት የኢንተርኔት ተደራሽነትን ገድቧል፤ የዜና ድረ-ገፆችን፣ ብሎጎችን፣ የተቃዋሚ ድረ-ገፆችን እንዲሁም በፓርላማ ሽብርተኛ ተብለው የተፈረጁ የአገር ውስጥ ተቃዋሚ ቡድኖች (ግንቦት 7፣ ኦነግ፣ እና ኦብነግ) ድረ-ገፆችን ጨምሮ በርካታ ድረ-ገጾችን (ኢትዮጵያ ውስጥ) እንዳይከፈቱ አግዷል፡፡ መንግስት እንደ ዋሺንግተን ፖስት፣ዘ ኢኮኖሚስት እና አል ጀዚራ ያሉ የዜና ገጾችን ለአጭር ጊዜ እንዳታዩ ያገደ ሲሆን፤ በአገሪቱ ባለው የሰብዓዊ መብቶች ሁኔታ ላይ ያተኮሩ የውጭ መንግስታት ሪፖርቶችን የያዙ ገጾችም እንዲሁ ለአጭር ጊዜ ታግደዋል፡፡ በውጭ አገር ነዋሪ የሆኑ ተቃዋሚዎች የሚያስተዳድሯቸው እንደ አዲስ ነገር፣ ናዝሬት፣ ኢትዮጵያን ሪቪው፣ ሳይበር ኢትዮጵያ፣ ቋጠሮ የአማርኛ መጽሔት፣ ትንሣዔ ኢትዮጵያ፣ እና የኢትዮጵያ ሚዲያ ፎረምን የመሳሰሉ በርካታ የዜና ብሎጎች እና ድረ ገጾች (ኢትዮጵያ ውስጥ) ተደራሽ አልነበሩም፡፡ ምንም እንኳ ተጠቃሚዎች በአማራጭ ድረ-ገፆች (ሰርቨሮች) መክፈት ቢችሉም፣ የውጭ አገር የዜና ድረ-ገጽ በአገር ውስጥ የሚከፈተው አልፎ አልፎ ብቻ ነበር፡፡ ባለስልጣናት የኢንተርኔት ተጠቃሚዎች ከመንግስት ቁጥጥር ውጭ በመሆን አገልግሎቱን እንዲያገኙ የሚያስችለውን የቨርቹዋል ፕራይቬት ኔትዎርክ (ቪ.ፒ.ኤን) አቅራቢዎችን የማገድ ርምጃዎችን ወስደዋል፡፡ በመንግስት መረጃ መሰረት 4 በመቶ የሚሆነው ሕዝብ የኢንተርኔት አገልግሎት ተጠቃሚ ነበር፡፡

**አካዳሚያዊ ነፃነትና ባህላዊ ሁነቶች**

መንግሥት ሥርዓተ-ትምህርትን፣ የመምህራን ምደባዎችን እና የተማሪዎች የትምህርት መስክ ውሳኔዎችን ጨምሮ የአካዳሚ ነጻነትን ገድቧል፡፡ በዩኒቨርሲቲ እና በከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤቶች የመናገር፣ ሐሳብን የመግለጽ እና የመሰብሰብ ነፃነቶች በተደጋጋሚ ተገድበው ነበር፡፡

ገዢው ፓርቲ ትምህርት ሚኒስቴርን በመጠቀም በድህረ ምረቃ መርሃግብር ምደባ ወቅት ለፓርቲው ታማኝ ለሆኑ ተማሪዎች ቅድሚያ መስጠት እንደቀጠለ ምንጮች ገልጸዋል፡፡ ለመጀመሪያ ዲግሪ በሚማሩ ተማሪዎች ዘንድ የፓርቲ አባል መሆን የተለመደ ባይሆንም፤ በየትኛውም የትምህርት ዘርፍ

ከተመረቁ በኋላ ስራ ለመቀጠር የፓርቲው አባል ለሆኑ ተማሪዎች ቅድሚያ እንደሚሰጥ አንዳንድ የዩንቨርስቲ መምህራን ተናግረዋል፡፡

መንግሥት የአካዳሚ ነፃነትን በሌሎችም መንገዶች ገድቧል፡፡ በየትኛውም ደረጃ ላይ የሚገኙ መምህራን ከተፈቀደው የትምህርት ዕቅድ ውጪ እንዲያስተምሩ አልተፈቀደላቸውም፡፡ ምንጮች የኢህአዴግ አባላት ያልሆኑ መምህራን ወደማይፈለጉ የሥራ መደቦች የሚዘዋወሩበት ዕድል ሰፊ እንደሆነ እና በደረጃ ዕድገት ወቅት እንደማይካተቱ ጠቁመዋል፡፡ የኢሕአዴግ አባል ያልሆኑ መምህራን ያለፕሮግራም የሚጠሩ ስብሰባዎችን አልተካፈላችሁም በሚል ከስራቸው እንደሚባረሩ የሚገልጹ አንዳንድ ሪፖርቶች ቀርበዋል፡፡ የመምህራን የሰው ኃይል ምደባ ግልጽነት የጎደለው ከመሆኑም ሌላ የድርጅት አባልነትን፣ ብሔርን ወይም ሃይማኖትን መሠረት ያደረጉ መድልዎች እንደሚፈፀሙ በመግለጽ የአካዳሚ ማኅበረሰቡ አባላት ቅሬታቸውን አሰምተዋል፡፡

ብዛት ያላቸው ታማኝ ምንጮች መምህራን፣ የአሥረኛ ክፍልና ከዚያም በላይ የሆኑ ተማሪዎች ስለ አብዮታዊ ዴሞክራሲ ጽንሰ-ሐሳብ እና ስለ ኢሕአዴግ የፓርቲ ርዕዮተ-ዓለም ሥልጠና መውሰድ ይጠበቅባቸው ነበር፡፡

ትምህርት ሚኒስቴር በ2002 ዓ.ም. ባወጣው የግል ዩኒቨርስቲዎችን በሕግ እና በመምህራን ትምሕርት ዘርፍ የዲግሪ መርሀ ግብር እንዳይሰጡ የሚከለክለው መመሪያ ላይ የተደረገ ለውጥ የለም፡፡ መመሪያው የግል ዩኒቨርሲቲዎች ሥርዓተ ትምህርታቸውን የሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱ ቀደም ሲል ካወጣው የተፈጥሮ ሣይንስ እና የማኅበራዊ ሣይንስ የአካዳሚ መርኃ-ግብሮች የ70ለ30 ድልድል ፖሊሲ ጋር እንዲያጣጥሙ ይጠይቃል፡፡ በዚህ የተነሳ ማህበራዊ ሳይንስ የሚያጠኑ ተማሪዎች ቁጥር እየቀነሰ መጥቷል፡፡ የግል ዩኒቨርሲቲዎች ሥርዓተ-ትምህርት ደግሞ እጅግ በአመዛኙ በማኅበራዊ ሳይንስ ላይ ያተኮረ ነበር፡፡ የትምህርት ሚኒስቴር ባለሥልጣናት መመሪያው ሲወጣ የትምህርት ጥራት ደረጃን ለመጠበቅ ያለውን አስፈላጊነት በምክንያትነት ጠቅሰው ነበር፡፡

**ለ. ሠላማዊ የመሰብሰብና የመደራጀት ነፃነት**

**የመሰብሰብ ነፃነት**

ምንም እንኳ ሕገ-መንግሥቱ የመሰብሰብ ነፃነትን ቢፈቅድም፣ መንግሥት ይህንን ነፃነት ገድቧል፡፡ በዓመቱ ውስጥ በበርካታ አጋጣሚዎች ባለሥልጣናት ፈቃድ ሳያገኙ ሰላማዊ ሰልፍ ወጥተዋል የተባሉ ሰልፈኞችን አቁስለዋል በቁጥጥር ሥርም አውለዋል፡፡ የጸጥታ ኃይሎች በሰላማዊ ዜጎች ላይ ለሞት የሚያደርስ የኃይል እርምጃ ወስደዋል፡፡

ታላላቅ ሕዝባዊ ስብሰባዎችን ወይም ሠላማዊ ሰልፎችን ማካሄድ ቢያስፈልግ አስተባባሪዎች ሁኔታውን ከ48 ሰዓታት በፊት ለመንግሥት ማሳወቅና ፈቃድ ማግኘት ይጠበቅባቸዋል። የአካባቢ መስተዳድር ባለሥልጣናት ሁሉም ማለት ይቻላል የኢሕአዴግ ወገንተኛ ሲኾኑ፣ በየከተማው የሚገኙ የመዘጋጃ ቤት አዳራሾችን ይቆጣጠራሉ። ተቃዋሚ ፓርቲዎች ለሕጋዊ የፖለቲካ ስብሰባ ይጠቀሙባቸው ዘንድ አዳራሾችን በሚጠይቁበት ጊዜ እነዚህ የአካባቢ ባለሥልጣናት እንደሚከለክሏቸው አልያም የስብሰባውን መርኃ-ግብር እንደሚያስተጓጉሉባቸው ጠቅሰው በርካታ ስሞታዎችን አቅርበዋል። የሆቴሎች እና የትልልቅ አዳራሾች ባለቤቶች ለምሳሌ የሆቴሉ መሰብሰቢያ ክፍል አገልግሎት የሚሰጠው ለሰርግ ብቻ ነው የሚሉ እና በግልጽ የማይታወቁ ውስጣዊ ደንቦችን በመጥቀስ የፖለቲካ ፓርቲዎች አዳራሾቻቸውን እንዳይጠቀሙ ስለመከልከላቸው በርካታ የታመኑ ሪፖርቶች ቀርበዋል።

የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደርን ጨምሮ የክልል መስተዳድሮች ለትልልቅ ስብሰባዎች ፈቃድ ለመስጠትም ሆነ አስፈላጊውን የፀጥታ ኃይል ለመመደብ እምብዛም ፈቃደኛ አልነበሩም።

ከ2003 ዓ.ም. መጨረሻ ጀምሮ በዓመቱ ውስጥ በአብዛኛው ጊዜ መንግስት በሐይማኖት ጉዳይ ጣልቃ ገብቷል ያሉ አንዳንድ የሙስሊም ማህበረሰብ አባላት በአዲስ አበባ ታላላቅ መስጊዶች፣ በአወሊያ የእስልምና ማዕከል እና በሌሎች የአገሪቱ ክፍሎች ከዓርብ ጸሎት በማስከተል ሰላማዊ ተቃውሞ አሰምተዋል። ብዙዎቹ ሰልፎች ያለምንም እክል የተካሄዱ ቢሆንም ፖሊስ አንዳንዶቹን ሲያስራቸው እና አላስፈላጊ ኃይል ሲጠቀም ተስተውሏል።

በሐምሌ መገባደጃ ባለስልጣናት በራሱ የተሾመ የሙሰሊሙ ማህበረሰብ መፍትሄ አፈላላጊ ኮሚቴ አባላትን ጨምሮ ሰልፈኞችን አስረው የነበረ ሲሆን፤መንስኤውም መንግስት በሃይማኖት ጉዳይ ጣልቃ መግባቱን መቃወማቸው ነበር። በኂላ ላይ ከሰልፈኞቹ አብዛኞቹ ምንም ክስ ሳይመሰረትባቸው ተለቀዋል። ጥቅምት 19 ቀን ባለስልጣናት በ29 ግለሰቦች ላይ በፀረ ሽብር ሕጉ መሰረት ክስ መስርተውባቸዋል። ከነዚህም 28ቱ ከተቃውሞ እንቅስቃሴው ጋር ግንኙነት የነበራቸው ሲሆን፤ አንድ ደግሞ ከውጭ አገር ኤምባሲ ሕገወጥ በሆነ መንገድ ገንዘብ በመቀበል የተከሰሱ ናቸው።

ጥቅምት 11 ቀን በአማራ ክልል ደቡብ ወሎ ዞን በአካባቢ የእስልምና ምክር ቤት ምርጫ ላይ በፖሊስ እና በሰላማዊ ሰልፈኞች መካከል ግጭት ተነስቶ ነበር። ይህን ግጭት በተመለከተ የተለያዩ ዘገባዎች ቀርበዋል። አንድ ሪፖርት ሰላማዊ ሰልፈኞች በምርጫው በተሳተፉ ሙስሊሞች ቤቶች ላይ ድንጋይ እንደወረወሩ ይናገራል። በምላሹም ፖሊስ የሰልፉን አስተባባሪ ያስራል፤ በዚህ ወቅት ሕዝቡ ወደ ፖሊስ ጣቢያው በመግባት አስተባባሪው እንዲፈታ ይጠይቃል። ሰልፈኞቹ ወደ ፖሊስ ጣቢያው የገቡት በጉልበት እንደሆነ በዚህም አንድ የፖሊስ አባል እንደገደሉ እና በአንድ ሌላ ላይ ደግሞ ከባድ የመቁሰል

አደጋ እንዳደረሱ ተነግሯል። ፖሊስም የታሰረውን የሰልፍ አስተባባሪ ጨምሮ ሁለት ሰልፈኞችን እንደገደለ ተገልጧል።

**የመደራጀት ነፃነት**

ምንም እንኳ ሕጉ የመደራጀት ነፃነትን እና በሠላማዊ የፖለቲካ እንቅስቃሴ የመሳተፍ ያልተገደበ መብትን ቢሰጥም በተግባር ግን መንግሥት ይህን መብት ገድቧል።

በበጎ አድራጎት እና ማኅበራት ሕግ መሠረት መንግሥታዊ ላልሆኑ ድርጅቶች የሚደረጉ ምንጫቸው ያልታወቁ ልገሳዎች አይፈቀዱም። በዚህም ምክንያት ለጋሾች በሙሉ ስማቸው በሚስጥር እንደማይያዝ ተገንዝበዋል። ይኸው አሠራር በማንኛቸውም ለፖለቲካ ፓርቲዎች በሚደረጉ ልገሳዎች ሁሉ ላይ በተመሳሳይ መልኩ ተፈፃሚ ነው።

የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር የዓለም አቀፍ መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶችን የምዝገባ ማመልከቻዎች የሚመረምር ሲኾን፣ [አመልካቹ ደርጅት] እንዲመዘገብ አልያም እንዳይመዘገብ የውሳኔ ሀሳብ ያቀርባል።

**ሐ. የሃይማኖት ነፃነት**

ስለ ሃይማኖት ነፃነት ሙሉ መግለጫውን ከዓለም አቀፍ የሃይማኖት ነፃነት ሪፖርት www.state.gov/j/drl/irf/rpt ድረ-ገጽ ያገኛሉ።

**መ. የመንቀሳቀስ ነፃነት፣ ተፈናቃዮች፣ የስደተኞች ጥበቃ እና ሀገር አልባ ሰዎች**

ምንም እንኳ ሕጉ በአገር ውስጥ የመንቀሳቀስ፣ ወደ ውጭ አገር የመጓዝ፣ የመሰደድ፣ እና ወደ ሀገር የመመለስ ነፃነትን ቢያጎናፅፍም፣ በተግባር ግን መንግሥት ከእነዚህ ነፃነቶች የተወሰኑትን ገድቧል።

መንግሥት ለስደተኞችና ከስደት ተመላሾች፣ ለጥገኝነት ጠያቂዎች፣ለአገር አልባ ሰዎች እና ለሌሎች ሰዎች ጥበቃ በማድረግ እና በመርዳት ረገድ ከተባበሩት መንግሥታት የስደተኞች ጉዳይ ከፍተኛ ኮሚሽነር (UNHCR) ጽ/ቤት እና ከሌሎች ሰብዓዊ ድርጅቶች ጋር በትብብር ሰርቷል።

**<u>የሀገር ውስጥ እንቅስቃሴ</u>**፡ መንግሥት ሰዎች በሶማሊ ክልል ወደሚገኘው ኦጋዴን አካባቢ እንዳይሄዱ፣ እንዲሁም በኦጋዴን ውስጥ እንዳይዘዋወሩ ጥሎ የነበረውን ገደብ ቢያለዝብም ሙሉ በሙሉ ግን አላነሳውም፤ ለዚህም ኦብነግ የፀጥታ/የደህንነት ስጋት ይፈጥራል የሚል ምክንያት ማቅረቡን ቀጥሏል። ( ክፍል 2. መ. ስር ተፈናቃዮች የሚለውን ይመልከቱ)። በጦርነት በተጎዱ አካባቢዎች በነበረው የጸጥታ ስጋት የተነሳ የምግብ እና የመድሃኒት አቅርቦቶች ለጊዜው ተቋርጠው ነበር።

መንግስት ለኤርትራውያን ስደተኞች ያወጣውን ከመጠለያ ጣቢያ ውጪ የመኖር ፖሊሲ በማስፋፋት ለሁለሁም ስደተኞች ከመጠለያ ውጪ እንዲኖሩ ፈቅዷል። ይህን መርሀ ግብር ከሚመራው የስደተኞች እና ከስደት ተመላሾች ጉዳይ አስተዳደር መስሪያ ቤት በተገኘ መረጃ በዓመቱ 3,412 ስደተኞች ከመጠለያ ጣቢያ ውጪ ለመኖር ችለዋል። ይህ አሃዝ በ2003ዓ.ም. 1,294 እንዲሁም 2002ዓ.ም. 723 ነበር። ከዚህ ፖሊሲ አስቀድሞ እንዲህ ዓይነት ፈቃድ የሚሰጠው በዋነኝነት የከፍተኛ ትምሕርትን ለመከታተል፣ ለሕክምና ክትትል ወይም በመጠለያ ጣቢያዎች የጸጥታ ስጋትን ለመቀነስ ነበር።

<u>ስደት</u>፡ ታዋቂ የሰብአዊ መብት ተሟጋቾችን ጨምሮ በርካታ ዜጎች በሌሎች አገሮች የፖለቲካ ጥገኝነት ጠይቀዋል፤ አልያም ያለፍላጎታቸው በውጭ አገራት በስደት ይኖራሉ። (ክፍል 2.ሀ.ን ይመልከቱ።).

**በአገር ውስጥ የተፈናቀሉ ሰዎች**

በዓመቱ በአገሪቱ ውስጥ የነበሩት የሀገር ውስጥ ተፈናቃዮች አጠቃላይ ቁጥር አልታወቀም። ቀደም ሲል በጋምቤላ፣ በኦሮሚያ፣ በደ/ብ/ብ/ሕ/ክ/ እና በሶማሌ ክልል በተቀሰቀሱ ግጭቶች ለመፈናቀል የተዳረጉ በርካታ ሰዎች አሁንም እንደተፈናቀሉ ናቸው። በዓመቱ ውስጥ በድርቅም ምክንያት ሰዎች ተፈናቅለዋል።

በደ/ብ/ብ/ሕ/ ክልል ቤንች ማጂ ዞን የተቀሰቀሰ የመሬት ይገባኛል ውዝግብ የብሔሮች ግጭት አስከትሎ 463 የአማራ ተወላጆች በመጋቢት ወር እንዲፈናቀሉ አድርጓል። እነዚህ ተፈናቃዮች ወደ አዲስ አበባ ተልከው መንግስት ምግብ እና ሌሎች አስፈላጊ ቁሳቁሶችን አቅርቦላቸዋል። የክልሉ መንግስት የተፈናቃዮቹ ቤተሰቦች በደርግ ዘመን (ከ1966-83ዓ.ም.) ጥለው ወደወጡበት አማራ ክልል እንዲመለሱ አሳስቧል። በመጨረሻ ክልላዊ መንግስቱ አብዛኞቹን ተፈናቃዮች በአማራ ክልል ሰሜን ጎንደር ወደሚገኘው ጠገዴ ለማዛወር ወስኗል።

በአማራ፣ኦሮሚያ እና ደ/ብ/ብ/ሕ/ ክልሎች በሐምሌ አጋማሽ እና በነሐሴ መካከል በተከሰቱ የጎርፍ አደጋዎች የተነሳ ነዋሪዎች ለጊዜያዊ መፈናቀሎች እንደተዳረጉ ሪፖርት ተደርጓል። በኋላም ከነዚህ ተፈናቃዮች አብዛኛዎቹ ወደየቤታቸው ተመልሰዋል።

በሐምሌ ወር በደቡባዊ የአገሪቱ ክፍል ሞያሌ አካባቢ በተነሳ የጎሳ ግጭት በ 10 ሺዎች የሚቆጠሩ ሰዎች ተፈናቅለዋል። የፌዴራል አደጋ መከላከል እና ምግብ ዋስትና ሴክተር የሰጠውን ምላሽ ተከትሎ ግጭቱ እስኪበርድ ድረስ የሞያሌ ከተማ በፌዴራል መንግስት ቁጥጥር ስር ቆይታለች። ይህም የፌዴራል ጉዳዮች ሚኒስቴር ቡድን በቦታው ተሰማርቶ የሰብዓዊ ዕርዳታን እንዲያስተባብር አስችሎታል።በፌዴራል አደጋ መከላከል እና ምግብ ዋስትና ሴክተር እና በልማት አጋሮች በጋራ የተከናወነ ጥናታዊ ዳሰሳ እንደሚያመለክተው አብዛኞቹ ተፈናቃዮች በመስከረም መጀመሪያ

ወደቤቶቻቸው ተመልሰዋል፡፡ ሆኖም 1,000 ቤተሰቦች ያለመጠለያ ቀርተዋል፤ 58,000 የሚሆኑ ሰዎች በግጭቱ የተነሳ የምግብ ዕርዳታ ፈላጊ ሆነዋል፤ እንዲሁም ከ78,000 የሚበልጡ ዜጎች ንጹህ የመጠጥ ውሃ አቅርቦት እንዳይደርሳቸው ተደርጓል፡፡

በዓመቱ ውስጥ ድርቅ በሶማሌ ክልል መፈናቀልን ያስከተለ ሲሆን፤በአንዳንድ አካባቢዎች በቀጠሉ ግጭቶች የተነሳ ችግሩ ተባብሶ ነበር፡፡

የፌዴራል መንግሥት የአገር ውስጥ ተፈናቃዮችን በተለየ መልኩ ስለማመለከታቸው፤ የአገር ውስጥ ተፈናቃዮች ጥበቃን፣ መመለስን፣ ዳግም ሠፈራን አልያም ዘላቂ መፍትሄዎችን የመሳሰሉ ጉዳዮችን የማስተናበር ኃላፊነት የተሰጠው ለዚሁ ተብሎ የተቋቋመ ጽ/ቤትም አልነበረም፡፡ መንግሥት የሀገር ውስጥ ተፈናቃዮችን የተመለከተ መረጃ አጠናቅሮ አልያዘም፡፡ በግብርና እና ገጠር ልማት ሚኒስቴር ሥር የሚገኘው የፌደራል የአደጋ አስተዳደርና የምግብ ዋስትና ሴክተር፣ ከጤና ጥበቃ እንዲሁም ከውሀ እና ኢነርጂ ሚኒስቴር ጋር በመተባበር ለአስቸኳይ የእርዳታ ጥያቄ ምላሽ የሚሰጥ ዋነኛው የመንግሥት አካል ነው፡፡

መንግሥት የሰብዓዊ መብት ድርጅቶች፣ መገናኛ ብዙሃን ፣ የረድዔት ድርጅቶች፣ እና ዲፕሎማቶች በግጭት ወደተጎዱ አካባቢዎች በተለይም በሶማሌ ክልል በሚገኙት ፊቅ፣ ደገሃቡር፣ ቆራሄ እና ዋርዴር አካባቢዎች እንዳይሄዱ ጥሎት የነበረው ገደብ እንደቀጠለ ነው፡፡ ቀደም ባሉት ዓመታት የተጀመረው ክልከላዎቹን የማለዘብ አዝማሚያ የቀጠለ ሲሆን ይህም በተለይ ለሶማሌ ክልል የሚደርሰው የሰብዓዊ ዕርዳታ እንዲሻሻል እገዛ አድርጓል፡፡ ጋዜጠኞች ግጭት ወዳለባቸው አካባቢዎች ከመግባታቸው በፊት እንዲመዘገቡ ተጠይቀዋል፡፡ መንግስት መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች የጸጥታ ችግር ወዳለባቸው አካባቢዎች እንዲገቡ የሚፈቅድ ግልጽ ፖሊሲ ስለሌለው፤ የክልል መንግስት ባለስልጣናት እና ወታደራዊ ኃላፊዎች የሚቀርቡላቸውን ጥያቄዎች በተደጋጋሚ ለፌዴራል መንግስት እንዲመሩ አድርገዋቸዋል፡፡ ክልላዊ ፖሊስ ወይም የአካባቢ ሚሊሽያዎች አልፎ አልፎ የፀጥታ ችግርን እንደምክንያት በመጥቀስ መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች ወደተወሰኑ ሥፍራዎች እንዳይሄዱ ከልክለዋል በሚል የቀረቡ ሪፖርቶች ነበሩ፡፡

**የስደተኞች ጥበቃ**

**<u>ጥገኝነት ስለማግኘት</u>**፡ የአገሪቱ ሕግ ጥገኝነት መስጠትን ወይም ስደተኞችን መቀበልን በሚመለከት ደንግጓል፤ መንግሥትም ለስደተኞች ጥበቃ ለማድረግ የሚያስችል ሥርዓት ዘርግቷል፡፡

በተባበሩት መንግሥታት የስደተኞች ጉዳይ ከፍተኛ ኮሚሽን ሪፖርት መሠረት፣ አገሪቱ እስከ ዓመቱ መጨረሻ 376,410 ስደተኞችን ተቀብላ አስተናግዳለች፡፡ ከስደተኞቹ ውስጥ አብዛኛዎቹ (223,243)

ከሶማሊያ የመጡ ሲኾን፣ ሌሎቹ ከሱዳን እና ከደቡብ ሱዳን (66,177 - በደቡብ ሱዳን እና በኢትዮጵያ ድንበር አካባቢ ከሚኖሩት ወደ 20,000 የሚጠጉ ያልተመዘገቡ ስደተኞች በተጨማሪ)፣ ከኤርትራ (62,996) እና ከሌሎች አገራት፣ በተለይም ከኬንያ (3,994) ናቸው። በዓመቱ ከሶማሊያ የገቡ አዲስ ስደተኞች 50,000 ያህል ሲኾኑ፣ ቁጥሩ በ2003 ከነበረው 100,000 በከፍተኛ ደረጃ መቀነሱን ያሳያል።

የተባበሩት መንግሥታት የስደተኞች ጉዳይ ከፍተኛ ኮሚሽን፣ መንግሥት እና የሰብዓዊ ድርጅቶች በሱዳን የብሉናይል ክፍለሀገር የሚካሄደውን ግጭት በመሸሽ ወደ ኢትዮጵያ ለሚገቡ የሱዳን ስደተኞች እንክብካቤ ማድረጋቸውን ቀጥለዋል።

በተባበሩት መንግሥታት  የስደተኞች ጉዳይ ከፍተኛ ኮሚሽን ሪፖርት መሰረት፣ በየወሩ በግምት ወደ 700 የሚጠጉ አዳዲስ ኤርትራዊያን ጥገኝነት ጠያቂዎች ወደ ኢትዮጵያ መግባት ቀጥለዋል። በመቶዎች የሚቆጠሩ ኤርትራዊያን ስደተኞች በየወሩ በሱዳን እና በግብጽ በኩል አድርገው ወደ እስራኤል፣ አውሮጳ እና ሌሎች አገራት ለመሄድ ለሁለተኛ ደረጃ ስደት አገራቸውን ይለቃሉ ተብሏል። የተባበሩት መንግሥታት የስደተኞች ጉዳይ ከፍተኛ ኮሚሽን እና የስደተኞችና ከስደት ተመላሾች ባለሥልጣን በ2003 700 የሚሆኑ፣ በሪፖርት ዓመቱ ደግሞ 952 ለሚሆኑ ግብፅ ውስጥ ታስረው ቆይተው በአገሪቱ ባለሥልጣናት ለተባረሩ ኤርትራዊያን ስደተኞች አቀባበል በማድረግ እና ወደ ማይ ዓይኒ አልያም አዲ ሐሩሽ የስደተኞች መጠለያ በማጓጓዝ ረድተዋቸዋል። የተባበሩት መንግሥታት የስደተኞች ጉዳይ ከፍተኛ ኮሚሽን ከወላጆች ተለይተው ኤርትራን ለቅቀው ወደ ኢትዮጵያ የሚሰደዱ ታዳጊዎች ቁጥር በዓመቱ መጨረሻ ላይ 1,200 እንደነበረ አመልክቷል። በዚህ መልኩ ከተሰደዱት ከጠቅላላው ታዳጊ ወጣቶች ውስጥ ዕድሜአቸው ከ15 እስከ 17 ዓመት ክልል ውስጥ የሚገኙት ከ75 በመቶ በላይ ይሆናሉ።

<u>ስራ የመቀጠር ዕድል</u>፡ መንግሥት ለስደተኞች የሥራ ፈቃድ አይሰጥም።

**<u>የመሠረታዊ አገልግሎቶች ተደራሽነት</u>**፡ በመጠለያ ጣቢያ የሚኖሩ ስደተኞች የትምህርት እና የጤና አገልግሎት ያገኛሉ። ከመጠለያ ጣቢያ ውጪ ያሉ ስደተኞችን በተመለከተም፣ መሠረታዊ አገልግሎቶችን በማግኘት ረገድ መድልዎ ስለመኖሩ የቀረቡ ሪፖርቶች አልነበሩም።

**<u>ዘላቂ መፍትኄዎች</u>**፡ መንግሥት ከኤርትራ፣ ከሶማሊያ፣ ከደቡብ ሱዳን እና ከሱዳን የሚመጡ ጥገኝነት ጠያቂዎችን በስደተኛነት ይቀበላል። መንግሥት ስደተኞች በቋሚነት ኢትዮጵያ ውስጥ እንዲኖሩ ቢፈቅድም፣ ዜግነት ማግኘት የሚችሉበትን ዕድል ግን አይሰጣቸውም። በሪፖርት ዓመቱ 5,543 ስደተኞች በሌላ አገር ለመኖር አገሪቱን ለቀው ሄደዋል።

## ክፍል 3. የፖለቲካ መብት አከባበር: የዜጎች መንግሥታቸውን የመቀየር መብት

ዜጎች መንግሥታቸውን በሠላማዊ መንገድ የመቀየር መብት እንዳላቸው በሕገ መንግሥቱ እና በሕግ ተደንግጓል። በተግባር ግን የገዢው ፓርቲ በተለያየ ሁኔታ ይህንን መብት ገድቦታል።

### ምርጫ እና የፖለቲካ ተሳትፎ

**በቅርቡ የተካሄዱ ምርጫዎች**: ነሐሴ 14 ቀን 2004፣ ጠቅላይ ሚኒስትር መለስ ዜናዊ አረፉ። ገዢው ፓርቲ ኢሕአዴግ ምክትል ጠቅላይ ሚኒስትሩን አቶ ኃይለማርያም ደሳለኝን የፓርቲው ሊቀመንበር በማድረግ የመለስን ቦታ ተክተው እንዲሠሩ የመረጣቸው ሲኾን፣ ይህንኑ ተከትሎም የአገሪቱ ጠቅላይ ሚኒስትር እንዲሆኑ ሰይሟቸዋል። መስከረም 11 ቀን ፓርላማው ኃይለማርያም ደሳለኝን የአገሪቱ ጠቅላይ ሚኒስትር አድርጎ መርጧል።

በ2002 በተካሄደው አገር አቀፍ የፓርላማ ምርጫ፣ ኢሕአዴግ እና አጋር ድርጅቶች ካሉት 547 መቀመጫዎች 545ቱን በተከታታይ ለአራተኛ የአምስት ዓመት የሥራ ዘመን በሥልጣን ላይ ለመቆየት አሸንፈዋል። የገለልተኛ የምርጫ ታዛቢዎች ተሳትፎ መንግሥት ባስቀመጠው ገደብ ምክንያት እጅግ በጣም ውሱን ነበር። ምንም እንኳ ምርጫዎቹን እንዲታዘቡ የተፈቀደላቸው በቁጥር አነስተኛ የሆኑ ዓለም አቀፍ ታዛቢዎች የድምፅ አሰጣጡ ቴክኒካዊ ገጽታዎች በብቃት ተካሂደዋል ብለው ቢደመድሙም፣አንዳንዶች ደግሞ ከምርጫው ዕለት አስቀድሞ ለነጻ እና ፍትኃዊ ምርጫ የተመቻቸ ሁኔታ እንዳልነበረ ጠቅሰዋል።ከ1997 አገራዊ ምርጫ ወዲህ በሥራ ላይ የዋሉ በርካታ ሕግጋት፣ መመሪያዎች እና የአሠራር ሒደቶች በጠቅላላው የምርጫ ሒደት ለኢሕአዴግ ግልጽ የተጠቃሚነት ዕድሎችን ፈጥረውለታል። የተቃዋሚ ዕጩዎችን እና ደጋፊዎችን ማስፈራራትን ጨምሮ መንግሥት የተጠቀመባቸው ኢ-ፍትኃዊ ስልቶች ለኢሕአዴግ በከፍተኛ ልዩነት ማሸነፍ አስተዋጽኦ ማድረጋቸውን የሚያረጋግጡ በርካታ ማስረጃዎች ነበሩ። በተጨማሪም፣ የመራጮች ትምህርት በድምፅ አሰጣጥ ቴክኒካዊ ሒደቶች ዙርያ መረጃ በመስጠት ላይ ብቻ የተገደበ ሲኾን፣ ይህም ትምህርት ከድምጽ መስጫው ዕለት ጥቂት ቀናት አስቀድሞ ብሎ በብሔራዊ ምርጫ ቦርድ አማካይነት ብቻ እንዲሰጥ ተደርጓል።

ከድምጽ መስጫው ዕለት አንድ ሳምንት በፊት ታዛቢዎቹን የላከው የአፍሪካ ሕብረት ምርጫውን ነፃ እና ፍትኃዊ ሲል ገልጾታል። የተወሰኑ ታዛቢዎቹን ከድምጽ መስጫው ዕለት ጥቂት ወራት በፊት የላከው የአውሮፓ ሕብረት ምርጫው በግልጽነት ረገድ ዓለም አቀፍ ደረጃዎችን ያላሟላ እና ለተቃዋሚ ፓርቲዎች እኩል የመወዳደሪያ ሜዳ ያልነበረው ነው ሲል ደምድሟል። በአጠቃላይ የአውሮፓ ሕብረት ምርጫው "በፍርኃትና በሥጋት የተሞላ" እንደነበር፣ በተቃዋሚዎች የቀረቡት ማዋከብ እና

ማስፈራራትን የተመለከቱ አቤቱታዎች ብዛት እና ተመሳሳይነትም “አሳሳቢ ጉዳይ” እንደሆነ በመጥቀስ “በአጠቃላይ የምርጫ ሒደቱ ግምገማ” ላይ እነዚህ ነጥቦች ከግምት መግባት አለባቸው ሲል አሳስቧል።

**<u>የፖለቲካ ፓርቲዎች</u>**፡ የፖለቲካ ፓርቲዎች በአብዛኛው ብሔር-ተኮር ናቸው። የኢሕአዴግ አባል ድርጅቶች ለአባሎቻቸው አንዳንድ ጥቅሞችን ያስገኛሉ፤ አባል ድርጅቶቹ በርካታ የንግድ ድርጅቶች ባለቤት ሲሆኑ፣ የሥራ ዕድልና የንግድ ኮንትራት ለታማኝ ደጋፊዎቻቸው እንደሚሰጡ በስፋት ይነገር ነበር። በርካታ ተቃዋሚ የፖለቲካ ፓርቲዎች የኢህአዴግ አባላት የቤቶች ወይም የሕንፃ ባለቤቶች ንብረታቸውን ለእነርሱ እንዳያከራዩ ጫና እንደሚፈጥሩ ወይም እንደሚያስፈራሯቸው በመጥቀስ ለቢሮ አገልግሎት የሚውሉ ቤቶች አልያም ሕንፃዎችን ለመከራየት መቸገራቸውን ተናግረዋል።

በሪፖርት ዓመቱ፣ መምህራን እና ሌሎች የመንግሥት ሠራተኞች የተቃዋሚ ፖለቲካ ፓርቲዎች አባል ከሆኑ ከሥራ ይታገዱ እንደነበር ተዓማኒ ሪፖርቶች ቀርበዋል። የኦሮሚያ ክልላዊ መንግሥት የተቃዋሚ ፓርቲ አባላትን፣ በተለይም መምህራንን፣ ከሥራ አባርራችኋለሁ በማለት ያስፈራራቸው እንደነበር የኦሮሞ ተቃዋሚ ቡድኖች ተናግረዋል። የመንግሥት ባለሥልጣናት በህጋዊ መንገድ የሚንቀሳቀሱ የኦሮሞ ተቃዋሚ ድርጅቶች በርካታ አባላት በምስጢር የኦሮሞ ነፃነት ግንባር አባላት ናቸው በማለት የሚከስሱ ሲሆን፣ ከዚህ ይበልጥ ሰፋ ባለ ደረጃም የበርካታ ተቃዋሚ ፓርቲዎች አባላትን ከግንቦት 7 ጋር ግንኙነት አላቸው በማለት ይከስሳሉ። በዩኒቨርሲቲ ደረጃ የመድረክ እና የአባል ድርጅቶቹ አባላት የማስተማር ሥራቸውን ይሠራሉ።

በምርጫ ቦርድ የተመዘገቡ የፖለቲካ ፓርቲዎች የአካባቢ ጽሕፈት ቤቶችን ለመክፈትና ለመጠቀም የግድ ከክልል መንግሥታት ፈቃድ ማግኘት አለባቸው።

በ2002 አጋማሽ ለምርጫ ቅስቀሳ የሚውል ድጎማ ከመንግሥት የሚሰጥበት የአሠራር ሥርዓት ይፋ ተደርጓል። በዚህ ሥርዓት መሠረት፣ የፖለቲካ ፓርቲዎች በከፊል በፓርላማ ውስጥ ባላቸው መቀመጫ መሠረት ከብሔራዊ ምርጫ ቦርድ የገንዘብ ድጎማ እንደሚያገኙ ተደንግጓል። በ2003፣ ኢሕአዴግ በፓርላማው እና በክልል ምክር ቤቶች ባለው የበላይነት ላይ በመመሥረት ከድጎማው የሚደርሰውን 75 በመቶ አካባቢ የሚደርስ ድርሻውን፣ በፓርላማው መቀመጫ ኖራቸውም አልኖራቸውም፣ የፖለቲካ ፓርቲዎች የጋራ ምክር ቤት አባላት ለነበሩ ሌሎች የፖለቲካ ፓርቲዎች አከፋፍሎታል። ትልቁ ተቃዋሚ ግንባር፣ መድረክ፣ ከኢሕአዴግ ጋር ባለው እልባት ያላገኘ ውዝግብ ሳቢያ ከጋራ ምክር ቤቱ ውጪ ሆኖ ቆይቷል። መድረክ አነስተኛ መጠን ያለው ድጎማ የቀረበለት ቢሆንም ፓርቲው ድጎማውን ለመቀበል ፈቃደኛ አልሆነም።

**<u>የሴቶች እና የአናሳዎች ተሳትፎ</u>**: ሴቶች ወይም አናሳዎችን ድምጽ ከመስጠት አለያም ከወንዶች ወይም አናሳ ካልሆኑ ዜጎች እኩል በሆነ ደረጃ በፖለቲካ ከመሳተፍ የሚከለክሉ ሕጎች አልያም ባህላዊ ወይም ልማዳዊ ድርጊቶች የሉም። በመላ አገሪቱ ካሉ ምክር ቤቶች ከፍተኛ የሴቶች ቁጥር ያለው የትግራይ ክልል ምክር ቤት ነው። ከአባላቱ 48.5 በመቶ ሴቶች ናቸው።

በብሔር ላይ የተመሠረተው የመንግሥት የፌደራሊዝም ፖሊሲ በሀገሪቱ ያሉ ዋና ዋና ብሔረሰቦች በሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ውስጥ የሚወከሉበትን ሁኔታ ፈጥሯል። በሀገሪቱ ከ80 በላይ ብሔረሰቦች ያሉ ሲሆን፣ አነስተኛ የሕዝብ ቁጥር ያላቸው ብሔረሰቦች በሕግ አውጭው ምክር ቤት ውክልና የላቸውም። በ1999 በተደረገው የሕዝብ ቆጠራ መሠረት በስድስት ክልሎች (ትግራይ፣ አማራ፣ ቤኒሻንጉል-ጉሙዝ፣ ደቡብ ሕዝቦች፣ ጋምቤላ እና ሐረር) ውስጥ በፓርላማ መቀመጫ ለማግኘት የሚያበቃ የመራጭ ብዛት የሌላቸው 24 የብሔር ቡድኖች ነበሩ፤ ነገር ግን በ2002 በተካሄደው ምርጫ ከእነዚህ የብሔር ቡድኖች የታጩ ግለሰቦች በሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ለሚገኙ 24 ልዩ መቀመጫዎች ተወዳድረዋል። በተጨማሪም እነዚሁ 24 የብሔር ቡድኖች እያንዳንዳቸው በፌዴሬሽን ምክር ቤት ውስጥ አንድ መቀመጫ አላቸው።

## ክፍል 4. ሙስና እና በመንግሥት ውስጥ የግልጽነት አለመኖር

የአገሪቱ ሕግ በመንግሥት የሥራ ኃላፊዎች ለሚፈፀም ሙስና የወንጀል ቅጣት ደንግጓል፤ ምንም እንኳ መንግሥት በርካታ የሥራ ኃላፊዎችን ለፍርድ ቢያቀርብም፣ አንዳንድ ባለሥልጣናት የሙስና ተግባራት መፈፀማቸውን ቀጥለዋል። ሙስና፣ በተለይም ጉቦ መጠየቅ፣ በዝቅተኞቹ የመንግሥት መዋቅር የሥራ ኃላፊዎች ችግር ሆኖ ቆይቷል። በፖሊስ እና በፍርድ ቤት አካባቢ የሚፈፀሙ ሙስናዎችም እንዲሁ ያልተቀረፉ ችግሮች ናቸው። አንዳንድ የመንግሥት ባለሥልጣናት መንግሥታዊ ድርጅቶችን ወደግል የማዛወር ሒደትን መጠቀሚያ ሲያደርጉት የሚታይ ሲኾን፣ የመንግሥት እና የፓርቲ የንግድ ድርጅቶች የኪራይ (Lease) መሬት እና ብድር በማግኘት ረገድ የቅድሚያ ተጠቃሚነት ዕድል ነበራቸው።

የፍትህ ሚኒስቴር፣ በዋነኛነት በፌደራል የሥነ-ምግባርና ፀረ-ሙስና ኮሚሽን አማካኝነት፣ ሙስናን የመዋጋት ተቀዳሚ ኃላፊነት ተጥሎበታል።

ነሐሴ 30 ቀን 2004፣ አምስት የድሬዳዋ ከተማ አስተዳደር ምክር ቤት አባላት የፌደራል ስነ-ምግባርና ፀረ-ሙስና ኮሚሽን በመሠረተባቸው ከሙስና ጋር የተያያዘ ክስ ተፈርዶባቸዋል። የመንግሥት መሬትን በህገ-ወጥ መንገድ መስጠትን፣ ከጨረታ ሂደቶች ጥቅም መሻትንና ጉቦ መቀበልን በሚያካትቱ ወንጀሎች

ጥፋተኛ መሆናቸው የተረጋገጠባቸው የምክር ቤቱ አባላት ከአንድ እስከ ሰባት ዓመታት የሚደርስ እስራት ተፈርዶባቸዋል፡፡

ሕጉ ሁሉም የመንግሥት ባለሥልጣናት እና ሠራተኞች ሀብታቸውን እና የግል ንብረታቸውን በይፋ እንዲያስመዘግቡ ይጠይቃል፡፡ የአገሪቱ ፕሬዚደንት፣ ጠቅላይ ሚኒስትር እና በካቢኔ ደረጃ ያሉ ሚኒስትሮች ሀብታቸውን አስመዝግበዋል፡፡ በዓመቱ መጨረሻ 32,297 የፌደራል መንግሥት ባለሥልጣናት ሀብታቸውን እንዳስመዘገቡ የፌደራል ሥነ-ምግባርና ፀረ-ሙስና ኮሚሽን ሪፖርት አመልክቷል፡፡

የአገሪቱ ሕግ ህዝብ ስለ መንግሥት አሠራር መረጃዎችን የማግኘት መብት እንዳለው ቢደነግግም፣ በተግባር ግን ይህ መብት በአመዛኙ ተገድቧል፡፡ ሕጉ የመረጃ ነፃነት ድንጋጌዎችን አካትቷል፡፡

መንግሥት ሕግጋትና ደንቦች ሥራ ላይ ከመዋላቸው በፊት በነጋሪት ጋዜጣ እንዲታተሙ ያደርጋል፡፡ የመንግሥት ኮሙኒኬሽን ጉዳዮች ጽሕፈት ቤት ከመንግሥት፣ ከመገናኛ ብዙኃን እና ከሕዝብ ጋር የሚደረጉ ግንኙነቶችን ይመራል፡፡ የግሉ ፕሬስ አባላት ለምንጠይቃቸው ጥያቄዎች መንግሥት ብዙ ጊዜ ምላሽ አይሰጠንም የሚል አቤቱታ አሰምተዋል፡፡

## ክፍል 5. በዓለም አቀፍ እና መንግሥታዊ ባልሆኑ አካላት የሚካሄድ የሰብዓዊ መብት ጥሰት ምርመራን በተመለከተ የመንግሥት አመለካከት

ምንም እንኳ በመንግሥት ከፍተኛ ገደብ ቢጣልባቸውም፣ በቁጥር አነስተኛ የሆኑ አገር በቀል የሰብዓዊ መብት ተሟጋች ድርጅቶች እንቅስቃሴ አድርገዋል፡፡ በአጠቃላይ መንግሥት አገር በቀል የሰብአዊ መብት ድርጅቶችን እና ዓለም አቀፍ ታዛቢዎችን እንቅስቃሴ በጥርጣሬና በጥንቃቄ ይመለከታል፡፡ በመንግሥት ቁጥጥር ሥር ያለው ሚዲያ ሂዩማን ራይትስ ዎች'ን የመሳሰሉ ዓለም አቀፍ የሰብአዊ መብት ድርጅቶችን የሚነቅፉ ዘገባዎች አቅርቧል፡፡ መንግሥት በዓመቱ በተደጋጋሚ ሚዛናዊነት የሚጎድለው እና የተሳሳተ ሪፖርት ያቀርባል በማለት ሂዩማን ራይትስ ዎች ላይ ጠንካራ ትችት ሰንዝሯል፡፡ መንግሥት በተጨማሪም ኢንተርናሽናል ክራይስስ ግሩፕ (ICG) ያወጣውን የጠቅላይ ሚኒስትር መለስ ዜናዊ ህልፈት የሚያሳድረውን ተጽዕኖ የሚተነትን ሪፖርት፣ ድርጅቱ (ICG) " ሚዛናዊ ያልሆነ" ተጠቅሟል፣ እንዲሁም ያሉትን ተጫባጭ ሁኔታዎች ያላገናዘበ በማለት ተችቶታል፡፡

የበጎ-አድራጎት ድርጅቶች እና ማኅበራት ሕግ ከሚሰበስቡት ፈንድ ከ10 ከመቶ በላይ ከውጭ ምንጮች የሚያገኙ የበጎ አድራጎት ድርጅቶች፣ ሶሳይቲዎች እና ማኅበራት (መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች እና የሲቪል ማኅበረሰብ ደርጅቶች) ሰብአዊ እና ዴሞክራሲያዊ መብትን፣ የብሔር ብሔረሰቦች እኩልነትን፣ ሥርዓተ-ፆታን፣ ሃይማኖትን፤ የሕፃናት እና የአካል ጉዳተኞች መብቶችን፣ የግጭት አፈታት ወይም

እርቅ፤ እንዲሁም የፍትህ አገልግሎት እና የሕግ አስፈፃሚ አካላት ብቃት ጉዳዮችን ለሚያራምድ ዓላማ መንቀሳቀስ የማይችሉ መሆኑን ደንግጓል። ምንም እንኳ ሁሉም እንቅስቃሴ ያደርጉ ነበር ባይባልም፣ የበጎ አድራጎት ድርጅቶች እና ማኅበራት ሕግ ከመፅደቁ በፊት 3,522 የተመዘገቡ ድርጅቶች ነበሩ። ሕጉ ፀድቆ ሥራ ላይ ከዋለ በኋላ ሁሉም የበጎ አድራጎት ድርጅቶች በመንግሥታዊው የበጎ አድራጎት ድርጅቶች እና ማኅበራት ኤጀንሲ ዳግም እንዲመዘገቡ ተጠይቀዋል። የሕጉ በሥራ ላይ መዋል መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች ከሰብአዊ መብቶች ጋር ተያያዥ በሆኑ ጉዳዮች ላይ የሚያደርጉትን እንቅስቃሴ በአስከፊ ሁኔታ የመገደብ አሉታዊ ውጤት ማሳደሩን ቀጥሏል። በሐምሌ ወር፣ የተባበሩት መንግሥታት የሰብአዊ መብቶች ከፍተኛ ኮሚሽነር አዲሱ የበጎ አድራጎት ድርጅቶች እና ማኅበራት ሕግ ከወጣ በኋላ የሲቪል ማኅበረሰቡ ምህዳር ‹‹በከፍተኛ ፍጥነት መጥበቡ›› እንደሚያሳስበው ገልጿል።

ከጥቅምት 2005 ጀምሮ 2,852 ነባርና አዲስ የሲቪል ማኅበረሰብ ድርጅቶች በሕጉ መሠረት ተመዝግበዋል። ከእነዚህ ውስጥ፣ 389ኙ የውጭ በጎ-አድራጎት ድርጅቶች፣ 491 "በኢትዮጵያ ነዋሪ" የበጎ-አድራጎት ድርጅቶች፣ 1,865ቱ ደግሞ "አገር በቀል" በጎ-አድራጎት ድርጅቶች፣ 60ዎቹ የጉዲፈቻ ኤጀንሲዎች፣ እንዲሁም 47ቱ የማኅበራት ስብስቦች (consortia) ናቸው። መንግሥት ዳግም ካልተመዘገቡት ድርጅቶች አብዛኛዎቹ ሕጉ ፀድቆ ሥራ ላይ ከመዋሉ በፊትም እንቅስቃሴ የማያደርጉ እንደነበሩ በአጽንኦት ይናገራል። አንዳንድ የሰብዓዊ መብት ተሟጋች ድርጅቶች ከገቢያቸው ከ10 በመቶ በላይ ከውጭ ለጋሾች ማሰባሰብ በማይችሉበት፣ ነገር ግን ተለይተው በተጠቀሱት ዘርፎች ለመንቀሳቀስ በሚያስችለው "አገር-በቀል" ማኅበርነት፣ አልያም ከገቢያቸው ከ10 በመቶ የበለጠ ከውጭ ለጋሾች መሰብሰብ በሚፈቅደው፣ ነገር ግን ተለይተው በተጠቀሱት ዘርፎች መንቀሳቀስን በሚከለክለው "በኢትዮጵያ ነዋሪ" ማኅበርነት በመመዝገብ ከሕጉ ጋር ራሳቸውን አጣጥመዋል።

ሕጉን ሥራ ላይ ለማዋል ከወጡት በርካታ የማስፈፀሚያ ደንቦች አንዱ፣ የ70/30 ደንብ የሚባለው፣ ከአንድ ድርጅት የሥራ ማስኬጃ በጀት ውስጥ የአስተዳደራዊ ወጪን ጣሪያ በ30 በመቶ ገድቧል። ደንቦቹ የመምህራን፣ የግብርና እና የጤና ኤክስቴንሽን ሠራተኞች፣ እንዲሁም ሌሎች የመንግሥት የሥራ ኃላፊዎች ሥልጠናን እንደ ‹‹አስተዳደራዊ›› ወጪ የሚፈርጅ ሲኾን፣ ለዚህም የሚያቀርበው መከራከሪያም ሥልጠና በተጠቃሚዎች ላይ ቀጥተኛ ውጤት የለውም የሚል ነው። ይህም ሁኔታ ወደ ብዙ ሰዎች ለመድረስ የአሠልጣኞች-ሥልጠና ሞዴልን መጠቀም በሚመርጡ የልማት እርዳታ አጋሮች ሊሰጡ የሚችሉ የሥልጠና መርኃ-ግብሮችን ቁጥር ገድቧል። በጉዳዩ ላይ ከልማት እርዳታ አጋሮች ጋር ውይይቶች ከተካሄዱ በኋላ መንግሥት የዚህን ደንብ አፈፃፀም እንደየፕሮጀክቶች ባህሪ እና ተጨባጭ ሁኔታ በተናጠል እየገመገመ ለማስተናገድ ተስማምቷል። በፌደራል ጉዳዮች ሚኒስቴር እና በለጋሽ አገራት ማኅበረሰብ ተወካይ በጋራ የሚመራ የሲቪል ማኅበረሰብ ዘርፍ የምክክር ቡድን በሕጉ አፈፃፀም

ሂደት የሚያጋጥሙ ተግዳሮቶችን ለመከታተልና በዚያም ዙርያ ለመወያየት በየተወሰኑ ጊዜያት ይሰበሰባል።

በጥቅምት ወር የበጎ-አድራጎት ድርጅቶች እና ማኅበራት ኤጀንሲ ባለፉት ሁለት ዓመታት ውስጥ ግብርን በተገቢ ሁኔታ ባለመክፈል፣ እንዲሁም የበጎ አድራጎት ድርጅቶችና ማኅበራት አዋጅ እና ተዛማጅ ደንቦችን ካለማክበር ጋር በተያያዘ ምክንያት 10 የሲቪል ማኅበረሰብ ድርጅቶችን መዝጋቱን ይፋ አድርጓል። በተጨማሪም ኤጀንሲው ለ476 የሲቪል ማኅበረሰብ ድርጅቶች ማስጠንቀቂያዎችን ሰጥቷል ተብሏል።

የበጎ-አድራጎት ድርጅቶች እና ማኅበራት ኤጀንሲ፣ የሰብአዊ መብቶች ጉባዔ እና የኢትዮጵያ የሕግ ባለሙያ ሴቶች ማኅበር ከውጪ ለጋሾች ያገኙትን ገንዘብ እንዳያንቀሳቅሱ በ2002 ያስተላለፈውን ውሳኔ ጠቅላይ ፍርድ ቤት በጥቅምት 9 አጽንቶታል።

መንግሥት፣ ጀስቲስ ፎር ኦል - ፕሪዝን ፌሎውሺፕ ኢትዮጵያ (JFA-PFE) ከተሰኘው የበጎ-አድራጎት ድርጅት በስተቀር፣ መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች የፌደራል ማረሚያ ቤቶችን፣ ፖሊስ ጣብያዎችን እና የፖለቲካ እስረኞችን እንዳይጎበኙ ከልክሏል። ጀስቲስ ፎር ኦል - ፕሪዝን ፌሎውሺፕ ኢትዮጵያ ከውጪ ለጋሾች ያልተገደበ የፋይናንስ ድጋፍ ማሰባሰብ እንዲችሉ በህግ የተቀመጠው ክልከላ ከማይመለከታቸው እና በሰብአዊ መብት ዙርያ እንዲንቀሳቀሱ ከተፈቀደላቸው ሦስት ድርጅቶች ውስጥ አንዱ ነው። ጀስቲስ ፎር ኦል - ፕሪዝን ፌሎውሺፕ ኢትዮጵያ እስረኞችን ለመጎብኘት የተፈቀደለት ሲሆን፣ እስረኞች ምህረት የሚያገኙበትን ዕድል በማመቻቸት አዎንታዊ ሚና ተጫውቷል።

የሰብዓዊ መብት ድርጅቶች፣ ጋዜጠኞች፣ የረድኤት ድርጅቶች እና የዲፕሎማቲክ ሚሲዮኖች ግጭት ወዳለባቸው አካባቢዎች፣ በተለይም በሶማሌ ክልል ፊቅ፣ ደገሐቡር፣ ቆራሄ እና ከፊል ዋርዴርን የመሳሰሉ ዞኖች እንዳይሄዱ የተጣለው ገደብ ቀጥሏል። ቀደም ባሉት ዓመታት የተጀመረው ገደቦችን በከፊል የማለዘብ እርምጃ የቀጠለ ሲኾን፣ ይህም በተለይ በሶማሌ ክልል የሰብዓዊ ረድዔት አቅርቦት እንዲሻሻል ረድቷል። ጋዜጠኞች ግጭት ወዳለባቸው አካባቢዎች ከመግባታቸው በፊት እንዲመዘገቡ ይጠየቃሉ። መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች ችግር ወዳለባቸው አካባቢዎች በሚያደርጉት እንቅስቃሴ ዙርያ መንግሥት የጠራ ፖሊሲ የለውም። ይህም የክልል መንግሥት የሥራ ኃላፊዎችና ወታደራዊ መኮንኖች ወደ እነዚህ አካባቢዎች ለመሄድ የሚቀርቡ ጥያቄዎችን ወደ ፌደራል መንግሥት እንዲመሩ አድርጓቸዋል። የክልል ፖሊስ ወይም የአካባቢ ሚሊሻዎች መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች አልፎ አልፎ በተለዩ ቦታዎች የሚያደርጉትን እንቅስቃሴ፣ የፀጥታ ችግርን እንደ ምክንያት በመጥቀስ፣ እንደገደቡ አንዳንድ ሪፖርቶች አመልክተዋል።

የአካባቢ ነዋሪዎች መንግሥታዊ ካልሆኑ ድርጅቶች እና የሰብዓዊ መብት ጥሰቶችን ለመመርመር ከሚመጡ የውጭ መንግሥታት ተወካዮች ጋር እንዳይገናኙ የፀጥታ ኃይሎች ያስፈራሯቸው አልያም ያስሯቸው እንደነበር ከታማኝ ምንጮች የተገኙ መረጃዎች አረጋግጠዋል።

<u>**የመንግሥት የሰብዓዊ መብት አካላት**</u>፡ መንግሥት፣ ፓርላማው በሚሰጠው ፈንድ የሚተዳደር እና በፓርላማው የሚገመገም፣ በከፊል ነፃ የሆነ የኢትዮጵያ ሰብዓዊ መብት ኮሚሽን የተሰኘ ድርጅት አቋቁሟል። ኮሚሽኑ የሰብዓዊ መብት ጥሰት አቤቱታዎችን በመመርመር ዓመታዊ እና ወቅታዊ ሪፖርቶችን የሚያወጣ አካል ነው። ኮሚሽኑ ከ17 ዩኒቨርሲቲዎች እንዲሁም የኢትጵያ የሕግ ባለሙያ ሴቶች ማኅበር እና የኢትዮጵያ ክርስቲያን ጠበቃዎች ፌሎውሺፐ ከተሰኙ ሁለት የሲቪል ማኅበረሰብ ድርጅቶች ጋር በመተባበር 112 የሕግ ምክር የሚሰጡ ማዕከላትን ያንቀሳቅሳል። ከዚህም በላይ ኮሚሽኑ ከሁለት ተጨማሪ ዩኒቨርሲቲዎች ጋር የትብብር ስምምነት ለመፈራረም የቅድመ-ዝግጅት ሥራዎችን አጠናቋል። እንደ ኢሰመኮ ሪፖርት፣ አዲስ አበባ የሚገኘው የድርጅቱ ዋና ጽ/ቤት በዓመቱ ከቀረቡለት 952 አቤቱታዎች ለ90 ከመቶው ውሳኔ ሰጥቷል።

የሕዝብ እንባ ጠባቂ ጽ/ቤት በአስፈጻሚው አካል ቅርንጫፍ መሥሪያ ቤቶች ተፈጽመዋል የሚባሉ ከአስተዳደራዊ በደሎች ጋር የተያያዙ አቤቱታዎችን በመቀበል ይመረምራል። ጽ/ቤቱ ከመስከረም 2003 እስከ መስከረም 2004 በአዲስ አበባ 2094 ያህል አቤቱታዎችን ተቀብሏል። ከእነዚህ ውስጥ ጽ/ቤቱ በ784 አቤቱታዎች ላይ ምርመራ ያካሄደ ሲኾን፣ የተቀሩትን አቤቱታዎች በአማራጭ ዘዴዎች መፍትሄ እንዳስገኘላቸው ሪፖርት አድርጓል። አብዛኛዎቹ አቤቱታዎች ከማኅበራዊ ዋስትና፣ ከአሠሪና ሠራተኛ፣ እንዲሁም ከመኖሪያ ቤት እና ከንብረት-ነክ ውዝግቦች ጋር የተያያዙ ነበሩ። የእንባ ጠባቂ ጽ/ቤት አገር-አቀፍ መረጃ አያጠናቅርም። የእንባ ጠባቂ ጽ/ቤት በዓመቱ በተለያዩ የአገሪቱ ክፍሎች አምስት አዳዲስ ቢሮዎችን ከፍቷል።

በግንቦት ወር መንግሥት ብሔራዊ የሰብዓዊ መብቶች የድርጊት መርኃ-ግብር የማርቀቅ ሒደት ያጠናቀቀ ሲኾን፣ የመርኃ-ግብሩ አፈፃፀም ማስተባበሪያ ጽ/ቤት ፍትህ ሚኒስቴር ውስጥ ይሆናል።

## ክፍል 6. አድልዎ፣ ማኅበራዊ ጥቃት እና ሕገ-ወጥ የሰዎች ዝውውር

ሕገ መንግሥቱ የዘር፣ የብሔር፣ የዜግነት ወይም ሌላ ማኅበራዊ መሠረት፣ የቀለም፣ የፆታ፣ የቋንቋ፣ የሃይማኖት እና የፖለቲካዊ ወይም ሌላ አመለካከት፣ የንብረት፣ የልደት፣ ወይም የደረጃ ልዩነት ሳይደረግ ለሁሉም ሰዎች እኩል ጥበቃ እንደሚደረግ ይደነግጋል። ነገር ግን በተግባር መንግሥት እነዚህን መብቶች በተሟላ ሁኔታ አላስከበራቸውም ብሎም ጥበቃ አላደረገላቸውም።

### ሴቶች

**<u>አስገድዶ መድፈርና የቤት ውስጥ ጥቃት</u>**፡ አስገድዶ መድፈር በሕግ የሚያስቀጣ ወንጀል ሲሆን፣ እንደ ድርጊቱ ክብደት ከ5 እስከ 20 ዓመት በሚደርስ እስራት ያስቀጣል፡፡ ሆኖም በትዳር ውስጥ የሚፈፀም አስገድዶ የመድፈር ድርጊትን ለመቆጣጠር በግልጽ የተቀመጠ ህግ የለም፡፡ መንግሥት ሕጉን በተሟላ ሁኔታ ተፈጻሚ አላደረገውም፤ የዚህም አንዱ ምክንያት ድርጊቱን ለሚመለከተው አካል ሪፖርት ያለማድረግ መጠነ-ሰፊ የሆነ ችግር ስላለ ነው፡፡ ይህን ወንጀል ከፈፀሙ ግለሰቦች መካከል ስንቶቹ ክስ እንደተመሠረተባቸው፣ እንደተፈረደባቸው አልያም እንደተቀጡ የሚጠቁም መረጃ አልነበረም፡፡ በ1996 የወንጀል ሕጉ ተሻሽሎ ከወጣ በኋላ የአስገድዶ መድፈር ወንጀልን ሪፖርት የማድረግ ዝንባሌ እንደጨመረ ማስረጃዎች ቢጠቁሙም፣ የፍትህ ሥርዓቱ ግን በዚህ መልኩ ከሚቀርቡት ክሶች ጋር ሊጣጣም አልቻለም፡፡

በትዳር ጓደኛ የሚፈፀም አስገድዶ መድፈርን ጨምሮ፣ የቤት ውስጥ ጥቃት ከፍተኛ ማኅበራዊ ችግር ነበር፡፡ መንግሥት በ2003 ያካሄደው የሥነ-ሕዝብ እና የጤና ጥናት እንደሚያመለክተው፣ 68.4 ከመቶ የሚሆኑት ሴቶች ባሎች ሚስቶቻቸውን የመደብደብ መብት አላቸው ብለው ያምናሉ፡፡ ቀደም ሲል በ1997 በተካሄደው ጥናት ላይ 81 ከመቶ ሴቶች ተመሳሳይ እምነት የነበራቸው ሲኾን፣ ይህን ዓይነት አስተሳሰብ ያላቸው ሴቶች ቁጥር እየቀነሰ መሄዱን ያመለክታል፡፡ የ2003ቱ የሥነ-ሕዝብ እና የጤና ጥናት ከወንዶች 45 ከመቶ የሚሆኑት ሚስትን መደብደብ ነውር የለውም ብለው እንደሚያስቡ ይፋ አድርጓል፤ ይህም በ1997 የሥነ-ሕዝብ እና የጤና ጥናት ከተመዘገበው 52 በመቶ የመቀነስ ሁኔታ ያሳያል፡፡

ምንም እንኳ ሴቶች ለፖሊስና ለፍርድ ቤቶች በማመልከት የሕግ ከለላ ማግኘት ቢችሉም፣ በተለይ በገጠር አካባቢዎች ያለው ማኅበረሰብ አመለካከት እና የመሠረተ ልማት አለመስፋፋት ብዙ ሴቶች ጉዳያቸውን ወደ ሕግ እንዳይወስዱት ገድቧቸዋል፡፡ በዚህ ረገድ መንግሥት ክስ የመሠረተባቸው አጥፊዎች ቁጥር በጣም ውሱን ነበር፡፡ የቤት ውስጥ ጥቃት ሕገ-ወጥ ሆኖ ሳለ፣ በአስገድዶ መድፈር እና በቤት ውስጥ ጥቃት ላይ የተወሰደው የሕግ እርምጃ ወጥነት የጎደለው ነበር፡፡ ወንጀል ፈጻሚዎቹ እንዳደረሱት ጉዳት አስከፊነት፣ ከአነስተኛ የገንዘብ መቀጮ ጀምሮ ከ10 እስከ 15 ዓመት በሚደርስ እስራት ይቀጣሉ፡፡

የቤት ውስጥ ጥቃት እና የአስገድዶ መድፈር ክሶች ብዙ ጊዜ ከመጓተታቸውም ሌላ ቅድሚያ አልተሰጣቸውም፡፡ ጾታን መሠረት ካደረገ ጥቃት አኳያ በፍትህ ሥርዓቱ ውስጥ ከፍተኛ ክፍተት መታየቱ ቀጥሏል፤ የዚህም ምክንያት ደካማ የመረጃ አያያዝ እና ምርመራ ነበር፡፡

በዓመቱ፣ በተለይ ሕፃናት እና ሴቶች ላይ የተፈፀሙ የጥቃት ወንጀሎችን ለመዳኘት "ለሕፃናት ተስማሚ" የሆኑ ችሎቶች ተቋቁመዋል፡፡ የፖሊስ አባላት በሀገር በቀል መንግሥታዊ ያልሆኑ ደርጅቶች

እና በሴቶች ጉዳይ ሚኒስቴር አማካይነት የቤት ውስጥ ጥቃትን በተመለከተ ሥልጠና እንዲወስዱ ተደርጓል። የኢትዮጵያ ሰብዓዊ መብት ኮሚሽን የሴቶችና የሕፃናት መብቶቸ ምክትል ኮሚሽነር አሉት።

በሴቶች እና ልጃገረዶች ላይ ጾታን መሠረት ያደረገ ጥቃት ተፈጽሟል፤ ነገር ግን ከባህላዊ ተቀባይነት፣ ከኃፍረት፣ ከፍርሃት ወይም የሕግ ጥበቃ እንዳለ ካለማወቅ የተነሳ ጥቃቶቹ ሪፖርት አልተደረጉም።

መንግሥት በሴቶችና በሕፃናት ላይ የሚደርሱ የሰብአዊ መብት ጥሰቶችን ለመመርመር፣ በ1997 በኢትዮጵያ ሰብአዊ መብቶች ኮሚሽን ስር የሕፃናትና የሴቶች ጉዳይ ብሔራዊ ኮሚቴ አቋቁሟል።

__ጎጂ ልማዳዊ ድርጊቶች__: ከሴት ልጅ ግርዛት በተጨማሪ በስፋት የሚፈፀሙት ጎጂ ልማዳዊ ድርጊቶች ግግ ማስቧጠጥ፣ እንጥል መቁረጥ እና ጠለፋ ነበሩ።

ጠለፋ ሕገ-ወጥ ድርጊት ቢሆንም፣ መንግሥትም ጠለፋን ለማስቀረት ሙከራዎች ቢያደርግም፣ እንደ አማራ፣ ኦሮሚያ እና ደቡብ ብሔር፣ ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ባሉ አንዳንድ ክልሎች እንደቀጠለ ነው። በጠለፋ አማካኝነት የሚከናወኑ አብዛኛዎቹ ጋብቻዎች በኃይል የሚፈፀሙ ወሲባዊ ግንኙነቶችን ያካተቱ ነበሩ፤ በአብዛኛው ጠለፋ በሚከናወንበት ጊዜ ሴቶች አካላዊ ጥቃት ይደርስባቸዋል። የጠለፋ ድርጊቶች በቤተሰቦች፣ በማኅበረሰቦች እና በጎሳ ቡድኖች መካከል ግጭቶችን ይቀሰቅሳሉ። ጠለፋን መሠረት ባደረገ ጋብቻ ተጎጂዋ ከጠላፊዋ ጋር ለመጋባት ከተስማማች ጠላፊው አይቀጣም።

__የሴት ልጅ ግርዛት__: ጎልተው ከሚታዩ ጎጂ ልማዳዊ ድርጊቶች መካከል አንዱ የሆነው የሴት ልጅ ግርዛት ሕገ-ወጥ ተግባር ቢሆንም፣ መንግሥት ይህንን ድርጊት ለመከላከል አልያም የድርጊቱን ፈጻሚዎች ለመቅጣት ጠንካራ እንቅስቃሴ አላደረገም። ድርጊቱ አሁንም በስፋት ይፈፀማል፤ እንዲያም ሆኖ፣ በ2002 በፖፑሌሽን ካውንስል (Population Council) የተካሄደ ጥናት የጎጂ ልማዳዊ ድርጊቶች መጠን እየቀነሰ መሄዱን አመልክቷል። በጥናቱ ከተካተቱት እድሜያቸው ከ40 እስከ 49 ከሚሆኑ ሴቶች መካከል 80 በመቶ የሚሆኑት ግርዛት ተፈጽሞባቸዋል። እድሜያቸው ከ15 እስከ 19 ከሆኑት ወጣት ሴቶች እና ሴቶች መካከል ድርጊቱ የተፈፀመባቸው 58 ከመቶ ያህል ናቸው። አፋር፣ ደቡብ ብሔሮች፣ ብሔረሰቦች እና ሕዝቦች እንዲሁም ኦሮሚያ የሴት ልጅ ግርዛት በከፍተኛ ሁኔታ የሚፈፀምባቸው ክልሎች ናቸው።

__ወሲባዊ ትንኮሳ__: ወሲባዊ ትንኮሳ በስፋት ይስተዋላል። የወንጀል ሕጉ ድርጊቱን በሚፈፅሙት ላይ ከ18 እስከ 24 ወራት የሚደርስ የእስራት ቅጣት ይጥላል። ነገር ግን፣ ባለሥልጣናት ከትንኮሳ ጋር የተያያዙ ሕጎችን ተፈጻሚ አላደረጉም።

**የስነ-ተዋልዶ መብቶች፡** ግለሰቦች የልጆቻቸውን ብዛት፣ በምን ያህል ጊዜ አራርቀው መውለድ እንደሚኖርባቸው እና የሚወለዱበትን ጊዜ በነፃነት እና በኃላፊነት ስሜት የመወሰን እና ከአድልዎ፣ ከማስገደድ እና ከጥቃት ነፃ በሆነ መንፈስ ይህንኑ ለማድረግ የሚያስችል መረጃ እና መንገዱን የማወቅ መብት አላቸው፡፡ የ2003 የሥነ ሕዝብና የጤና ጥናት እንዳመለከተው፣ በመላ አገሪቱ ባለትዳር ከሆኑ ሴቶች መካከል 29 በመቶ የሚሆኑት የወሊድ መቆጣጠሪያ ተጠቃሚ ነበሩ፡፡ ይህ ቁጥር ከስድስት ዓመታት በፊት በተካሄደው ጥናት ከነበረበት ደረጃ በሁለት እጥፍ አድጓል፡፡ የ2003 የሥነ ሕዝብና የጤና ጥናት የእናቶች ሞት መጠን ከ100,000 ወላዶች 676 መሆኑን አመልክቷል፡፡ በ1997 የሥነ ሕዝብና የጤና ጥናት መሠረት ይህ አኃዝ ከ100,000 ወላዶች 673 ነበር፡፡ ከፍተኛ የደም መፍሰስ፣ ኢንፌክሽን፣ ከደም ግፊት ጋር የተያያዙ የጤና ችግሮች፣ እና በምጥ ወቅት የሚያጋጥሙ እክሎች ለእናቶች ሞት ዋነኛዎቹ ምክንያቶች እንደነበሩ ተጠቁሟል፡፡ በስፋት የሚስተዋለው በቤት ውስጥ የመውለድ ሁኔታ ለእነዚህ ችግሮች መከሰት መሠረታዊ ምክንያት ነበር፡፡ በጥናቱ ላይ በጤና ተቋማት ወይም በሠለጠኑ አዋላጆች ልጅ የተገላገሉ 9 ከመቶ ያህል ሴቶች ብቻ ነበሩ፡፡ የፌደራል ጤና ጥበቃ ሚኒስትሩ እንደተናገሩት፣ የጤና ልማት ሠራዊት በመባል የሚታወቀው የመንግሥት መርኃ-ግብር ይህ ቁጥር በትግራይ ክልል ወደ 50 ከመቶ ገደማ እንዲደርስ አስችሏል፡፡

**መድልዎ፡** በሴቶች ላይ የሚፈፀም መድልዎ በግምት 85 ከመቶ ያህል የአገሪቱ ሕዝብ በሚኖርበት የገጠሩ ክፍል የጎላ ነበር፡፡ ሕጉም ቢሆን መድልዎን የሚያንፀባረቁ ደንቦችን ይዟል፡፡ ባልን ሕጋዊ የቤተሰብ መሪ አድርጎ እውቅና መስጠቱ፣ እንዲሁም ዕድሜያቸው ከአምስት ዓመት በላይ ለሆኑ ሕፃናት ብቸኛ ሞግዚት ወይም አሳዳጊ አድርጎ መሰየሙ ለአብነት ይጠቀሳሉ፡፡ ፍርድ ቤቶች የቤት ውስጥ ጥቃትን ፍች ለማጽደቅ በቂ ምክንያት አድርገው አያዩም፡፡ የቱንም ያህል ረጅም ዓመታት ያስቆጠረ ትዳር ቢሆን፣ ብዙ ልጆች ቢወልዱም፣ በርካታ ንብረቶችን በጋራ ቢያፈሩም፣ ትዳር የሚፈርስበት ሁኔታ ከተፈጠረ ሕጉ ለሴቶች ያስቀመጠው ለሦስት ወራት ብቻ የገንዘብ ድጋፍ የማግኘት መብትን ነው፡፡ በልማዳዊ ሕግ ለተፈፀመ ጋብቻ የሚሰጠው የሕግ እውቅና ውሱን ነው፡፡ ልማዳዊ ሕግ ባል ለቤተሰቡ የገንዘብ ድጋፍ እንዲያደርግ የሚያስገድደው የሕግ አግባብ ስለሌለው ሴቶችና ሕፃናት አንዳንዴ ችግር ላይ የወደቁበት ሁኔታ ተፈጥሯል፡፡ ምንም እንኳ በመደበኛ የሕግ ሥርዓት ውስጥ ዘመናዊ ሕጎች ቢኖሩም፣ ባህላዊ ፍርድ ቤቶች ኢኮኖሚያዊ እና ማህበራዊ ግንኙነቶችን በተመለከተ ባህላዊ ሕጎችን መተግበር ቀጥለዋል፡፡

ሕገ-መንግሥቱ መሬት የመንግሥት እንደሆነ ደንግጓል፡፡ ወንዶችም ሆኑ ሴቶች በውርስ ሊያስተላልፉ የሚችሉት በመሬት የመጠቀም መብቶች አሏቸው፡፡ የመሬት ሕግ ከክልል ክልል ይለያያል፡፡ ሁሉም የፌደራል እና የክልል የመሬት ሕጎች ሴቶች የመንግሥት መሬት ማግኘት እንዲችሉ ሁኔታዎችን

አመቻችተዋል። የውርስ ሕጎችም ባሎቻቸው የሞቱባቸው ሴቶች በትዳር አብረው ሲኖሩ ያፈሩትን የጋራ ንብረት መውረስ እንደሚችሉ ደንግገዋል።

በከተሞች አካባቢ ሴቶች ሥራ የማግኘት ዕድላቸው ከወንዶች አንፃር አናሳ ሲሆን፣ ባሉት የሥራ ዘርፎችም ለተመሳሳይ ሥራዎች ተመሳሳይ ክፍያ አይሰጣቸውም ነበር። በተጨማሪም ባለው ልማዳዊ አስተሳሰብ ወይም አመለካከት የተነሳ ሴቶች የትምህርት ደረጃቸው ዝቅተኛ በመሆኑ በጥሩ ደመወዝ እንዳይቀጠሩ፣ ብድር እንዳያገኙና የራሳቸውን የንግድ ሥራ እንዳይሰሩ ወይም እንዳይመሩ ተገድበዋል።

የትምህርት ሚኒስቴር እንዳመለከተው፣ በመጀመርያ ዲግሪ እና በድህረ-ምረቃ ትምህርት የሴቶች ተሳትፎ እያደገ የመሄድ ዝንባሌውን በመቀጠል በ2002/03 የትምህርት ዘመን ከነበረበት 123,706፣ በ2003/04 የትምህርት ዘመን ወደ 144,286 አድጓል።

**ሕፃናት**

**<u>የልደት ምዝገባ</u>፡** ሕጻናት ዜግነታቸውን የሚያገኙት ከወላጆቻቸው ነው። ሁሉም ሕፃናት ሲወለዱ መመዝገብ እንዳለባቸው ሕጉ ይደነግጋል። በተግባር እንደታየው ግን በሆስፒታል የተወለዱ ሕፃናት ሲመዘገቡ፣ ከሆስፒታል ውጪ የተወለዱ አብዛኞቹ ሕፃናት ግን አልተመዘገቡም። ብዙዎቹ ሕፃናት በተለይ በገጠር አካባቢ የሚወለዱት በመኖሪያ ቤት ውስጥ ነው።

**<u>ትምህርት</u>፡** በፖሊሲ ደረጃ የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ዕድሜያቸው ለትምህርት ለደረሱ ሕፃናት በነፃ እንደሚሰጥ ተደንግጓል። ሆኖም ግን ወጣቶችን ተቀብለው የሚያስተምሩ በቂ ትምህርት ቤቶች በተለይ በገጠር አካባቢዎች የሉም። ለትምህርት ቤት የሚያስፈልጉ ቁሳቁሶች ዋጋ ከፍተኛ በመሆኑ ብዙ ቤተሰቦች ልጆቻቸውን ወደ ትምህርት ቤት እንዳይልኩ መሰናክል ሆኗል። የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ግዴታ እንደሆነ የሚደነግግ ሕግም አልነበረም። ትምህርት ለመከታተል የተመዘገቡ ተማሪዎች ቁጥር ከሰለጠኑ መምህራን ቁጥር በላይበከፍተኛ ፍጥነት አድጓል።

**<u>የሕፃናት ጥቃት</u>፡** በሕፃናት ላይ በርካታ ጥቃቶች ተፈጽመዋል። በሚያዝያ ወር አንዲት ሕፃን በሴት አሳዳጊዋ የደረሰባትን ተደጋጋሚ ጥቃት የሚያሳይ ቪዲዮ በዩትዩብ (YouTube) በስፋት የተሰራጨ ሲሆን ይህም የሕፃናት ጥቃት ተከላካይ ኢትዮጵያውያን የሚል የፌስቡክ ቡድን እንዲቋቋም አስችሏል። የአፍሪካ ሕፃናት ፖሊሲ መድረክ በ2001 ያካሄደው ጥናት እንደሚያሳየው በሕግ አካላት መካከል ባለው የሕግ አተረጓጎም ልዩነት፣ እንዲሁም በአጥፊዎች የዋስ መብት መጠበቅ ወሲባዊ ጥቃቶችን የሚፈጽሙ ጥፋተኞችን መክሰስ አስቸጋሪ ሆኗል። የዋስ መብቱ የተጠበቀለት ጥፋተኛ ብዙ ጊዜ ይሸሻል ወይም የጥቃቱን ተጎጂ ወይም ቤተሰብ በማስፈራራት ክሱ እንዲነሳ ያስገድዳል። በዚሁ

ዓመት ለሕፃናት ተስማሚ የሆኑ በተለይም በሕፃናት እና በሴቶች ላይ የሚደርሰውን ጥቃት የሚዳኙ ችሎቶች ተቋቁመዋል፡፡

<u>**የሕፃናት ጋብቻ**</u>፡ ሕጋዊ ጋብቻ ለመፈፀም ወንዶችና ሴቶች ዕድሜያቸው 18 ዓመት መድረስ እንደሚገባው ሕጉ ይደነግጋል፣ ይሁን እንጂ ህጉ ወጥነት ባለው ሁኔታ ተግባራዊ አልተደረገም፡፡ አንዳንድ በገጠር የሚገኙ ቤተሰቦች ህጉ ስለመኖሩ ግንዛቤ አልነበራቸውም፡፡ በበርካታ ክልሎች በዕድሜ ጠና ያሉ ወንዶች ወጣት ልጃገረዶችን የማግባት ሁኔታ ያለ ሲሆን፤በዚህ ልማዳዊ ድርጊት ላይም ከፍተኛ ተቃውሞና ትችት እንደቀጠለ ነው፡፡

በሥነ-ሕዝብና ጤና ጥናት መሰረት ዕድሜያቸው ከ 20-49 የሆኑ ሴቶች አማካይ የመጀመሪያ ጋብቻ የሚፈጽሙብት ዕድሜ 17.1 እንደሆነ ያመለክታል፡፡ የመጀመሪያ ጋብቻ የሚፈጸምበት ዕድሜ ከፍ እያለ መጥተል፡፡ ዕድሜያቸው ከ20-24 በሆኑ ሴቶች ላይ በ1998 በተደረገው ጥናት አማካይ የመጀመሪያ ጋብቻ የሚፈጸምበት ዕድሜ 16.5 ሲሆን ፤ በጥናቱ ከተካተቱና ዕድሜያቸው ከ45-49 ከሆኑ ሴቶች መካከል 39 በመቶ የሚሆኑት በ15 ዓመታቸው ጋብቻ ፈጽመዋል፡፡ ዕድሜያቸው ከ15-19 ከሆኑ ወጣት ሴቶች መካከል 8 በመቶ ያህሉ ብቻ አግብተዋል፡፡

ለአቅመ ሄዋን ያልደረሱ ሕፃናት በተለይ በአማራና ትግራይ ክልሎች በሰባት ዓመታቸው ሳይቀር ጋብቻ ፈጽመዋል፡፡ የሕፃናት ጋብቻ በአማራ ክልል በስፋት የሚስተዋል ሲሆን ፤ በክልሉ በተደረገ የሥነ-ሕዝብና ጤና ጥናት በ1997 ዓ.ም 14.7 ዓመት የነበረው አማካይ የመጀመሪያ ጋብቻ የሚፈጸምበት ዕድሜ በ 2003 ወደ 15.1 ዓመት ከፍ ብሏል፡፡ የአማራ እና በመጠኑም ቢሆን የትግራይ ክልላዊ መንግስታት ያለዕድሜ ጋብቻን በተመለከተ ወጣት ሴቶችን ለማስተማር ሞክረዋል፡፡

<u>**ጎጂ ልማዳዊ ድርጊቶች**</u>፡ በወጣት ሴቶች ላይ የሚፈጸም ማህበራዊ ጥቃት አስቸጋሪነቱ እንደቀጠለ ነው፡፡የሴት ልጅ ግርዛት፣ ያለዕድሜ ጋብቻ፣ በጠለፋ ማግባት፣ የምግብና የሥራ ክልከላዎች በወጣት ሴቶች ላይ ከሚፈጸሙ ጎጂ ልማዳዊ ድርጊቶች መካከል ጥቂቶቹ ነበሩ፡፡ የአፍሪካ ሕፃናት ፖሊሲ መድረክ እ.ኤ.አ በ2006 ያካሄደው ጥናት እንደሚጠቁመው በጥናቱ ከተካተቱት ወጣት ሴቶች መካከል 68.5 በመቶ የሚሆኑት ወሲባዊ ጥቃት የደረሰባቸው ሲሆን፣ 84 ከመቶ የሚሆኑት አካላዊ ጥቃት ደርሶባቸዋል፡፡

አብዛኛዎቹ ወጣት ሴቶች በአንድ ወይም በሌላ መንገድ ለግርዛት ተዳርገዋል፡፡ ከጠቅላላው ሕዝብ 15 በመቶ ያህሉ በሚኖርበት የከተማ አካባቢ የግርዛት ድርጊት ዝቅተኛ ነው፡፡ ወጣት ሴቶች በተወለዱ በሰባት ቀናቸው በተለይ ቂንጥር (Clitoris) የሚባለውን የብልታቸው ክፍል በግርዛት ሳቢያ እንዲያጡ ተደርጓል፡፡ ለአቅመ ሄዋን ሲደርሱ ደግሞ እጅግ አደገኛ የሆነው የግርዛት ዓይነት ተፈጽሞባቸዋል፡፡

የኖርዌይ ሕፃናት አድን ድርጅት ባደረገው የገንዘብ ድጋፍ በ2000 በተካሄደ ጥናት መሠረት ባለፉት አሥር ዓመታት የሴቶች ግርዛት በሀገር አቀፍ ደረጃ 24 በመቶ ቀንሷል። ለዚህም በሀገሪቱ የተካሄደው ጠንካራ ፀረ የሴት ልጅ ግርዛት ዘመቻ በተወሰነ ደረጃ አስተዋጽኦ አድርጓል። በዚህ አመት ዘመቻው በደቡብ ብሔር ብሔረሰቦችና ሕዝቦች እንዲሁም በአፋር ክልል ውጤት ያመጣ ቢሆንም፤ እጅግ አደገኛ የሆነው የግርዛት ዓይነት በደቡብ ብሔር ብሔረሰቦችና ሕዝቦች በአብዛኛው ወጣት ሴቶች ላይ መፈጸሙን  የታመኑ ምንጮች ዘግበዋል። የወንጀለኛ መቅጫ ሕጉ ‹ክሊቶሪስ› የተባለውን የብልት ክፍል በማንሳት ግርዛት በሚፈጽሙ ባህላዊ ገራዦች ላይ ቢያንስ የሦስት ወር እስራት፣ ወይም የ500 ብር (28 የአሜሪካ ዶላር) የገንዘብ መቀጮ ይጥላል። እጅግ አደገኛ በሆነ ሁኔታ ግርዛት የሚያከናውኑትን ደግሞ ከአምስት እስከ አስር ዓመት በሚደርስ እስራት ይቀጣል። ነገር ግን የሴት ልጅ ግርዛትን በተመለከተ አንድም ክስ አልቀረበም። መንግሥት የሴት ልጅ ግርዛትን ለማስቆም በመንግሥት ትምህርት ቤቶች፣ በጤና ኤክስቴንሽን መርኃ ግብሮች እና በመገናኛ ብዙኃን ትምህርት ሰጥቷል።

<u>**የሕፃናት ወሲባዊ ብዝበዛ**</u>፡ በፈቃደኝነት ወሲባዊ ግንኙነት ለመፈፀም ዝቅተኛው የዕድሜ ገደብ 18 ዓመት ቢሆንም፣ ሕጉ ተፈጻሚ አልሆነም። ለአቅመ አዳም/ሄዋን ካልደረሰ/ች ህፃን ጋር ወሲባዊ ግንኙነት መፈጸም ከ3 እስከ 15 ዓመት የሚደርስ ቅጣት እንደሚያስከትል በሕግ ተደንግጓል።

ለአቅመ አዳም/ሄዋን ባልደረሱ ሕፃናት ላይ አስጸያፊ ወሲባዊ ደርጊት ሲፈፀም የሚያሳዩ ምስሎችን የሰራጨ ሰው በአንድ ዓመት እስራትና በ10,000 ብር (550 የአሜሪካን ዶላር) የገንዘብ መቀጮ እንደሚቀጣ ተደንግጓል። በተጨማሪም ሕጉ ትርፍ ለማግኘት ሲባል ለአቅመ-አዳም/ሄዋን ያልደረሱ ሕፃናትን ለወሲብ ድርጊት ማሰማራትና የወሲብ ንግድ እንዲጀምሩ መገፋፋትን ይከለክላል። ነገር ግን የሕፃናት ወሲባዊ ብዝበዛ፣ በተለይ በከተሞች አካባቢ ቀጥሏል። ዕድሜያቸው 11 ዓመት የሆኑ ወጣት ሴቶች ለወሲብ ንግድ እንዲሰማሩ መመልመላቸው ተነግሯል። ከእነዚህ ወጣት ሴቶች ጋር ግብረ ሥጋ ግንኙነት ለመፈጸም የሚፈልጉት ወጣት ሴቶቹ በግብረ ሥጋ ግንኙነት ከሚተላለፉ በሽታዎች ነፃ ናቸው የሚል እምነት ስለነበራቸው ነበር። ወጣት ሴቶችን ከገጠር ወደ ከተማ በማስኮብለል በሆቴሎች እና በመዝናኛ ስፍራዎች የወሲብ ንግድ እንዲሰሩ ይደረጋል። አንዳንድ ወጣት ሴቶች በራሳቸው ቤተሰቦች ተገፋፍተው ወደ ወሲብ ንግድ እንደገቡ ሪፖርቶች አመልክተዋል።

<u>**ሕፃናትን መግደል**</u>፡ በኋላቀር እና ባዕድ አምልኮ ምክንያት ሕፃናትን መግደል በደቡብ ኦሞ ሸለቆ አካባቢ ባሉ ጎሳዎች መተግበሩ ቀጥሏል። የአካባቢ መስተዳድሮች ድርጊቱን ለማስቆም ማኅበረሰቡን ለማስተማር ጥረት አድርገዋል።

<u>**የሕፃናት መፈናቀል**</u>፡ የሠራተኛና ማኅበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር የ2002 ሪፖርት እንደሚያመለክተው፣ በግምት 150,000 ሕፃናት በጎዳና ላይ የሚኖሩ ሲሆን፣ ከእነዚህ ውስጥ 60,000 የሚሆኑት በአዲስ

አበባ ይገኛሉ። እንደ ሚኒስቴሩ ሪፖርት ከሆነ በወላጆች ህመም እንዲሁም በቤተሰቡ የገቢ አነስተኛነት ምክንያት ቤተሰቦች ልጆቻቸውን መርዳት አለመቻላቸው ችግሩን አባብሶታል። እነዚህ ሕፃናት በቡድን ሆነው ይለምናሉ፤ ወይም መደበኛ ያልሆነ ሥራ ይሠራሉ። በ2002 ፖፑሌሽን ካውንስል ያንግ አደልትስ (Population Council Young Adults) ባደረገው ጥናት በጎዳና ላይ ከሚኖሩና ከሚሰሩ ወንዶች ልጆች መካከል 82.3 በመቶ የሚሆኑት ትምህርት ይማሩ ነበር ወይንም ለመማር ተመዝግበዋል! 26.4 በመቶው አንዱን ወላጃቸውን ያጡ ሲሆን፤47.2 በመቶ የሚሆኑት ሁለቱንም ወላጆቻቸውን ያጡ ናቸው። 72 በመቶ የሚሆኑት በሕይወታቸው በአንድ ወቅት በክፍያ ሥራ ላይ ተሰማርተዋል።ወላጅ አልባ ሕፃናትን የሚንከባከቡ መንግሥታዊና የግል ድርጅቶች በጎዳና ላይ ያሉ ሕፃናትን መንከባከብ አልቻሉም።

__በተቋማት የሚረዱ ሕፃናት__፡ በማዕከላዊ ስታቲስቲክስ ኤጀንሲ የ2002 ሪፖርት መሠረት በሀገሪቱ ውስጥ በግምት 5.4 ሚሊዮን ወላጅ አልባ ሕፃናት ይገኛሉ። አብዛኛዎቹ ከዘመዶቻቸው ጋር የሚኖሩ ናቸው። በመንግሥት የሚተዳደሩ የወላጅ አልባ ሕፃናት ማሳደጊያ ተቋማት የተጨናነቁ እና ንጽህና የጎደላቸው ነበሩ። ከገንዘብ እጥረት የተነሳ ሆስፒታሎችና የሕፃናት ማሳደጊያ ተቋማት ለወላጅ አልባ ሕፃናት ትኩረት አልሰጡም። በደቡብ ብሔር ብሔረሰቦች ክልል በርካታ ህፃናት በቂ የጤና ክብካቤ ባለማግኘታቸው ለሞት ተዳርገዋል።

__ዓለም አቀፍ የሕፃናት ጠለፋ__፡ ሀገሪቱ የ1972ቱ ዓለም አቀፍ የሕፃናት ጠለፋ የሲቪል ገጽታዎች የሔግ ስምምነት አባል አይደለችም።

**ፀረ-ሴማዊነት**

የአይሁድ ማኅበረሰብ አባላት ቁጥር በግምት 2000 ነበረ። ፀረ-ሴማዊ የሆኑ ድርጊቶችን የተመለከቱ ሪፖርቶች አልነበሩም።

**ሕገ-ወጥ የሰዎች ዝውውር**

የአሜሪካ የውጭ ጉዳይ መሥሪያ ቤትን ሕገ-ወጥ የሰዎች ዝውውር ሪፖርትን በwww.state.gov/j/tip ድረ-ገጽ ላይ ይመልከቱ።

**አካል ጉዳተኞች**

ሕገ መንግሥቱ ለአካል ጉዳተኞች እኩል መብት አይሰጥም። ነገር ግን የአካልና የአእምሮ ጉዳተኞች በሥራ ቅጥር ወቅትና ህንፃዎችን ተደራሽ በማድረግ ረገድ መድልዎ እንዳይደረግባቸው የሚከለክሉ ሁለት ሕጎች አሉ። መስማት የተሳናቸው ሰዎች መኪና እንዳያሽከረክሩ ሕጉ ይከለክላል።

የአካል ጉዳተኞች ተቀጥረው የመሥራት መብት አዋጅ በቅጥር ወቅት አካል ጉዳትን መሠረት ያደረገ መድልዎን ይከለክላል፡፡ በተጨማሪም ቀጣሪ መሥሪያ ቤቶች ለአካል ጉዳተኞቸ አስፈላጊ የሥራና የሥልጠና ሁኔታዎችን ማመቻቸት እንደሚገባቸው ይደነግጋል፡፡ በሴት የአካል ጉዳተኞቸ ላይ ያለውን ተጨማሪ ጫናም ሕጉ ከግምት አስገብቷል፡፡ መንግሥት ሕጉን ለማስፈጸም የተወሰኑ እርምጃዎችን ወስዷል፡፡ ለምሳሌ ያህል መስማት ለተሳናቸው የመንግሥት ሠራተኞች አስተርጓሚዎችን መድቧል፡፡

ምንም እንኳ የህንፃዎችን የተደራሽነት ደረጃ የተመለከቱ ዝርዝር ደንቦች ባይወጡም፣ የኢትዮጵያ የህንፃ አዋጅ የሚገነቡ ህንፃዎች የመፀዳጃ ክፍሎች ለአካል ጉዳተኞች ተስማሚ በሆነ መልኩ እንዲገነቡ ይደነግጋል፡፡ ይሁን እንጂ ህንፃዎችና የመጸዳጃ ክፍሎች በአብዛኛው ለአካል ጉዳተኞች ተስማሚ አልነበሩም፡፡ የቤት አከራዮች አካል ጉዳተኞች የመጀመሪያ ወለል ላይ እንዲከራዩ ማስመረጥ ይጠበቅባቸዋል፡፡ ይህም ተግባራዊ ሆኗል፡፡

በትምህርትና በቅጥር ሴት የአካል ጉዳተኞች ከወንዶቹ የበለጠ ተጎጂዎች ነበሩ፡፡ በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ በ2000 የተካሄደ ጥናት ሴት የአካል ጉዳተኞቸ ከወንድ የአካል ጉዳተኞች ይልቅ በቤት ውስጥ ሥራ ጫና እንደሚደርስባቸው አመልክቷል፡፡ ፖፑሌሽን ካውንስል (Population Council) በ2002 በወጣቶች ላይ ባደረገው ጥናት ወጣት ወንድ የአካል ጉዳተኞች የትምህርት ተሳትፎ የአካል ጉዳት ከሌለባቸው ወጣት ወንዶች ዝቅተኛ ነበር፡፡ በጥናቱ መሰረት የአካል ጉዳተኛ ወጣት ሴቶች የትምህርት ተሳታትፎ ከወንድ አካል ጉዳተኞች ተሳትፎ ያነሰ ነበር፡፡ የአካል ጉዳት ካለባቸው ወጣት ሴቶች መካከል 23 በመቶ የሚሆኑት ትምርት ቤት ገብተዋል፡፡ በሌላ በኩል የአካል ጉዳት ከሌለባቸው ወጣት ሴቶች መካከል 48 በመቶ እንዲሁም 55 በመቶ ወንዶች ትምህርት ቤት ገብተዋል፡፡ በጥቅል ሲታይ ጥናቱ ካካተታቸው የአካል ጉዳትኛ ወጣቶች መካከል 47.5 በመቶ በጉዳት ሳቢያ ትምህርት ቤት መግባት አልቻሉም፡፡ የአካል ጉዳተኛ ወጣት ሴቶች የአካል ጉዳት ከሌለባቸው ወጣት ሴቶች ይበልጥ ለአካላዊና ወሲባዊ ጥቃት ተጋልጠው ነበር፡፡ ወሲብ ከፈጸሙ የአካል ጉዳተኛ ወጣት ሴቶች  መካከል 33 በመቶ ያህሉ የግዳጅ ወሲብ ተፈጽሞባቸዋል፡፡ በጥናቱ መሰረት ከወንድ የአካል ጉዳተኞች መካከል 6 በመቶ ያህሉ ድብደባ ተፈጽሞባቸውል፡፡ ጥናቱ ካካተታቸው ጤናማ ወጣቶች  መካከል 2 በመቶ ያህሉ ድብደባ ተፈጽሞባቸውል፡፡

በርካታ መስማትና ማየት ለተሳናቸው አካል ጉዳተኞች የተቋቋሙ ትምህርት ቤቶች፣ እንዲሁም የአእምሮ ዕድገት ውሱንነት ችግር ላለባቸው ሕፃናትና ወጣቶች የሥልጠና ማዕከላት ተዘጋጅተዋል፡፡ ከዘጠኙ የክልል መንግሥታት በአምስቱ ሰው ሰራሽ የአካል ጉዳተኞች መርጃ መሳሪያዎች ማምረቻ ማዕከላት ነበሩ፡፡

ብሔራዊ ማየት የተሳናቸው ማህበር፣ ብሔራዊ መስማት የተሳናቸው ማኅበር እና ብሔራዊ የአካል ጉዳተኞች ማኅበርን የመሳሰሉ በርካታ ሀገር በቀል ተቋማት በበጎ አድራጎት ድርጅቶች እና ማኅበራት ህግ ምክንያት አሉታዊ ተጽዕኖ ደርሶባቸዋል፡፡

**ብሔር/ዘር/ እናሣ ኅሳዎች ብሔረሰቦች**

በሀገሪቱ ከ80 በላይ ብሔር/ብሔረሰቦች አሉ፡፡ ከጠቅላላው ህዝብ ቁጥር ከፍተኛውን ቁጥር (35%) የያዘው የኦሮሞ ብሔረሰብ ነው፡፡ የፌልራል ሥርዓቱ ድንበሮችን ዋና ዋና ብሔረሰቦችን አሰፋፈር መሠረት በማድረግ የለየ ነው፡፡ አብዛኛዎቹ የፖለቲካ ፓርቲዎች በዋናነት ብሔረሰብን መሠረት ያደረጉ ነበሩ፡፡

በዓመቱ ውስጥ በብሔረሰቦች መካከል በተነሳ ግጭት ከ100-150 ሰዎች ለሞት ተዳርገዋል ከአካባቢያቸውም ተፈናቅለዋል፡፡ በብሔረሰቦች መካከል ለሚነሳው ግጭት የውሃ እጥረት አስተዋጽኦ አድርጓል፡፡

መጋቢት 20 ታጣቂዎች በሕዝብ ማመላለሻ አውቶቡስ ላይ በጋምቤላ ክልል ዋና ከተማ አቅራቢያ ቦንጋ በታባለ አካባቢ የደፈጣ ጥቃት ፈጽመዋል፡፡ ታጣቂዎቹ አውቶቡሱን በማስቆምና ተሳፋሪዎች እንዲወርዱ በማስገደድ “ደገኛ” ያሏቸውን የአማራና የትግራይ ብሄር አባላትን ከአካባቢው ነዋሪዎች በመለየት “ደገኛ” ብለው የፈረጇቸውን 21 ሰዎች ሲገድሉ 9 አቁስለዋል፡፡

በዓመቱ መጀመሪያ ላይ ኢትዮጵያና ኬንያ በሚዋሰኑበት የሞያሌ ከተማ አካባቢ በተቀናቃኝ ቡድኖች መካከል የነበረውን የቆየ የብሔር ውጥረት ወደ ከፋ ደረጃ ያሸጋገረ ግጭት ተከስተል፡፡ በኬንያ ድንበር አካባቢ በተፈጸመ ተከታታይ የበቀል እርምጃም በሺህ የሚቆጠሩ የቦረና እና ገርባ ጎሳ አባላት ወደ ኢትዮጵያ ለመሰደድ ተገደዋል፡፡ በሐምሌ ወር የቦረና ፣ የገርባና ጋሪ ጎሳ አባላት በኢትዮጵያ ድንበር በኩል ተጋጭተው 85 ሰዎች ሲሞቱ በአስር ሺህ የሚቆጠሩ ሰዎች ተፈናቅለዋል፡፡

**ማኅበረሰባዊ በደሎች፣ መድልዎ፣ እና ጾታዊ ማንነትን እና ወሲባዊ ዝንባሌን መሠረት ያደረጉ ጥቃቶች**

በሀገሪቱ ሕግ መሠረት በፈቃደኝነት የሚፈፀም የተመሳሳይ ጾታ ግንኙነት በእስራት የሚያስቀጣ ወንጀል ነው፡፡ እንዲህ ዓይነት ዝንባሌ ባላቸው ወንዶች እና ሴቶች ላይ ጥቃቶች መፈፀማቸውን የሚገልጹ አንዳንድ ሪፖርቶች ነበሩ፡፡ ሆኖም እነዚህን ጥቃቶች ከፍርሃት የተነሳ ወይም በቀል፣ መድልዎና መገለል ይደርስብናል በሚል ስጋት ተጎጂዎች ሪፖርት አላደረጉም፡፡ በተመሳሳይ ፆታ መካከል የሚደረግ የወሲብ ግንኙነት በሀገሪቱ ህገ-ወጥ በመሆኑና ሊደርስባቸው የሚችለውን መገለል በማሰብ መሰል

ወሲባዊ ዝንባሌ ያላቸው ራሳቸውን ይፋ አያደርጉም። የተመሳሳይ ጾታ ግንኙነት የሚፈጽሙ ማኅበረሰብ አባላት መብት ተሟጋቾች አልፎ አልፎ  እስር ምርመራና አካላዊ ጥቃት ተፈጽሞባቸዋል።

አዲስ አበባ የሚገኘው የኤድስ መረጃ ማዕከል የተመሳሳይ ጾታ ዝንባሌ ያላቸው ሴቶችና በርካታ ወንዶች ማንነታቸውን በመግለጽ የሚደርስባቸውን መገለል ለመሸሽ እንዴት ባህሪያቸውን መቀየር እንደሚችሉ ምክር በመሻት ስልክ የደወሉ እንደነበሩ  ሪፖርት አድርጓል። በርካታ ወንድ ግብረ-ሰዶማውያን ስጋት፣ ግራ መጋባት፣ የማነንት ቀውስ፣ ድብርት፣ ራስን ማግለል፣ የሃይማኖት ግጭት እና ራስን የማጥፋት ስሜት ችግሮች እንደደረሱባቸው ተናግረዋል።

**ሌሎች ማህበረሰባዊ ሁከቶች ወይም መድሎዎች**

ከኤች.አይ.ቪ/ኤድስ ጋር የሚኖሩ ወይም በበሽታው የተጎዱ ዜጎች በትምህርት፣ በሥራ እንዲሁም በማህበራዊ ኑሮ መድልዎ እና መገለል ደርሶባቸዋል። ይህን በተመለከተ የተለያዩ መረጃዎች ቢኖሩም የችግሩን ስፋት የሚያሳይ ስታቲስቲካዊ መረጃ አልተገኘም።

## ክፍል 7. የሠራተኛ መብቶች

### *ሀ. የመደራጀት ነፃነት እና በህብረት የመደራደር መብት*

ሠራተኞች በሠራተኛ ማህበራት እንዲደራጁ ፣ በማህበራት እንዲታቀፉ ፣ ህጋዊ የስራ ማቆም አድማ እንዲያደርጉ ፣ በህብረት እንዲደራደሩ  ሕገ-መንግስቱና ሕጉ ይፈቅዳል። እነዚህ መብቶች አገሪቱ ባወታቻቸው ሌሎች ህጎች ምክንያት ተግባራዊ እንዳይሆኑ ተገድበዋል። የ1995 የአሰርና ሠራተኛ አዋጅ በተለይ በሥራ አስኪያጅ ደረጃ ያሉ ተቀጣሪዎችን፣ መምህራንን፣ ዳኞችን፣ ጠበቃዎችን እና የደህንነት አገልግሎት ሠራተኞችን ጨምሮ የመንግሥት ሠራተኞችን ሕጉ እንደማይመለከታቸው ይገልጻል።

ዓለም አቀፍ የሥራ ድርጅት የበጎ አድራጎትና የሲቪክ ማህበራት ህግ በሰራተኞች የመደራጀት የመመዘገብ ውስጣዊ አስተዳደርና ማኅበረን የማፍረስ መብት በተመለከተ መንግስት ጣልቃ እንዲገባ አስችሎታል የሚል ሪፖርት አቅርቧል።

አንድን ማህበር ለመመሥረት ቢያንስ አሥር ዓባላት ያስፈልጋሉ። ምንም እንኳ ሁሉም ማህበራት የመመዝገበ መብት እንዳላቸው ሕጉ ቢደነግግም የተቀመጡትን መስፈርቶች ያላሟሉ ማህበራትን መንግሥት ላይመዘግብ ይችላል። አንድ የሠራተኛ ማኅበር ግልጽ በሆነ ሁኔታ የለቲካ እንቅስቃሴ ማራመድ እንደሌለበት ህጉ ይደነግጋል። ወቅት ጠብቀው እንዲሁም በትርፍ ሰዓት የሚሰሩ የግብርና ሠራተኞች የሠራተኛ ማህበር ማቋቋም እንደማይችሉ ተደንግጓል። አሰሪዎች በሰራተኛ ማህበራት ላይ

መድልዎ እንዳይፈጽሙና በሠራተኛ ማህበር ውስጥ በመሳተፉ የተባረረ ሠራተኛ ቢኖር ወደ ሥራው እንዲመለስ ህጉ ያስገድዳል፡፡

የህብረት ድርድር መብት እንዲከበር ሕጉ ጥበቃ ቢያድርግም ይህ መብት በከፍተኛ ደረጃ ተገድቢል፡፡ የሕብረት ሥምምነትን ለማሻሻል ወይም በአዲስ ለመተካት የሚደረግ ድርድር ሥምምነቱ ከማብቃቱ ከ3 ወራት በፊት ሊጠናቀቅ ይገባል፡፡ ይህ ካልሆነ የደመወዝና የጥቅማ ጥቅም ህጉ ተግባራዊ ሊሆን አይችልም፡፡ የመንግስት ሠራተኞች የሕዝብ ትምህርት ቤቶች መምህራንን ጨምሮ የሙያ ማኅበራትን መመሰርት እንዲሁም አባል መሆን ይችላሉ፡፡ ነገር ግን ለተሻለ ክፍያና የስራ ሁኔታ መደራደር አይችሉም፡፡ በተጨማሪም የመንግስት ዘርፍ የአሰርና ሠራተኛ ዘርፍ ዳኝነት አፈጻጸም ከግሉ ዘርፍ ይልቅ የተወሳሰበ ነበር፡፡

ምንም እንኳን ሠራተኞች መብታቸውን ለማስጠበቅ የሥራ ማቆም አድማ ማድረግ እንደሚችሉ በህገ መንግሥቱና በህግ የተደነገገ ቢሆንም የሥራ ማቆም አድማን ማካሄድ አስቸጋሪ እንዲሆን የሚያደርጉ ውስብስብና ጊዜ ወሳጅ ሥነ-ሥርዓቶች ነበሩ፡፡ ለምሳሌ የሥራ ማቆም አድማ ከመደረጉ ቢያንስ ከ30 ቀናት በፊት ለሚመለከተው አካል ማሳወቅ ይኖርባቸዋል፡፡ ተጎጂ ነን ባይ ሠራተኞች የሥራ ማቆም አድማ ከማድረጋቸው በፊት ከቀጣሪው መሥሪያ ቤት ጋር በድርድር ጉዳዩን እንዲፈቱ ህጉ ይጠይቃል፡፡ እነዚህ ህጎች ቀጣሪውም ሠራተኛውን ከሥራው በማገድ ድርድር እንዲራዘም በር ይከፍታል፡፡ የሥራ ማቆም አድማ ለማድረግ የሠራተኛውን 2/3ኛ ድጋፍ ማግኘት ያስፈልጋል፡፡ ጉዳዩ ወደ ፍርድ ቤት ወይም የሠራተኛ ማህበርን ለሚመለከት ቦርድ ካልቀረበ ሠራተኛው ከላይ የተጠቀሱትን አማራጮች ሳይከተል የሥራ ማቆም አድማ የማድረግ መብት አለው፡፡ ይህ የሚሆነው ግን ቢያንስ ከአስር ቀናት በፊት ለሌላኛው ወገንና ለሠራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር ሲያሳውቅ እንዲሁም ጉዳዩን በድርድር ለመፍታት ጥረት ሲያደርግ ነው፡፡

በአየር ትራንስፖርት፣ በከተማ አውቶቡስ፣ በኤሌክትሪክ ኃይል አቅርቦት፣ በነዳጅ ማደያ፣ በሆስፒታልና መድሃኒት ቤቶች፣ በእሳት አደጋ መቆጣጠሪያ፣ በቴሌኮሙኒኬሽን እና በከተማ ጽዳት በመሳሰሉት እጅግ ጠቃሚ ማህበራዊ አገልግሎት በሚሰጡ ተቋማት የሚሠሩ ሠራተኞች የሥራ ማቆም አድማ ማድረግ እንደማይችሉ ይደነግጋል፡፡ ነገር ግን ከላይ በተዘረዘሩት የሥራ ዘርፎች ILO ጠቃሚ ማህበራዊ አገልግሎት ይሰጣሉ ብሎ ካወጣቸው ዘርፎች በላይ ናቸው፡፡ አድማ ባደረጉ ሠራተኞች ላይ የሚደረግ የበቀል እርምጃን ህጉ ይከለክላል፡፡ ሆኖም ግን በህገወጥ የሥራ ማቆም አድማ ላይ የሚሳተፉ ማኅበራትና ሠራተኞች በፍትሐብሔር ወይም በወንጀለኛ ህግ ሊጠየቁ እንደሚችል ህጉ ይደነግጋል፡፡ እጅግ ጠቃሚ ማህበራዊ አገልግሎት በሚሰጡ ዘርፎች ውስጥ የሚሰሩ ሠራተኞች የሥራ ማቆም አድማ እንዲያደርጉ ያስተባበሩ የሠራተኛ ማኅበራት እንዲፈርሱ ሊወሰን ይችላል፡፡

መደበኛ ባልሆነው የስራ ዘርፍ የተሰማሩ ሠራተኞች በአሰሪና ሰራተኛ ህግ መሰረት በማኅበር ሊደራጁ አይችሉም፡፡ እንዲሁም የሠራተኛ ህግ ከለላ አይደረግላቸውም፡፡ በዓመቱ መንግስት ባጋጠመው የሰው ኃይል እጥረት ሳቢያ ህጎችን በሚፈለገው ደረጃ ተፈጻሚ ማድረግ አልቻለም፡፡ የፍትሕ ሂደት መዘግየትም ተስተውሏል፡፡

የመደራጀትና በህብረት የመደራደር መብት አልተከበሩም፡፡ ምንም እንኳ መንግስት ማህበራት እንዲደራጁ የፈቀደ ቢሆንም ዋነኞቹ የሰራተኛ ማኅበራት በመንግስት የተቀ.ቀ.ሙና በመንግስት ቁጥጥር ሥር የሚገኙ ናቸው፡፡ መንግስት ብሔራዊ የመምህራን ማኅበር ያቀረበውን የምዝገባ ጥያቄ በተመሳሳይ ሁኔታ የተቀ.ቀ.መ ማኅበር መኖሩን እንደምክንያት በማቅረብ ጥያቄውን ውድቅ አድርጓል፡፡

በ2003 ዓ.ም Educational International ለዓለም አቀፍ የሥራ ድርጅት ባቀረበው ሪፖርት መንግስት መብሔራዊ መምህራን ማኅበር አባላት ላይ የሚያደርገው ክትትልና ወከባ አባላቱን ለዘመናት ሲያገለግል የቆየውን ማኅበር ለቀው እንዲወጡ የሚያደርገው ማስፈራራት እንዳሳሰበው ገልጿል፡፡ በህዳር ወር ዓለም አቀፍ የሥራ ድርጅት በብሔራዊ መምህራን ማኅበር ላይ የሚፈጸመው የመደራጀት መብት ጥሰትና በማኅበር ውስጥ ጣልቃ መግባት ፤ ማስፈራራት ሠራተኞችን ከሥራ ማባረርና ማሰር እንዳሳሰበው ገልጿል፡፡ድርጅቱ መንግስት የብሔራዊ መምህራን ማኅበርን በአፋጣኝ እንዲመዘግብ ጠይቋል፡፡ በተጨማሪም የበጎ አድራጎት ድርጅቶችና ማኅበራት ህግ የሠራተኛ ማኅበራትን እንደማይመለከት እንዲያረጋገጥ ሲቪል ሰርቪሱን እንዲያስችልንና ሠራተኞች በመረጡት ማኅበር የመሳተፍ መብታቸውን እንዲያከብር የዓለም አቀፍ የሥራ ድርጅት አሳስቧል፡፡

ምንም እንኳን ዜጎች በህብረት የመደራደር መብትን በነፃነት እንዲተገብሩ መንግስት የፈቀደ ቢሆንም ተወካዮች የክፍያ ድርድር የሚያርጉት በተቀ.ም ደረጃ ብቻ ነበር፡፡ በመደበኛ የኢንዱስትሪ ዘርፍ ያሉ የሰራተኛ ማኅበራት የአሰሪና ሰራተኛ ህግን ሥራ ላይ ለማዋል የተወሰነ ጥረት አድርገዋል፡፡

ምንም እንኳን መንግስት በማህበራት ውስጥ የሚንቀሳቀሱ ሠራተኞችን የማግለል ሁኔታ የሚከለክል ቢሆንም በሠራተኛ ማህበር ውስጥ በንቃት የሚንቀሳቀሱ ሠራተኞችን ቀጣሪዎች ብዙ ጊዜ ከሥራ እንደሚያባርሯቸው ማህበራቱ ሪፖርት አድርገዋል፡፡ ለምሳሌ ያህል አዲስ አበባ የሚገኘው የባልቻ ሆስፒታል አስተዳደር በስራ ላይ ያለውን የሰራተኛ ማኅበር ለማዳካም በማሰብ ራሱ የሚቆጣጠረው የሰራተኛ ማኅበር ለማቀ.ቀ.ምና ሰራተኞችም የማህበሩ አባላት እንዲሆኑ ጥረት አድረጓል፡፡በኦሮሚያ ክልል ምስራቅ ወለጋ በሚገኝ የስኳር ማምረቻ ፋብሪካ የሰራተኛ ማኅበር ሊቀመንበር የሰራተኛውን መብት ለማስከበር ባደረገው እንቅስቃሴ ከስራ ተባሯል፡፡ ቻይናውን አሰሪዎች በአጠቃላይ ሰራተኞች ማኅበር እንዲያቋቁሙ አልፈቀዱም፡፡ አልፎ አልፎም የሰራተኛ ማኅበር መሪዎችን አዛውረዋል

አባርረዋል እንዲሁም የማኅበራት መሪዎችን በማስፈራራት ወይንም ጫና በመፍጠር ሥራ እንዲለቁ አድርገዋል።።

አለአግባብ የተባረሩ ሰራተኞች በፍርድ ቤት የሚመሰረቱት ክስ ፍርድ ቤቶች ባለባቸው የሥራ ጫና ምክንያት የሠራተኛ ጉዳዮች ፍርድ የሚያገኙት ከዓመታት በኂላ ነበር። በሠራተኛ ማኅበራት ውስጥ የሚንቀሳቀሱ ሠራተኞችን ያላግባብ ከሥራ ያባረሩ ቀጣሪዎች ሠራተኞቹን ወደ ሥራ ገበታቸው እንዲመልሷቸው  የታዘዙ ሲሆን በተግባርም ሠራተኞቹን ወደሥራ መልሰዋል። የሥራ ማቆም አድማ አድራጊዎች ላይ የሚወሰደውን የበቀል እርምጃ ህግ ቢከለክልም፣ አብዛኛዎቹ ሠራተኞች መንግሥት ይህን ከለላ ተፈፃሚ ያደርጋል የሚል እምነት አልነበራቸውም። በሀገሪቱ ካለው ከፍተኛ የሥራ አጥነት ችግርና በፍርድ ቤት የሠራተኛ ጉዳዮች የሚወስዱትን ረጅም ጊዜ ከግምት በማስገባት  አንዳንድ ሠራተኞች በሥራ ማቆም አድማዎች ወይም ሌሎች የሠራተኛ አድማዎች ላይ ለመሳተፍ እንደሚፈሩ የሠራተኛ ማህበራት ኃላፊዎች ተናግረዋል።

### ለ. የግዳጅ ሥራ ክልከላ

በሕፃናት ላይ የሚፈጸም የግዳጅ ሥራን ጨምሮ ሌሎቸ የግዳጅ ሥራዎችን ህጉ ይከለክላል። ነገር ግን ፍርድ ቤቶች የግዳጅ ሥራን እንደ ቅጣት እርምጃ እንዲወስዱ ይፈቅዳል። የግዳጅ ሥራ ክልከላን መንግሥት በበቂ ሁኔታ ተፈፃሚ አላደረገም።

የግዳጅ ሥራ በተግባር ተፈጽሟል። አዋቂዎችና ሕፃናት በጎዳና ላይ ንግድ ፣ በልመና ፣  በሽመና ሥራ ወይም በግብርና ሥራ በግድ እንዲሠማሩ ተደርገዋል። ከዚህ ሌላ ሕፃናት በግዳጅ የቤት ውስጥ ሠራተኛ ሆነው እንዲሰሩ ተደርገዋል። ሰዎች ለተበደሩት ገንዘብ ምትክ በግዳጅ የሽመናና የሸክላ ሥራዎችን በመሥራት፣ ከብት በማገድ፣ እንዲሁም ሌሎች የግብርና ሥራዎች በማከናወን ለአበዳሪዎች የሚሰሩበት ሁኔታ በተለይ በገጠር አካባቢዎች ተስተውሏል።

የአሜሪካ የውጭ ጉዳይ መሥሪያ ቤት በሕገ-ወጥ የሰዎች ዝውውር ላይ ያወጣውን ሪፖርት በwww.state.gov/j/tip ላይ ይመልከቱ።

### ሐ. የሕፃናት ጉልበት ብዝበዛና የሥራ ቅጥር ዝቅተኛ ዕድሜ

ለቀን ሥራ ወይም በደመወዝ ለሚሠራ ሥራ የቅጥር ዝቅተኛ የመነሻ ዕድሜ 14 ዓመት እንደሆነ በሕግ ተደንግጓል። ይህ ዝቅተኛ የመነሻ ዕድሜ ግን በራሳቸው የተቀጠሩ ሕፃናት ወይም ያለክፍያ በሚሰሩ ሕጻናት ላይ ተፈፃሚነት የለውም። ዕድሜያቸው ከ14 እስከ 18 ዓመት የሆኑት አደገኛ በሚባሉ (በፋብሪካዎች ወይም በተንቀሳቃሽ ማሽኖች በሚሰሩ ሥራዎች ወይም በልጆች ጤና ላይ አደጋ የሚያስከትሉ ሥራዎችን ያጠቃልላል) እና የሌሊት ሥራዎች ላይ መሰማራት እንደሌለባቸው ህጉ

ደንግጓል። በ14 እና በ18 ዓመት የዕድሜ ክልል ውስጥ ያሉ ልጆች  በቀን ከሰባት ሰዓት በላይ እንዳይሰሩ እንዲሁም በህዝብ በዓላት በእረፍት ቀናት ወይም  የትርፍ ሰዓት ሥራዎችን መሥራት እንደሌለባቸው ህጉ ይገልጻል። አደገኛ ሥራዎች ተብለው በህጉ የተዘረዘሩት በማሽኖች የሚከናወኑ የፋብሪካ ሥራዎች ወይም የሕፃናትን ጤና አደጋ ላይ የሚጥሉ ማንኛውም ሥራዎች ናቸው። ከተከለከሉ የሥራ ዘርፎች መካከል የመንገደኞች ትራንስፖርት የኤሌክትሪክ ኃይል ማመንጫዎች የከርሰምደር ሥራዎች የመንገድ ጽዳት እና ሌሎች ዘርፎች ይገኛሉ። የ"Labor Inspectors" ማነስ መንግስት ሕጉን ለመተግበር አስቸጋሪ ያደረገው በመሆኑ በርካታ ወጣቶች አደገኛ በሚባሉ ስራዎች ላይ ተሰማርተው ነበር በተለይ በግንባታ ስራ ላይ አደጋ ለመከላከል ሲባል ህጉ ከ16 ዓመት በታች የሆኑ ወጣቶችን የሙያ ት/ቤት ተቀብሎ እንዳያስተምር ያስገድዳል። መንግስት እነዚህን ህጎች በአግባቡ ተግባራዊ አላደረገም።ትግበራቸውን ለመከታተል የተመደበው በጀት ውስን ከመሆኑም በላይ በአግባቡ ባለመተግበራቸው የተጣሉ ቅጣቶች እጅግ በጣም ዝቅተኛ ነበሩ። ምንም እንኳ የጎንደር ዩንቨርሲቲ በ2003 የሥራ ኢንስፔክተሮች ስልጠና የጀመረ ቢሆንም በአገሪቱ ባለው የተቆጣጣሪዎች እጥረት ምክንያት የህጻናት የጉልበት ብዝበዛ የስራ ቦታ ደህንነትና የጤና አገልግሎትን በተፈለገው ደረጃ ተግባራዊ አልሆነም።

የሠራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር የሕፃናት የጉልበት ብዝበዛ ጉዳዮችን የሚከታተለው ከሴቶች፣ ወጣቶችና ሕፃናት ሚኒስቴር ጋር በመተባበር ነበር። በዓመቱ በሁለቱ ሚኒስቴር መሥሪያ ቤቶች ያለው የትብብር፣ የመረጃ ልውውጥና ቅንጅት መሻሻል አሳይቷል። አስከፊ የሕጻናት ጉልበት ብዝበዛ ለማጥፋት አገር ዓቀፍ የድርጊት መርሃ ግብር በዓመቱ መጨረሻ ላይ ተፈርሟል። መንግስት የሕጻናት ጉልበት ብዝበዛን በተመለከተ የግንዛቤ ማስጨበጫ ሥራዎች ያከናወነ ሲሆን ከሕጻናት ጉልበት ብዝበዛ ነጻ የሆነ ቀጣና የሙከራ ፕሮጀክት ተግባራዊ አድርጓል።

ትምህርት ቤት የመግባትን አስፈላጊነትን ለማስገንዘብ በመንግስትና መንግስታዊ ባልሆኑ ድርጅቶች ቅንጅት ሕጻናት በስፋት በእርሻ ሥራ በተሰማሩባቸው አካባቢዎች ማህበረሰብን ማዕከል ያደረጉ የግንዛቤ ማስጨበጫ ሥራዎች ተከናውነዋል። በዓመቱ መንግሥት በግብርና መስኮች የሕጻናትን ችግር ለመቅረፍ በማሰብ የግብርና ሥራዎችን ዘመናዊ ለማድረግ፣ እንዲሁም ትምህርት ቤቶችን ለመገንባት ጥረት አድርጓል።

የሕፃናት የጉልበት ብዝበዛ በገጠርም ሆነ በከተማ ከባድ ችግር ሆኖ ቆይቷል። በገጠርም ይሁን በከተማ ሕፃናት ሥራ የሚጀምሩት ገና በልጅነታቸው ነው። ሕፃናት በተለይ ከእጅ ወደ አፍ በሆነ የእርሻ ሥራ፣ በባሕላዊ ሽመና፣ በዓሳ ማስገር፣ በቤት ውስጥ ሰራተኝነት ተሰማርተዋል። ከቅርብ ጊዜያት ወዲህ በግንባታ ስራ ላይ ቁጥራቸው በርካታ የሆነ ሕጻናት ተሰማርተዋል። በገጠር ያሉ ሕፃናት በተለይ

ወንዶቹ በከብት ጥበቃ፣ በጥቃቅን ንግድ፣ በእርሻ ስራ በአረም ነቀላ እና በሰብል መሰብሰብ ሥራዎች ተሰማርተው የነበረ ሲሆን፣ ሴት ሕጻናት ደግሞ በማገዶ ለቀማና በውሃ መቅዳት ሥራዎች ተሳትፈዋል። ወላጅ አልባ ሕፃናትን ጨምሮ በከተማ ያሉ ልጆች በቤት ውስጥ ሥራዎች ለረጅም ሰዓታት እንዲሰሩ ስለሚደረግ ትምህርታቸውን በአግባቡ ለመከታተል አልቻሉም። በከተማ ያሉ ሕፃናት በግንባታ፣ በማምረቻ ኢንዱስትሪዎች፣ በጫማ መጥረግ፣ በልብስ ስፌት፣ በሽክም ሥራ፣ በታክሲ ረዳትነት፣ በመኪና ጥበቃ፣ በሕዝብ ማመላለሻዎች እና በጥቃቅን ንግዶች እንዲሁም አልፎ አልፎ እንስሳትን በመጠበቅ ሥራ ላይ ተሰማርተው ነበር። አንዳንድ ሕጻናት ክፍያ ሳይሰጣቸው ወይንም አስተማማኝ የስራ ላይ ደህንነት ጥበቃ በሌለበት አካባቢ እንዲሰሩ ተደርገዋል፡፡ የጉልበት ሥራ የሚሠሩ ሕፃናት ብዙውን ጊዜ በአሰሪዎቻቸው የአካል፣ የወሲብና የሞራል ጥቃት ደርሶባቸዋል።

*ተጨማሪ መረጃ አስከፊዎቹ የሕፃናት ጉልበት ብዝበዛ ጥናት ግኝቶች የሚለውን የሥራ ሚኒስቴር ሪፖርት* ከwww.dol.gov/ilab/programs/ocft/tda.htm. *ማግኘት* ይችላሉ።

### *መ. ተቀባይነት ያላቸው የሥራ ሁኔታዎች*

በሀገር አቀፍ ደረጃ ዝቅተኛ የደመወዝ ክፍያ ተብሎ የተቀመጠ የገንዘብ መጠን የለም። አንዳንድ የመንግሥት ተቋማትና የልማት ድርጅቶች ግን በራሳቸው ዝቅተኛ የደመወዝ መጠን ወስነዋል። ትልቁን ቁጥር የያዙት የመንግሥት ሠራተኞች ሲሆኑ፣ ዝቅተኛው የወር ደመወዛቸው 420 ብር (23 የአሜሪካን ዶላር) ነበር። በባንኮችና በኢንሹራንሶች የሚሠሩ ደግሞ ዝቅተኛ ደመወዛቸው 336 ብር (18 የአሜሪካን ዶላር) ነው። የመጨረሻው ዝቅተኛ የገቢ መጠን 315 ብር (17 የአሜሪካን ዶላር) መሆኑን መረጃዎች ያመለክታሉ። ከአጠቃላይ የህዝቡ ብዛት አነስተኛ ቁጥር ያለው የወር ደመወዝተኛ ሲሆን፤ የሚኖረውም በከተሞች አካባቢ ነው። መደበኛ ባልሆነው የስራ ዘርፍ የሚከፈለው ወርሃዊ ደመወዝ ለሰው ልጅ መሰረታዊ ፍላጎቶችን ለማሟላት ከሚያስፈልገው በታች ነው።

የሠራተኛ ሕጉ አንድ ሠራተኛ በሳምንት ውስጥ ቢበዛ ለ48 ሰዓታት መሥራት እንዳለበት፣ እንዲሁም በሳምንት የ24 ሰዓታት እረፍት፣ የትርፍ ጊዜ ክፍያና ከመጠን ያለፈ የትርፍ ሰዓት ስራ ማሰራትን ህጉ የከለክላል። በዓመት ውስጥ ደመወዝ የሚከፈልባቸው 13 የህዝብ በዓላት አሉ። በልማት ድርጅቶችና በመንግሥት የፋይናንስ ተቋማት የሚሰሩ ሠራተኞች የትርፍ ሰዓት ሥራ ክፍያ የማግኘት መብት፣ እንዲሁም የመንግሥት ሠራተኞች ትርፍ ሰዓት የሰሩበትን የማካካሻ ሰዓት የማግኘት መብት እንዳላቸው ተቀምጧል።

መንግሥት፣ ኢንዱስትሪዎችና የሠራተኛ ማህበራት የሥራ አካባቢ ጤናና ደህንነት መስፈርቶች ላይ ተደራድረዋል። መሰረታዊ የሰራተኛ ማህበር እንዲያቋቁሙ ያልተፈቀደላቸው የቤት ሠራተኞች፣ ወቅታዊና ጊዜያዊ የእርሻ ዘርፍ ሰራተኞች የስራ አካባቢ ጤናና ደህንነት ጥበቃ አያገኙም።

የሠራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር የቁጥጥር መምሪያ የስራ ላይ ጤናና ደህንነት መስፈርቶች ተግባራዊ መሆናቸውን የመቆጣጠር ኃላፊነት አለበት። ሥራቸውን በማይጎዳ መልኩ ራሳቸውን ከሥራው የማግለል መብት ነበራቸው። ሀገሪቱ 380 “Labor Inspectors” አሏት። ሆኖም የሠራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር ከበጀት እጥረት የተነሳ መስፈርቶቹን ተፈጻሚ አላደረገም። የሠራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር ውሱን የአስተዳደር አቅም፤የመብት ጥሰት አቤቱታዎችን የመቀበል፤ የመመርመርና የመከታተል ድክመት እና ዝርዝር የሆነ የስራ አካባቢ ጤናና ደህንነት ክትትል መመሪያዎች አለመኖር፣ መስፈርቶቹ በተግባር እንዳይውሉ መሰናክል ሆኗል። በተጨማሪም የሚተላለፉት ቅጣቶች ዝቅተኛ በመሆናቸው የመብት ጥሰቱን ሊገቱት አልቻሉም። ለጊዜያዊ የግብርና ሰራተኞች የሚከፈለው ካሳ፣ ጥቅማጥቅሞችና የስራ ሁኔታ በሰራተኛ ማህበር ከታቀፉ ቋሚ የግብርና ሰራተኞች እጅግ ዝቅተኛ ነው። ምንም እንኳ መንግሥት ሕጉን ተፈጻሚ ለማድረግ ብዙ ባይንቀሳቀስም፣ በተግባር እንደሚታየው በመደበኛው ዘርፍ የሚሠሩት አብዛኛዎቹ ሠራተኞች በሳምንት 39 ሰዓታት ሠርተዋል። ነገር ግን፣ በርካታ የውጭ ዜጎች፣ ስደተኞች እና መደበኛ ባልሆነ ዘርፍ የሚሰሩ ሠራተኞች በሳምንት ከ48 ሰዓታት በላይ ሠርተዋል።

ምንም እንኳን ሠራተኞች አደገኛ ከሆኑ የሥራ ሁኔታዎች ራሳቸውን በማራቃቸው ምክንያት የቅጥር ኮንትራታቸው መቋረጥ እንደሌለበት ህጉ ቢደነግግም አብዛኛዎቹ ሠራተኞች ይህን ካደረጉ ከሥራ ሊባረሩ እንባረራለን በሚል ይሰጋሉ።

የሀገሪቱ የኢኮኖሚ መሰረት በሆነው የግብርና ዘርፍ ውስጥ አደገኛ የሥራ ሁኔታዎች ተስተውለዋል። እንዲሁም በማደግ ላይ ባሉት የግንባታና የኢንዱስትሪ ዘርፎች በተመሳሳይ አደገኛ የሥራ ሁኔታዎች እና የጉልበት ብዝበዛዎች ተስተውለዋል።

* * * * * *